# ጸሎት

በ ዲያቆን አሸናፊ መኰንን

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!
የመጀመሪያ እትም መጋቢት 2001 ዓ.ም.

አድራሻ:- መ.ሳ.ቁ. 1591 ኮድ1110
አዲስ አበባ
ይህን መጽሐፍ ለማከፋፈል ለምትፈልጉ:-
የስልክ ቁጥር 0911-393521
0911-678251 መጠየቅ ትችላላችሁ::

«አእላፈ፣ እመመክሩ አእላፍ፣
አንተ ዘሀለይኮ ወዘወሰንኮ ኢይተርፍ፤»

ትርጓሜው:-

«ዐሥር ሺህ ሰው ተሰብስቦ፣
ዐሥር ሺህ ምክር ቢመክር፤
አንተ ያሰብከውና የወሰንከው አይቀርም::»

## ስጦታ

ለ ______________________

ከ ______________________

ወደሚሰማ አምላክ ተባብረን በመጮህ የኃጢአትና የመከራ ግንብ ፈርሶልን ተስፋችን እንዲፈጸም ጥሪ ከማድረግ ጋር ይህን መጽሐፍ በፍቅር አበረክታለሁ።

ቀን ______________________

ፊርማ ________________

## ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | 7 |
| መግቢያ | 10 |
| ምዕራፍ አንድ — ጸሎት አስትንፋስ ነው | 14 |
| ምዕራፍ ሁለት — ጸሎት መታየት ነው | 20 |
| ምዕራፍ ሦስት — ጸሎት ንግግር ነው | 29 |
| ምዕራፍ አራት — የጸሎት ኃይል | 38 |
| ምዕራፍ አምስት — የጸሎት ምክንያታችን | 45 |
| ምዕራፍ ስድስት — ጸሎትና አገልግሎት | 51 |
| ምዕራፍ ሰባት — እምነት | 59 |
| ምዕራፍ ስምንት — እንደ ፈቃዱ መጸለይ | 65 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ — በስሙ መጸለይ | 73 |
| ምዕራፍ ዐሥር — ኃጢአታችንን መናዘዝ | 80 |

**አርእስት** **ገጽ**


ምዕራፍ ዐሥራ አንድ
የምንለምነውን ማወቅ . . . . . . . . . . . 86

ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት
ትዕግሥት . . . . . . . . . . . . . 92

ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት
ምስጋና . . . . . . . . . . . . .103

ምዕራፍ ዐሥራ አራት
ልመና . . . . . . . . . . . . . . 112

ምዕራፍ ዐሥራ አምስት
ንስሐ . . . . . . . . . . . . . . .125

ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት
ምልጃ . . . . . . . . . . . . . 131

ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት
እግዚአብሔር ይመልሳል. . . . . 139

ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት
የጸሎት ጌጥ . . . . . . . . . . . 145

ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ
የጸሎት እንቅፋቶች . . . . . . . . 153

ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . 164


# መቅድም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

«ጸልዩ!» የሚሉት ቃላት ጣዕም ያላቸው ቃላት ብቻ ሳይሆኑ ማስጠንቀቂያንም ያዘሉ ቃላት ናቸው:: በረከትን ለማግኘትና ከሚመጣውም መዓት ለመዳን መፍትሔ የሚያሳዩን ቃላት ናቸው:: ጸሎት ያለፈውን፣ ያለውንና የሚመጣውን ዘመን የምንባርክበት፣ ውስኑ ሰው ምሉዕ በኵለሄ፣ ደካማው ሰው ሁሉን ቻይ የሚሆንበት መንፈሳዊ መሣሪያ ነው:: ጸሎት እግዚአብሔር ለእኛ መልካምነት ዋጋ የሚሰጥበት ሳይሆን በቸርነቱ እኛን የሚባርክበት የጸጋው መስፈሪያ ነው::

ሠርገኛ በመጣ ቀን ድግስ መደገስ፣ ጦርነት በተጀመረ ቀን ዕቃን መሸከፍ እንደማይቻል እንዲሁም መከራና ስደት ሲመጣ መጸለይ እየተገረፉ እንደ መጮህ ነው (ምሳ. 1፥23-33):: በደግ ቀን ያልጸለዩት በክፉ ቀን አይረዳም:: አቤት አቤት ማለት አሁን ነው:: ዛሬ የምናየውና የምንሰማው መልካም አይደለም:: የዓለም ችግር ከስብሰባና ከነገሥታት ምክክር እያለፈ ነው:: ችግሩም አራርቆ አለመውለድ፣ የኢኮኖሚ መላሸቅ፣ የቴክኖሎጂ እጥረት፣ ዓለም በአንድ መሪ አለመመራቷ፣ በአንድ ገንዘብ አለመገበያየት አይደለም:: ችግሩ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት መላላት ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *«የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?»* (ሉቃ. 18፥8) ያለውን ቃል ስናስብ በጣም ያስደነግጣል:: ይህን ቃል የተናገረው ሳይታክቱ ዘወትር መጸለይ እንዳለባቸው በተናገረበት አንቀጽ ነው:: መጸለይ እምነት ነው:: በመጨረሻው ዘመን ግን የመጸለይ እምነት ጠፍቶ ሰው ሠራሽ መላ ክርስቲያኖች ሳይቀሩ እንደሚፈልጉ የሚገልጽ ነው:: ምእመናንን ትተን አጋልጋዮችን ብንቆጥር ዛሬ በዓለም ላይ ከሚሊየን በላይ ቀሳውስትና ጳጳሳት ይገኛሉ:: ነገር ግን ጌታችን *«የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?»* (ሉቃ.18፥8) አለ::

ዛሬ መፍትሔ ይገኝባታል የምትባለው ቤተ ክርስቲያን በነገሥታት ግልግል የምትኖር፣ በምድራዊ ፍርድ ቤቶች የምትካሰስ፣ የበላዮችዋ ለበታቾች የማይራሩ፣ የበታቾች ለበላዮች የማይገዙባት ሆናለች:: መሪዎቿ የዓለም መፍትሔ ክርስቶስ መሆኑን ለመናገር አፍረዋል:: ቤተ ክርስቲያን ሁሉም በፊቱ ደስ ያለውን የሚያደርግባት፣

አንዱ ራሱን በመጣል፣ ሌላው ልማድን ሃይማኖት በማድረግ፣ አንዱ ከዘመን ጋር መራመድ በሚመስል ንቃት፣ የቀረው ከሁሉም ብሬ በማንሣት እየተሯሯጠባት ይገኛል:: ውጤቱ ምንድነው? ስንል ገንዘብ ለማከማቸት ነው:: «የወፍ ዘፈን አውራጁ አይታወቅም» እንደሚባለው ቤተ ክርስቲያን ሁሉም የሚንጫጫባት፣ ሁሉም እኔ ልክ ነኝ የሚልባት፣ የወንጌል ዳኝነት የጠፋባት ሆናለች:: የሥርዓትና የአምልኮው አጽም ቢቆምም ሕይወት ስላጣ ሕዝቡን ሲያሳርፍ፣ ለአገር ምሕረት፣ ለወገን ቸርነት ለማምጣት አልቻለም:: እውነት የያዙ መንፈሳውያን አገልጋዮች ፍርድና አጥተው በደጅ ቆመዋል:: ባሕልና እምነትን የቀላቀሉ ሰዎች እንዳበደ ውሻ እየተክለፈለፉ ስንቱን ጤነኛ ልጅ ገደሉባት:: ለዚህ ሁሉ . መፍትሔው እርስ በርስ ተስማምቶ የሚቀርብ ከፍቅር ልብ የሚወጣ ጸሎት መሆኑን ማን ይናገር?

ፍሬን የተበጠሰበት መኪና የሚያስደስተው ሲሄድ ሳይሆን ሲቆም ነው:: ፍጻሜው ገደል ነውና:: የቤተ ክርስቲያንም ጉዞ መለኮታዊ መሪነት የሌለው በመሆኑ አስደሳቹ ነገር ቆም ብሎ ከእግዚአብሔር ጋር መስማማት ነው:: ከዘገየን ግን የቁጣው ሰይፍ ከሰገባው እየተመዘዘ ነውና የሚከብድ ውርደት ይገጥመናል:: ክርስቲያን ክርስቲያንን እያሳደደ ብዙ ዘመን አሳለፍን:: በዚህ መሐል አሕዛብ ተረስተው ኃይላቸውን አጠናከሩ:: በመለያየት ያጠነከርነው የአሕዛብ ክንድ በንስሐ ካልተመለስን በአቋም መግለጫ የሚታጠፍ አይደለም:: ከእግዚአብሔር ጋር ስንታረቅ የማይደፈረው መለኮታዊ ቅጥር በዙሪያችን ይሆናል:: ከአረማውያን ጋር እየወገነ ክርስቲያን ወንድሙን ሲወጋ የነበረው ክርስቲያን ዕጣው እንዴት የከፋ እንደ ነበረ በግብፅ፣ በአልጀሪያ፣ በታንዛንያ የምናየው ነው:: እግዚአብሔር መዓቱም ምሕረቱም በእጁ ነውና ብንመለስ የምሕረቱ ጠል ይወርድልናል:: ባንመለስ የመዓቱ ሰይፍ ይቀጣናል:: ዛሬም ቤተ ክርስቲያን አማኞቿን ለእምነትና ለፍቅር እንጂ ለጦርነት ማነሣሣት አይገባትም:: የቤተ ክርስቲያን አጥሯ ቅድስና እንጂ የሥጋ ክንድ አይደለም::

የቤተ ልሔም ሕፃናት ሳያውቁትና ሳያምኑበት ለክርስቶስ ሞቱ:: እነርሱስ ክብር አግኝተዋል:: ሕዝባችን ግን ይልቁንም ወጣቱ የትምህርትና የእምነት ጊዜ እያለው ሳያውቀው ቢሞትለት ክብሩ ምንድነው? ደግሞስ ያልኖርንለትን ክርስቶስ ብንሞትለት እርሱ ራስን በመሠዋት እንጂ በወንድነት መቼ ይከብራል? የዚህ ሁሉ ችግሩ በጸሎት ዘመኑን እየመረመረ የሚናገር አገልጋይ በመጥፋቱ ነው:: በእውነት ካወቅንበት ለማመንም ለመጸፍም ከዚህ ዘመን የተሻለ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን የላትም::



እንዳችን ከእንዳችን የማንሻል ልብሳችን ያደፈ፣ እግዚኦ እግዚኦ ብንልም ጭቃ ላይ ተቀምጠን እጠበኝ የምንል፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ የበደልን ሕዝቦች ነን:: እስተያየት ከመስጠት ወጥተን እድነን በሚለው ጸሎት ወገናችንን ካልሆነም ራሳችንን እናድናለንና እንጸልይ! ብዙ ዘመን ተካሰስን የምድራችን ችግሩ ነገሥታቱ ናቸው እልን፤ መፍትሔ አልመጣም:: ጳጳሳት ናቸው አልን፤ መፍትሔ አልመጣም:: እርሱ ነው እርሷ ነች በሚለው መጠቋቆም የቤታችንና የአገራችን መናወጥ አላቆመም:: ሁላችንም በድለናል:: ንስሐ መግባት አለብን:: ይህ ልዩ የሆነ የመጨረሻው መጀመሪያ ሰዓት ነውና እንጠቀምበት:: እንደ ዮናስ ለመርከቡ መናወጥ ምክንያቱ እኔ ነኝ እንበልና ራሳችንን በመጣል ማዕበሉ ጸጥ ይበል! የከፋውን ቀን መከራ መቋቋም አልችልም፣ የወገኔንም ሥቃይ ቆሜ ማየት አይሆንልኝም የምንል ይቅር እንባባል! ተግተን እንጸልይ!

# <u>መግቢያ</u>

ምድራዊው ሰው ከሰማያዊ አምላክ ጋር የሚገናኝበት መስመር ጸሎት ተብሎ ይጠራል። ታላላቅ ውሳኔዎች ሁሉ ከሰማይ ተወስነዋል። ሰው ሆነን መፈጠራችን፣ በዚህ አገር መወለዳችን፣ በዚህ ዘመን መገኘታችን፣ የምንኖርበት የዕድሜ ስፍር፣ ራሳችንን የምናገኝበት ቤተሰብ የእግዚአብሔር ውሳኔ ወይም የሰማይ አዋጅ ነው። በሕይወታችን ዋና ዋና ነገሮች ከሰማይ ጋር የተያያዙ ከሆኑ ዕለታዊ ኑሮአችንም ከሰማይ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳለው እርግጥ ነው። ዕለታዊ ግንኙነትን ከምናደርግበት መንገድ አንዱና የመጀመሪያው ጸሎት ነው።

እግዚአብሔር የኅብረት አምላክ ነው። ህልውናውም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚባል አንድነት ነው። ሰውን የፈጠረው ባሕርዩን ሊያካፍለው፣ ፍቅሩን ሊገልጽለት ነው። በገነት ውስጥ ለሰው ልጅ ከተሰጠው ትልቅ ጸጋ አንዱ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው። የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረጉ የልምምድ ውጤት ወይም በታሪክ ያገኘው ትርፍ አይደለም። ተፈጥሮአዊ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲያደርግ ሆኖ የተፈጠረ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር በቋሚነት ኅብረት ከሚያደርግባቸው የግንኙነት መሣሪያዎች አንዱና ቀዳሚው ጸሎት ነው።

በሰው ተፈጥሮ ውስጥ እግዚአብሔር ካልሆነ ማንም ሊደፍነው የማይችል፣ በምድራዊ ሙላቶች የማይካካስ፣ መርሳትን ምክንያት በማድረግ ተዘንግቶ የማይታለፍ የሕይወት ቀዳዳ አለ። የሰው ልጅ ያለ እግዚአብሔር በራሱ መኖር የማይችል፣ እርካታንም ለራሱ ማበጀት የማይችል ደካማ ፍጡር ነው። የትም ባዝኖ፣ ለራሱ አስቦ ለራሱ ደግ መሆን ሲያቅተው ወደ ፈጠረው አምላክ፣ ወደ አዳነው ጌታ መመለስ ይፈልጋል። ውሎ ውሎ ከቤት፣ ኖሮ ኖሮ ከመሬት እንደማይቀር ሰውም ከመንከራተት በኋላ ወደ አምላኩ ይመለሳል።

ምእመን ለእግዚአብሔር የታመቀ ብሶቱን፣ ለአምላኩም ከፍ ያለ ሐዘኑን የሚገልጸው፣ ኃጢአቱን ተናዝዞ ሸክሙን የሚያቀለው፣ ደካማ እሱነቱን አስረክቦ በዕረፍት የሚኖረው በጸሎት አማካይነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለአሁን ብቻ ሳይሆን ላለፈውና ለሚመጣውም ዘመን እንደሚያስፈልገን፣ ያለ እግዚአብሔር ሕይወታችን የተበተነ ነዶ፣ ፍሬ የሌለው ልምላሜ፣ ያልተቋጨ ራእይ፣ ያላለቀ ሩጫ፣ ድል አልባ ትግል፣ ፍቅር የለሽ አገልግሎት



መሆኑን ይገልጽልናል። ይህንን አሳብ በይበልጥ ከሚያስረግጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሁለቱን እንጠቅሳለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው የጽድቅ መልእክት ውስጥ፦ *«ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን»* (ሮሜ. 11፥36) ይላል። «ሁሉ» የሚለው ቃል ሰማይና ምድርን ኃላፊና መጻያትን ይጠቀልላል። በሌላ ስፍራም *«ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም»* (ዮሐ. 1፥3) ይላል። ታሪክ እንኳ ሳይቀር እግዚአብሔር ወዳቀደለት ፍጻሜ እየተጓዘ ነው። «ሁሉ» የሚለው ቃል የእኛን ብቻ ሳይሆን የዓለሙን ህልውና ይጠቀልላል። ብዙ ነገሮች ጥያቄ በሆኑብኝ ሰዓት፣ የተቀመጥኩበት መቀመጫ ሲነቃነቅ፣ የቤቴ ጣራ ሲነደል፣ ደስታና መርዶ በአንድ ጊዜ ስሰማ፣ ዕንባና ሳቅ ሲቀላቀሉብኝ *«ሁሉ በእርሱ ሆነ»* የሚለው ቃል ልቤን አሳርፎታል። ሐዋርያው «ሁሉ <u>ከ</u>እርሱና <u>በ</u>እርሱ <u>ለ</u>እርሱም ነውና» ብሏል። ከ- በ - ለ የሚሉት ገላጭ ቃላት ኃይል አላቸው። «ከእርሱ» ሲል የነገሮች ሁሉ መሠረት፣ የታሪክ ሁሉ መነሻ፣ የፍጥረት ጉዞ ሁሉ ጀማሪ፣ የመፍጠርና የማዳን ዕቅድ አውጪ እግዚአብሔር መሆኑን ይገልጻል። ሁሉ ከእርሱ ሲል እግዚአብሔር አብን ይጠቅሳል በማለት አባቶቻችን ይተረጉማሉ። «በእርሱ» የሚለው ቃል ደግሞ የዕቅዱ ፍጻሜ፣ የጅምሩ ግብ፣ የውጥኑ መሳካትና መሆን በእግዚአብሔር እንደሆነ ሲገልጽ ይህም ወልድን የሚወክል ቃል ነው። «ለእርሱ» የሚለውም ቃል የዕቅዱ ስምረት፣ የማዳኑ ውጤት ክብሩ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚሰጥ ሲሆን ይህም መንፈስ ቅዱስን ይገልጣል። ስብሐት፣ ውዳሴ፣ አኰቴት መለኮታዊ ዳርቻቸው መንፈስ ቅዱስ ሲሆን ከሥላሴም ተርፎ ለሌላ የማይሰጥ ነው።

ዛሬ ዘመናዊውን ዓለም በእንስራ ውስጥ እንደ ገባ ወተት የሚንጠው ምንድነው? ስንል «ሁሉ ከእኔ፣ ሁሉ በእኔ፣ ሁሉ ለእኔ» የሚለው መመሪያ ነው። ሥልጣኔውና ቴክኖሎጂው በቂያችን ነው፣ እንደ ደካማ እግዚአብሔር ማለት ምን ይሠራል? እግዚአብሔር ቢኖርም እጅና እግርን አጣጥፋችሁ ጸልዩ አይልም፣ ሥራ ማለት ጸሎት ነው የሚል አስተሳሰብ ውስጥ ስለገባን ሕይወታችን ፍጹም መረጋጋት አጥታለች። ጸሎት ሁሉ ከእርሱ እንደሆነ አምነን ፈቃዱን የምንጠይቅበት፣ ሁሉ በእርሱ መሆኑን አምነን ድካማችንን የምናስታውቅበት፣ ሁሉ ለእርሱ መሆኑን አምነን ስለሆኑና ስላልሆኑ ነገሮች ምስጋና የምናቀርብበት መንገድ ነው።

ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ቍጥር 5 ላይ ያለው ቃል ነው:- *«ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና»* ይላል:: ይህ ቃል የሥነ ልቡናው ዓለም ያስታጠቀንን «እችላለሁ» ባይነትን የሚጥል፣ የእኔነትን መንግሥት የሚያፈርስ፣ እንደ ሕፃን ልጅ በሁለንተናችን በእግዚአብሔር ላይ ተደጋፊ እንድንሆን የሚጋብዝ ነው::

መንፈሳዊ ተግባራት፣ ቅድስና፣ ከኃጢአት ጋር ያለን ትግል፣ ፍሬያማ አገልግሎት ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ረዳትነት ድካም ብቻና ከሽንፈት ውጭም ድል የሌላቸው ሙከራዎች ናቸው:: እንዲሁም ሥጋዊ ሩጫችን ያለ እግዚአብሐር ከንቱ፣ ነፋስን ለመጨበጥ እንደ መሮጥ ነው:: ይህን ቃል የሚያጠናክርልን ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ:- *«እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፥ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፥ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል፤ በማለዳ መገሥገሣችሁም ከንቱ ነው:: ለወዳጆቹ እንቅልፍን በሰጠ ጊዜ እናንተ የመከራን እንጀራ የምትበሉ፥ ከተቀመጣችሁበት ተነሡ»* የሚለው ነው (መዝ. 126፥1-2):: ክሰው በፊት መነሣት ከሰው በኋላ አምሽቶ መግባት አይደለም የሰው ስኬት! እግዚአብሔር ሲረዳን ብቻ ነው:: የጸሎትን መሣሪያ የምንጠቀመው ያለ እግዚአብሔር የሚሆን አንዳች ነገር ስለሌለ ነው::

ዘመናዊነት እግዚአብሔርን ባያከብርም በእግዚአብሔር ጥበብ ወደ ሥልጣኔ ደርሰናል:: ቴክኖሎጂው የሰውን ጊዜና ጉልበት ያዳነ ፍጥነትና ጥራትን ያመጣ ነው:: እንዳለፉት ትውልዶች የአሁኑ ትውልድ ብዙ ጉልበትና አቅም አያባክንም:: ምክንያቱም ቴክኖሎጂው እያገዘው ስለሆነ ነው:: በዘመናዊው ቴክኖሎጂ የማይተካ ነገር ቢኖር ጸሎት ነው:: ዘመናዊውን ቴክኖሎጂ ከሚጠቀሙ ሰዎች ይልቅ የበለጠ መሣሪያ የሚጠቀሙ ቢኖሩ ጸሎተኞች ናቸው::

በዛሬው ዘመን በዙሪያችን የከበበን ነገር ሁሉ የጸሎት ርእስ ነው:: አገልጋይ እንደ መሆኔ በአካልም ሆነ በስልክ ሰዎች እውነተኛ ስሜታቸውን ሲገልጡልኝ እሰማለሁ:: ሁሉ ሞልቶልናል ጸሎት ለእኛ አስፈላጊ አይደለም ብንል እንኳ ብዙ የጎደለባቸው ሰዎች በዙሪያችን አሉ:: የእጃችንን ሀብት፣ የቃላችንን ማጽናናት መስጠት ብቻ ሳይሆን ጊዜ ሰጥተን ልንጸልይላቸው የሚገባ የመከራ መመላለሻ የሆኑ ሰዎች እንደ አየሩ ዙሪያችንን ከበውናል::



ዕንባዎች ያለ ማቋረጥ ሲፈስሱ እናያለን:: በልቅሶ የሚቆራረጡ ድምፆችን በስልክ እናስተናግዳለን:: *«የነጋው ጠዋት የሚመሽ፣ የሚዋል አልመሰል አለኝ እባክህ የሚያውል ቃል ንገረኝ»* የሚሉ ተማጽኖዎች ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር እየበረከቱ ነው:: በበሽታ የተጎዱ፣ መድኃኒታቸው ላይ ጸልዩልን የሚሉ ወገኖች አሌ የማይባሉ ናቸው:: በሕክምናው ተስፋ የቆረጡ፣ ከሐኪሙ በላይ የመድኃኒት ዓይነትን በቃላቸው የሚናገሩ ግን መድኃኒቱ መድኃኒት ያልሆነላቸው ሰዎች በየዕለቱ ይገጥሙናል:: ከዚህ በፊት የማናውቃቸው በታክሲ መጠበቂያ ስፍራ በድንገት ያገኘናቸው ሰዎች ትንሽ የምንሰማቸው መሆኑን ካወቁ የቤታቸውን ምሥጢር ያለ ይሉኝታ ይነግሩናል:: ብዙ ገንዘብ ያጡ ሰዎች አሉ ከዚያ በላይ ገንዘብ እያላቸው ሰላም ያጡ ሰዎች ልቅሶ በዝቷል:: ሕፃናት ሕይወታቸው ዋስትና እያጣ የሌሎች ግፍ ማርኪያ እየሆኑ ነው:: ወጣቶች ተስፋ በመቍረጥና በአደንዛዥ ዕፅ ተጠቅተዋል:: ወደ እግዚአብሔር ቤት በባዶነት መጥተው በባዶነት የሚመለሱ ወገኖች በዝተዋል:: በቤተ ክርስቲያን የሰይጣን ሰርጎ ገቦች ገብተው አደባባዩንና አመራሩን ተቆጣጥረዋል:: ነገሥታት ለራሳቸውም ሆነ ለሚመሩት ሕዝብ ዋስትና አጥተው ተጨንቀዋል:: ከዚህ ሁሉ በላይ ዓለም ወደ ፍጻሜ እያመራ ባለበት ሰዓት ትልቁ መፍትሔ ምንድነው? ስንል በክርስቶስ አምኖ የጸሎትነት ኃይል መጠቀም ነው::

በዓለማችን ላይ ያሉት ችግሮች ለብዙ ጋዜጠኞች፣ ደራሲያን ... እንጀራ ሲሆኑ ይችላሉ:: ለክርስቲያን ግን የጸሎት ርእሶች ናቸው:: ክርስቲያን ፀሐፊያንም በዓለም ላይ ያሉትን ችግሮች ቢገልጹም አብዛኛው ችግር ግን ጸሎትን የሚፈልግ መሆኑ አልገባቸውም:: መጸለይ ብንችል እርስ በርሳችን ለመነቃቀፍ ጊዜ ባላገኘን ነበር:: ይህ ጽሑፍ አብዝተን ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት እንድንገናኝ ያስገነዝባል:: የጸሎትን ትርጉምና ጸሎት ሲያሟላቸው ስለሚገቡ ነገሮች ይናገራል:: እግዚአብሔርን የምናመልከው እንደ ፈለግነው ሳይሆን እርሱ በሰጠን የአምልኮ መስፈርት መሆኑን ያስረዳል:: ይህን መጽሐፍ ከዚህ በፊት ካሳተምኩት «ተንሥኡ ለጸሎት» ከሚለው መጽሐፍ ጋር አብራችሁ ብታነቡት ጥልቅ ወደ ሆነ የጸሎት ትርጓሜ ትደርሳላችሁ:: ጸልዩ! ጸሎት ለሚያስፈልገው ሁሉ ጸልዩ! ለሰውና ለእንስሳት ጸልዩ! በጸሎት እድልኦ የለምና ለሁሉ ጸልዩ! ለእኔ ለደካማ ወንድማችሁም እባካችሁ ጸልዩ! እግዚአብሔር እእምሮአችሁን ይባርክ!

# ምዕራፍ አንድ

## ጸሎት እስትንፋስ ነው

*«ዓሣ ከውኃ ከተለየ ክርስቲያንም ከጸሎት ከራቀ ሕይወት የለውም።»*

የጸሎትን ሕይወት የተለማመዱ የቀደሙት አባቶች ለጸሎት ብዙ ምሥጢራዊ ፍችዎችን ሰጥተዋል። ከዚያ ውስጥ *«ጸሎት እስትንፋስ ነው»* የሚለው ትርጉም ቀዳሚ ሆኖ እናገኘዋለን። እነዚህ አባቶች ለጸሎት የሰጡት ትርጓሜ ከልምምዳቸው እንጂ ከምርምራቸው የተገኘ ስላልሆነ በኑሮ የተፈተነ ትርጉም ነው። እስትንፋስ ከሕይወት ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት አለው። እስትንፋስ የሚጠራበት ሌላው ስያሜ ሕይወት የሚለው ነው። ያለ እስትንፋስ መኖርና የሕይወትን ቀጣይነት ማረጋገጥ አይቻልም። የእስትንፋስን አንገብጋቢነት፣ ለእጥንት ልምላሜ፣ ለህልውና ቀጣይነት፣ ለልብ ሕያውነት ያለውን አስተዋጽኦ አገናዝበው ጸሎትን እስትንፋስ ማለታቸው አስደናቂ ነው።

አንድ አባት «ዓሣ ከውኃ ከተለየ ክርስቲያንም ከጸሎት ከራቀ ሕይወት የለውም» ብለዋል። ጸሎት የክርስቲያን እስትንፋስ ነው። ጸሎት የክርስትና እስትንፋስ ከሆነ የማያቋርጥ የሕይወት ሂደት ነው ማለት ነው። አንድ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕልውናውን ጠብቆ ለመቆየት ጸሎት ቃሉና ኅብረት ያስፈልጉታል። ከእነዚህ ከሦስቱ ነገሮች የራቀ ክርስቲያን ወደ ኋላ ለመመለስና ብሎም እስከ መካድ ይደርሳል። የክርስትናን ሕይወት ጠብቆ ለመቆየት ጸሎት አስፈላጊ ነው። ቃሉና ኅብረትም ኃይል የሚያገኙት በጸሎት ነው። እስትንፋስን የሚታገሉ በሽታዎች አሉ። ለምሳሌ፦ የአስም በሽታን ብንመለከት በሽተኛውን በቂ አየር በማሳጣት ለሥቃይ ይዳርገዋል። የሕይወትን ሩጫ ሊጨርሱ የተቃረቡ ሰዎች መተንፈስ ስለሚያቅታቸው መተንፈስን የሚያግዙ መሣሪያዎች ተገጥመውላቸው ይታያሉ። የሚያያቸው ሰውም ወደ ሞት የተቃረቡ መሆናቸውን እያየ ያዝንላቸዋል። ጸሎትም እስትንፋስ በመሆኑ በበቂ ሁኔታ መግባትና መውጣት ካልቻለ ምእመኑ ያለው የመንፈስ ሞት ዋዜማ ላይ ነው።



የጸሎትን እስትንፋስነት ከሚገልጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች የተሰሎንቄን መልእክት የሚተካከለው የለም፦ *«ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና»* (1ተሰ. 5፥16-18)። ይህ ንባብ ምክር፣ ትእዛዝ፣ ማጽናናት ያለበት ነው።

*«ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ»* ይህን ጥቅስ የምናገኘው በዚህ ክፍል ብቻ አይደለም። በፊልጵስዩስ 4፥4 ላይም *«ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ፥ ደስ ይበላችሁ»* ይላል። አንድ ሰው ደስ ይበልህ ብንለው በምን? ይለናል። መልሱ «በጌታ» የሚል ነው። ሁልጊዜ በሁኔታዎች፣ በዚህ ዓለም ተለዋዋጭ ነገሮች መደሰት አይቻልም። ሁልጊዜ ግን በማይለወጠው እግዚአብሔር የመደሰት መንፈሳዊ መብት ተሰጥቶናል። *«ደስ ይበላችሁ»* የሚለው ቃል የትእዛዝ አንቀጽ ነው። ስለዚህ መደሰት ከምንፈጽማቸው ትእዛዛት አንዱ ነው። ሕፃን ልጅ በዚህ በችግርና በውጣ ውረድ ዓለም ላይ የሚደሰተው ስለማያውቅ ብቻ አይደለም። በወላጆቹ ስለ ረካና ሁሉን ይችላሉ ብሎ ስለሚያምን ነው። እኛም እግዚአብሔር በህልውናውና በተቀደሱት ጠባያቱ ከእኛ ጋር ስላለ ብቻ ደስ ሊለን ይገባል። ይህ ካላስደሰተን ዓለምና ሞላው የእኛ ቢሆንም ደስ አይለንም።

ለጸሎት ከሚያስፈልጉን ነገሮች አንዱ በእግዚአብሔር መደሰት ነው። ጸሎትን ከምናቆምባቸው ምክንያቶች የመጀመሪያው በእግዚአብሔር ማኩረፍ እንደሆነ፤ ከሚያጸልዩን ነገሮች አንዱም በእግዚአብሔር መደሰት ነው። ነባራዊውንና ተመላላሹን የዓለምን ጠባይ ስንመለከት ይልቁንም በመረጃ ሕይወት ላይ ስንመሠረት ደስተኛ መሆን በፍጹም አይቻለንም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሳዝኑ ነገሮች በሞሉበት ዓለም ላይ ለደስታ ቢጋብዘን ትክክለኛ ነው ወይ? ማለታችን አይቀርም። ደስታ ግን በዓለም ላይ ያለ፣ ሰው ለሰው፣ ወይም ቁሳቁስ ለሰው የሚሰጠው ነገር አይደለም። ደስታ የእግዚአብሔር ነው። ደስታን ከምናገኝበት መንገድ አንዱም የጸሎት ሕይወት ነው።

ነቢዩ ዳዊት *«እግዚአብሔርን አሰብኩት ደስም አለኝ፤»* (መዝ. 76፥3) ብሏል። ብዙ ነገሮች ሲያስቧቸው ያሳዝናሉ። ላለማሰብ ነው መጠጥ፣ ቲያትር፣ ዝሙት፣ ዘፈን የሚፈለጉት። ሲያስቡት ደስ የሚያሰኝ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔርን ከምናስብበት፣ ውበቱን ከምናይበት መነጽር አንዱና ዋነኛው ጸሎት ነው። የእግዚአብሔር ሰው ስለ ሆነው ስለ ሙሴ የተነገረውን ቃል ስናስብ

ልባችን በሐሴት ይሞላል፡፡ *«እንዲህም ሆነ፤ ሙሴ ከሲና ተራራ በወረደ ጊዜ ሁለቱ የምስክር ጽላቶች በሙሴ እጅ ነበሩ፤ ሙሴም ከተራራው በወረደ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ተነጋገረ የፊቱ ቁርበት እንዳንጸባረቀ አላወቀም ነበር፡፡ አሮንና የእስራኤልም ልጆች ሁሉ ሙሴን ባዩ ጊዜ፥ እነሆ የፊቱ ቁርበት አንጸባረቀ፤ ወደ እርሱም ይቀርቡ ዘንድ ፈሩ»* (ዘፀ. 34፥29-30)፡፡

ብሩህ ፊት ትልቅ ጸጋ ነው፡፡ ለሰዎችም ከምናቀርበው ከማንኛ ውም ግብዣ የሚበልጥ ነው፡፡ ብሩህ ፊት የደስተኛ ልብ ውጤት ነው፡፡ ልብ ደግሞ ደስተኛ የሚሆነው እግዚአብሔርን ሲያስብ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔርን የምናስበው በጸሎትና በጽሞና ነው፡፡ ሙሴ በእግዚአብሔር ፊት ለዐርባ ቀንና ለዐርባ ሌሊት በመቆየቱ ፊቱ በራ፡፡ ቃልንም ተቀበለ፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ስንቆይ እነዚህን ሁለት በረከቶች እንቀበላለን፡- ደስታንና መሪ ቃሎችን፡፡ የእኛም ፊት በደስታ የሚፈካው በእግዚአብሔር ፊት ስንቆምና የእግዚአብሔር ብርሃን ሲሳልብን ብቻ ነው፡፡

## ሳታቋርጡ ጸልዩ

አየር የማያቋርጥ የሕይወት ሂደት ነው፡፡ የምንተነፍሰው በተራ ሳይሆን ባለ ማቋረጥ ነው፡፡ ዛሬ ያለነው ትላንት በሳብነው አየር፣ አሁን ያለነው ቅድም በገባው አየር አይደለም፡፡ ከአየር ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት እያደረግን ነው ያለነው፡፡ እንዲሁም ያለ ማቋረጥ እንድንጸልይ ታዝዘናል፡፡ ምክንያቱም ጸሎት እስትንፋስ ነውና፡፡ ደግመን የምናስበው ቃል አለ፡- «ዓሣ ከውኃ ከተለየ ሕይወት እንደ ሌለው ክርስቲያንም ከጸሎት ከራቀ ሕይወት የለውም፡፡»

ጸሎት እስትንፋስ ነው የሚለው ቃል ኃይል ያለውና ገላጭ ቃል ነው፡፡ ስንተነፍስ የተቃጠለው አየር እየወጣ በምትኩ አዲስ አየር ይገባል፡፡ እንዲሁም ስንጸልይ በተቃጠለ አየር የሚመሰለው ጭንቀታችን፣ ብሶታችንና ፍርሃታችን እየወጣ በአዲስ አየር የሚመሰለው ተስፋ፣ ፍቅርና ሰላም ወደ ውስጣችን ይገባል፡፡ በጸሎት ውስጥ ያለው ደስታ በምላሹ የሚገኝ ሳይሆን ከሚሰማን አምላክ ጋር በመነጋገራችን ብቻ የሚሆንልን ደስታ ነው፡፡ እግዚአብሔር ምላሽ ባይሰጠን እንኳ ጊዜ ሰጥቶ ስለ ሰማን ደስ ሊለን ይገባል፡፡

ባሕር በራሱ አየር ስለ ሌለው ወደ ባሕር የሚጠልቁ ጠላቂዎችና ዋናተኞች አየር ስበው ይገባሉ፡፡ የሳቡት አየር ሲያልቅ እንደ ገና ብቅ



ብለው ይጠልቃሉ፡፡ ባሕር የዓለም ምሳሌ መሆኑን ብዙ የአገራችን ሊቃውንት ተናግረዋል፡፡ ባሕር የራሱ አየር እንደ ሌለው ይህ ዓለምም በራሱ ተስፋና ሰላም የሌለው ዓለም ነው፡፡ በማለዳ ተነሥተን ወደ ሥጋ ተግባራችን መሄድ ወደ ባሕር እንደ መጥለቅ ነው፡፡ ስለዚህ የቃሉንና የጸሎትን አየር ስበን ልንገባ ይገባል፡፡ የሳብነው የጸሎትና የቃሉ አየር ሲያልቅም እንደ ገና መሳብ ይገባናል፡፡ አንዳንዴ ቶሎ ሊያልቅ ይችላል፡፡ አየሩ ሲያልቅ ምልክት አለው፡፡ ራሳችንንና አካባቢውን መቀበል ያቅተናል፡፡ በድንገት መብራት እንደ ጠፋ ተስፋችን ይቋረጣል፡፡ ፍቅር አልባ እንሆናለን፡፡ ለመኖር አቅም እናጣለን፡፡ ይቅር ያልነውን ቂም ማስታወስና አጠገባችን ያሉትን ሰዎች ከጐዱን ክፉ ሰዎች ጋር ማመሳሰል እንጀምራለን፡፡ ይህ አየሩ እንዳለቀ ምልክት ነው፡፡ ስለዚህ ፈጥነን መጸለይና የቃሉን ዘለላ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ማንበብ ይኖርብናል፡፡ ምናልባት ባለ ጉዳይ ተሰልፎ ሊሆን ይችላል፡፡ ለጥቂት ሰዓት መጸዳጃ ቤትም ቢሆን ገብተን መጸለይና የቃሉን ፍሬ ከመጽሐፍ ቅዱስ መልቀም አለብን፡፡ ዛሬ ያለነው ትላንት በሳብነው አየር አይደለም፡፡ እንዲሁም በትላንት ብርታታችን የዛሬን ክርስትና እንደሚገባ መኖር አንችልም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል *«ሳታቋርጡ ጸልዩ»* ይላል፡፡ አዎ ጸሎት እስትንፋስ ነው፡-

- እስትንፋስ የማያቋርጥ የሕይወት ሂደት ነው፡፡
- ስንተነፍስ የተቃጠለው አየር እየወጣ አዲስ አየር ይገባል፡፡
- ዓለም አየር የሌላት ባሕር ናት፡፡ አየሩ ጸሎትና ቃሉ ነው፡፡

## «በሁሉ አመስግኑ»

ጸሎት ማለት ጥያቄን (ጉድለትን) ለእግዚአብሔር ማሰማት ብቻ አይደለም፡፡ ጸሎት ምስጋናንም የሚያካትት ነው፡፡ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ዓላማ አንዱ ምስጋና ነው፡፡ ስሙን ለመቀደስ፣ ክብሩን ለመውረስ ተፈጥሯል፡፡ በሰማይም ዘላለማዊ ሆኖ የሚቀጥለው ልመና ሳይሆን ምስጋና ነው፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን አድርጎልናል፡፡ የውለታው ክፍያ ሳይሆን የውለታው መታሰቢያ የሚሆን ምስጋናችን ይገባዋል፡፡ ያደረገልንን እንኳን በሙሉ ለመክፈል ይቅርና ምን ያህል እንደ ሆነ መጠኑንም መረዳት አይቻለንም፡፡ ራሱ እግዚአብሔር ብቻ እንዳደረገልን የሚያውቀው ብዙ ተአምራት አለ፡፡ እግዚአብሔርም ስላደረገልን ነገር ከምስጋና የበለጠ ዋጋ አለመጠየቁ ይገርማል፡፡ ሴትዮዋ «እግዚአብሔር ይህን ሁሉ አድርጎልሽ ተመስገን ብቻ ነው ወይ የምትይው?» ቢሏት «እኔ ምን ላድርገው ተመስገን ብቻ በሉኝ

ብሎ ዋጋውን ያሳነሰው እርሱ ራሱ ነው» ብላለች:: ለምስጋና የሚያነቃን ነገር ቢኖር «ማሰብ» ነው:: ስናስብ ማመስገን እንጀምራለን::

ምስጋና የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነው:: ስላደረገልን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እግዚአብሔር ስለሆነም ልናመሰግነው ይገባል:: በዚህ ክፍል ላይ ግን ሐዋርያው «በሁሉ አመስግኑ» አለ:: ቃሎቹ *ሥጋዊውን* አቅም የሚፈትኑ ይመስላሉ:-

- ሁልጊዜ ______________
- ሳታቋርጡ ______________
- በሁሉ ______________

ሁልጊዜ፣ ሳታቋርጡ፣ በሁሉ የሚሉት ቃላቶች ከባድ ይመስላሉ:: እግዚአብሔር ግን ከባድ ትእዛዝ አልሰጠንም:: የከበሩ ትእዛዛት ስንሰማቸው ይከብዳሉ ሲፈጸሙ ግን ይቀላሉ:: ምክንያቱም ስንንቀሳቀስ መንፈስ ቅዱስ ስለሚረዳን ነው:: በሁሉ ማመስገን ከባድ አይደለም:: ምክንያቱም እንደ እኛ ሰው የነበረው ኢዮብ እንዳመሰገነ ተጽፏል:: ኢዮብ የሚያመልከው ያለውን ነገር ሳይሆን እግዚአብሔርን በመሆኑ በዙሪያው የሚያየው ነገር ቢያጣ እንኳ የማይታየውን ጌታ በእምነት እያየ አመሰገነ:- *«ራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጥቻለሁ፥ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ! እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን»* (ኢዮብ 1፥21) አለ::

ሐዋርያውም *«በሁሉ አመስግኑ»* አለ:: ስለ ማጣቱም ስለ ማግኘቱም፣ ስለ ሕመሙም ስለ ጤናውም፣ ስለ ከፍታውም ስለ ዝቅታውም፣ ስለ ክብሩም ስለ መዋረዱም አመስግኑ ማለቱ ነው:: ክርስትናችንን ልዩ የሚያደርገው በማይመቹ ሁኔታዎች ውስጥ ዝማሬ ስንጀምር ነው:: በምቹ ስፍራማ ማንም ሊያመሰግን ይችላል:: በማይመቹ ስፍራዎች ያለ ምስጋና:-

- የአሁኑን መከራ ሳይሆን የሚመጣውን ክብር ማሰብ፣
- የሚታየውን ጉዳት ሳይሆን የማይታየውን የእግዚአብሔር ክብር ማየት፣
- ከችግሩ በላይ የክርስቶስን ጉልበት ማመን፣
- ችግርን እያዘኑ እያለቀሱ ከማዳነቅ ለእግዚአብሔር ብቻ ክብር ሰጥቶ ጠላትን ማሳፈር ነው:: (ለችግር ማዘንና ማልቀስ ችግሩን ማወደስ ነውና)::



እግዚአብሔርም *ሥራህ* ትክክል ነው ሲሉት ይወዳል:: ስለዚህ ምስጋና በጀመርንበት ጉድለት *መሥራት* ይጀምራል:: ምስጋናውም ወደ ድል እየተለወጠ ይመጣል:: ጠላትም በጣም ያፍራል:: ሰይጣን ሌላ ውጊያ ይጀምራል እንጂ ምስጋና በጀመርንበት ጉዳይ *መሣሪያውን* አያባክንም::

ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ እስር ቤት ሳሉ በእኩለ ሌሊት፣ በእጅና በእግር ብረት ውስጥ ሆነው ዝማሬ ጀመሩ:: *«ድንገትም የወኅኒው መሠረት እስኪናወጥ ድረስ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ፤ በዚያን ጊዜም ደጆቹ ሁሉ ተከፈቱ የሁሉም እስራት ተፈታ»* (የሐዋ. 16፥26):: ምስጋና ኃይል አለው:: የተዘጋውን ደጅ ይከፍታል፣ እስራትን ይፈታል:: የእግዚአብሔርን ህልውና ከኃይል ጋር ይጋብዛል:: ጳውሎስና ሲላስ ዝማሬ የጀመሩት የዜማ መሣሪያዎች መግቢያ ሰጥተዋቸው፣ በድምፅ ማጉያ ታጅበው፣ የዘማሪ ቡድን እየተቀበላቸው፣ የኖታ ሕግጋትን ጠብቀው አልነበረም:: የዘመሩት በእኩለ ሌሊት፣ በወኅኒ ቤት፣ በእግርና በእጅ እስራት ውስጥ ሆነው ነው:: በቀትር መዘመር ቀላል ነው:: በእኩለ ሌሊት ለመዘመር ግን የሚያየንን ጌታ ማየት ይጠይቃል:: ድምፅ አማረልኝ ብሎ መዘመር የገቢ ምንጭ ነው:: በቁስል ውስጥ ሆኖ መዘመር ግን ጥልቅ ክርስትና ነው:: በሁሉ ማመስገንን የተለማመደው ጳውሎስ ነው *«በሁሉ አመስግኑ»* ያለው::

«ሁልጊዜ» «ሳታቋርጡ» «በሁሉ» የሚሉት ቃላቶች ጸሎት የማያቋርጥ የሕይወት ሂደት ወይም እስትንፋስ እንደ ሆነ ይገልፃሉ:: *ማሣሪያው ቃል «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና»* (1ተሰ. 5፥18) ይላል:: ቢያመንም፣ ብናጣም፣ ቢጎድልብንም በትዳራችን እንኖራለን:: አየሩን እያየን ሳይሆን ሁልጊዜ በትዳራችን እንኖራለን:: ኑሮአችን ነውና:: ከሁሉም ስሜታችን ጋር *ሥራችንን* እንሠራለን:: ጸሎትም የሕይወታችን ዋነኛ ክፍል ደግሞም *ሥራችን* ነው:: ስለዚህ ሁልጊዜ ያለ ማቋረጥ ልናከናውነው ይገባል:: በርግጥም ጸሎት እስትንፋስ ነው::

# ምዕራፍ ሁለት

## ጸሎት መታየት ነው

*«... ስንጸልይ የእኛ መልክ በእግዚአብሔር ዓይን ውስጥ የእግዚአብሔርም መልክ በእኛ ዓይን ውስጥ ይሳላል።»*

የቀደሙት አባቶች ስለ ጸሎት ከሰጡት ትርጉም ሁለተኛው *«ጸሎት ለእግዚአብሐር መታየት ነው»* የሚለው አስደናቂ ትርጉም ነው። እነዚህ አባቶች የጸሎት ሕይወት ስለ ነበራቸው ለጸሎት የሰጡት ትርጉም የጸሎትን ምንነት ያብራራል። የሥነ መለኮት ምሁር ስለ ጸሎት ሊናገር አይችልም። ምክንያቱም ጸሎት ልምምድ እንጂ ፍልስፍና ስላልሆነ ነው። ጸሎት ሁሉን ለሚያውቅ፣ ሁሉን ለሚያይ፣ ልብና ኩላሊትን ለሚመረምር፣ ኃላፊያትንና መጻያትን ለሚያውቅ ለእግዚአብሔር መገለጽ ማለት ነው።

ኃጢአታችንን፣ ድካማችንን፣ ከአቅማችን በላይ የሆነውን ነገር ለእግዚአብሔር መንገር ይገባናል። ተሸንፈን እንዳልተሸነፈ የምንግደረደረው ለሰው ነው። ለሚረዳንና በድካማችን ለማይገረመው ጌታ ግልጽ መሆን ይገባናል። ሁለንተናችንን ለእግዚአብሔር ስናጋልጥ እግዚአብሔር ደስ ይለዋል። ቃሉ፦ *«እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው»* ይላል (ሮሜ. 12፥1)። መሥዋዕት በካህኑ ፊት የተራቀተ ነው። ቆዳው ይገፈፋል፣ የሆድ ዕቃው ይከፈታል፣ ልብና ኩላሊቱ አንጀትና ሳንባው ሳይቀር ይታያል። ራስን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብም ልክ እንደ መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር ፍጹም መታየት ነው። እግዚአብሔር ድካማችንን ቢያውቀውም እንድንገልጽለት ይፈልጋል።

ለሰዎች የማንነግረው በውስጣችን ሆኖ የሚኖር ብዙ የኑሮ ምሥጢር አለን። ብዙዎቻችን ሰው የኑሮአችንን ምሥጢር ሰምቶ



ዳግም አብሮን የሚቆም አይመስለንም። እንደ ሐረግ የተቀጣጠሉ እንደ ሰንሰለት የተያያዙ የሕይወት ትግሎች አሉብን። አንዱን ልክ እንደ ጨረስን ተረኛው ይቀጥላል። ለራሱ ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እንኳ የምናፍርባቸው ብዙ ኃጢአቶች በደጃችን ላይ ዛሬም እንዳደቡ ናቸው። ትዳራችን በባሕር ላይ እንዳለች መርከብ ወይ ማዕበል ወይ የነፋስ ሽውታ አያጣውም። አሞኛል ማለት እስኪያሳፍረን የበሽታ ዘመድ ሆነን ሊሆን ይችላል። የነፍስ ማደሪያ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን የሥጋ አደባባይ ሆናብን ተጨንቀናል። እነዚህንና በቃላት ለመግለጥ የማንችላቸውን ብዙ ጉድለቶች በዕለታዊው ኑሮአችን እያስተናገድን እንገኛለን። እነዚህን ሁሉ ግን በጌታ ፊት መግለጥ ወይም መጸለይ ይገባናል። ጸሎት ለእግዚአብሔር መታየት ነውና።

ማንም ሰው ለሐኪሙ የላይና የውስጥ አካሉን ለማሳየት አያፍርም። መፍትሔ አገኛለሁ ብሎ ስለሚያስብ ሐኪሙ ሁን እንዳለው ይሆናል። ምንም ሳያስቀር የሚያደርገውንና የሚሰማውን ይገልጣል። ሐኪሙም እየሰማ ያለውን በሽታ አያደንቅም፣ አይታዘብም፣ ምሥጢር ጠባቂም ነው። በሽተኛውም በሽታውን ነግሮት ሳይፈጽም መፍትሔውን መፈለግ ይጀምራል። ትልቁ የነፍስ ሐኪማችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በመራራት የሕይወታችንን ጥዝጣዜ የሚሰማን እርሱ ብቻ ነው። መስማት ብቻ ሳይሆን ይሰማዋል። ማድመጥ ብቻ ሳይሆን ይረዳናል። ድካማችን አይገርመውም፤ አይታዘበንም፤ ለእርሱ የነገርነውንም ምሥጢር ሌላ ጋ አናገኘውም። ለጥያቄዎቻችንም ሙሉ መልስ አለው። የዕብራውያን መልእክት ፀሐፊ *«እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ። ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም። እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ»* (ዕብ. 4፥1፥16) ይላል።

የሰው ልጅ የሚያልፍበትን የሕይወት ሂደት ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ አልፎበታል። ረሀብን፣ ስደትን፣ ችግርን፣ ውጣ ውረድን፣ መጠላትን፣ መነቀፍን፣ መዋረድን፣ ሐሰተኛ ፍርድን፣ ... በሕይወቱ አስተናግዷል። «እግዚአብሔር የማልፍበትን የሕይወት ጎዳና ቢያውቅ ኖሮ ይራራልኝ ነበር» ማለት አንችልም። እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሰው የሚደርስበትን ሁሉ ቀምሷል። ስለዚህ የምናልፍበትን የሕይወት ሂደት ያውቀዋል ደግሞም

ይራራልናል፡፡ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ዙፋን የፍርድ ዙፋን ነበር፡፡ ከአዳም የተወለዱ ሁሉ የአባት ዕዳ በልጅ አልፎባቸው ኃጢአተኞች ሆነው በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር ወድቀው ነበር፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአትን ዋጋ በመክፈሉ በእርሱ አምነው የሚመጡትን ለመቀበል እግዚአብሔር የምሕረትን ዙፋን ዘርግቷል፡፡ መከራን፣ የሕይወትን ቁስለት፣ ድካምን ሁሉ የሚያሸንፍ ኃይል አለ፡፡ ደክሞ ያበረታን፣ ሞቶ ያዳነን ጌታ በዙፋኑ ተቀምጧል፡፡ ሊረዳንም ዘወትር ትጉህ ነው፡፡ ስለዚህ በችግሮቻችን ማጉረምረም፣ ማዘንና መተከዝ አይገባንም፡፡ ወደ ረድኤት መንበሩ ቀርበን ጸጋንና ኃይልን መቀበል ይገባናል፡፡ በነቢይነቱ ሊያጽናናን፣ በካህንነቱ ኃጢአታችንን ይቅር ሊል፣ በንጉሥነቱ ኃይልን ሊሰጠን ዛሬም ሕያው ነው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው የእግዚአብሔርን የኃይልና የፈጣሪነት ሥልጣኑን ለመግለጥ አይደለም፡፡ ይህ ከጥንት ጀምሮ ታውቆ ይኖራል፡፡ ዛሬም እንኳ ከሃድያን የሆኑ ፈላስፎች አንድ ኃይል አለ ይላሉ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ፍጥረቱን ሁሉ ስለሚያፈቅረው አንድ አባት ሊናገር ነው፡፡ መናገር ብቻ ሳይሆን ፍቅሩን እስከ ሞት ሊገልጥልንም ነው፡፡ ያ አባት ሰማያዊ አባት በመሆኑ ከምድራዊ አባት ይለያል፡፡ ጸሎት ማለትም አፍቃሪ ከሆነው ከሰማያዊ አባት ጋር መነጋገር ነው፡፡ ይህን የሚገልጹ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ጸሎትን አስተምሯል፡፡ ያስተማረው ጸሎት *«እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ»* (ማቴ. 6፥9) ያለበት እንጂ ይህን ጸልዩ ያለበት ባለመሆኑ አቡነ ዘበሰማያት የጸሎት ሞዴል እንደሆነ እንረዳለን፡፡ አንድ ጸሎት ከሚያሟላቸው ነገሮች አንዱም የእግዚአብሔርን ክብሩን ማክበር፣ ባሕርዩን ማወደስ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ክብሩን ከምናከብርበት፣ ባሕርዩን ከምናወድስበት ቋንቋ አንዱ እግዚአብሔርን «አባታችን» ብለን መጥራት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን «አምላካችን ሆይ፣ ፈጣሪያችን ሆይ» ሳይሆን «አባታችን ሆይ» ብለን እንድንጠራው አዝዞናል፡፡ ለምንድነው? ስንል ጸሎት ከቸር አባት ጋር የሚደረግ የፍቅር ውይይት ስለሆነ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ሲጸልዩ ቃላትን ሳይቀር በጣም ይጠነቀቃሉ፡፡ ቃል ቢገድፉ እንደሚቀሰፉ ያስባሉ፡፡ ሕፃኑ ልጅ ግን በአባቱ ፊት ቃላት አይጠነቀቅም፡፡ ያ ማለት አባቱን መድፈር ይችላል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች በዳኛ ፊት እንደ ቆመ ወንጀለኛ ተጠንቅቀው ስለሚጸልዩ ወደ ጣዕመ ጸሎት መድረስ



አልቻሉም፡፡ እግዚአብሔር ግን የሚፈርድብን ሳይሆን የሚናፍቀን አባታችን ነውና በመንፈሳዊ ነጻነት መጸለይ ይገባናል፡፡ ወላጆች የተሰባበረና ያልተስተካከለ የልጆቻቸውን ቋንቋ ሰምተው ይፈጽማሉ፡፡ ሰደጅ ሰው ልጆቹ ምን እንደሚሉ እንኳ ግልጽ አይደለም፡፡ ወላጆች ግን ልጆቻቸው ለማለት የፈለጉትን ያውቃሉ፤ ያደርጋሉም፡፡ እኛም ለእግዚአብሔር ልጆች ነን፡፡ ቃላት ባናዋቅርም እግዚአብሔር ይሰማናል፡፡ ሰምቶም ያደርግልናል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ዋጋ ያለው ከጸሎት ቃል በላይ የጸሎት ልብ፣ ከቀልጣፋ አንደበት በላይ ንጹሕ ኅሊና ነው፡፡ አንድ ሰባኪ የተናገረው ቃል ዘወትር ይታወሰኛል፡- «አንተ አጣመህ ብትጸልይም እግዚአብሔር አቃንቶ ይሰማዋል፡፡»

ጌታችን ለደቀ መዛመርቱ ጸሎትን ሲያስተምር *«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ፥»* (ማቴ. 6፥9) በሉ አለ፡፡ በምድር ላይ አባት ተብለው የሚጠሩ ብዙዎች አሉ፡፡ የእግዚአብሔር አባትነት ግን ልዩ ነው፣ ሰማያዊ ነው፡፡ የእኛን አገር አባቶች ስናስብ እግዚአብሔር አባት ነው የሚለው ትርጉም ያንስብን ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በአገራችን የአባትን ጣዕም የሚያውቁ በጣም ጥቂቶች ስለሆኑ ነው፡፡ አባቶች ቢኖሩ እንኳ የእኛ አገር አባቶች የሚታወቁት በፍቅር ሳይሆን በፍርሃት ነው፡፡ በአገራችን እናትም አባትም የምትሆነው ያችው እናት ናት፡፡ ምናልባት እግዚአብሔር እናት ነው ቢባል ቃሉ ይነካን ይሆናል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከክፉዎቹ ሳይሆን ከደጎቹም ጋር ተወዳድሮ የተለየ አባት ነው፡፡ ለዚህ ነው ጌታችን *«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ»* በሉ ያለው፡፡ እግዚአብሔር ከምድራዊ እናት ይልቅ ቅርብ፣ ከምድራዊ አባት ይልቅ አሳቢ ነው፡፡ ልጆቹን ለመቀበልም እጆቹ ተዘርግተው ይኖራሉ፡፡ ወደ እርሱ በመጡት ላይ ፊቱን የማያጠቍር፣ ደጁን በፍጥረቱ ላይ የማይዘጋ ነው፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ፡- *«አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደ ገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና»* (ሮሜ. 8፥15) ይላል፡፡ እግዚአብሔር አባ አባት ወይም አባዬ አባብዬ ብለን በውድ ፍቅር የምንጠራው አባት ነው፡፡ ደግሞም እርሱ ልዩ አባት ነው፡፡ አባ የሚለው ቃል በዓለም ላይ ያሉ ሕጻናት በተፈጥሮ የሚቀዳጁት ቋንቋ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ስንወለድም እግዚአብሔርን አባ ብለን የመጥራት ነጻነትና ፍቅር እናገኛለን፡፡ ካልተወለድን በቀር እግዚአብሔርን ስሜትን በሚነካ ፍቅር አባት ብለን መጥራት አይሆንልንም፡፡ የዳግመኛ ልደት አንዱ ጸጋ እግዚአብሔርን አባት ብሎ መጥራትና መቅረብ ነው፡፡ «አባ» «አሜን» «ሃሌ ሉያ» የሚሉት ቃላት ዓለም አቀፋዊ ቃላት ናቸው፡፡ እነዚህ

ቃላት ጸሎትን የሚያመለክቱ በመሆናቸው ጸሎት የሰው ዘር ፍላጎት መሆኑን እንረዳለን:: ይልቁንም «አባ» የሚለው ቃል የተፈጥሮ ቋንቋ በመሆኑ ጸሎት ተፈጥሮአዊ ፍላጎት መሆኑን ያስረዳናል::

እግዚአብሔርን አባ የምንለው በክርስቶስ አይተነው ነው:: ለእግዚአብሔር ያለን ፍርሃት ዛሬ ባሪያ ጌታውን እንደሚፈራው ያለ ፍርሃት ሳይሆን ልጅ አባቱን እንደሚፈራው ያለ የፍቅር ፍርሃት ነው:: በራሱ ላይ በተመሠረተው ፍቅር እግዚአብሔር አባታችን ሆኗል:: እኛም በልጅነት ስሜት ወደ እርሱ መቅረብ ያስፈልገናል::

ልጆችን ስንመለከት በአባታቸው ላይ ያላቸው መደገፍ እጅግ ብዙ ነው:: ለምሳሌ:-

## 1. <u>ቃላትን አይጠነቀቁም</u>

አባቱ ፊት የሚፈልገውን ጽፎ የሚያነብ ልጅ በፍጹም የለም:: አባቴ ስለ ቃላቴ ደካማነት ይታዘበኛል የሚልና ፍርሃት ያሸማቀቀው ልጅ እንዳለ አልሰማንም:: ከዚያ ይልቅ በአባታቸው ጉልበት ላይ ሆነው በፍጹም ነጻነት የሚሹትን የሚናገሩ ልጆች ብዙ ናቸው:: እግዚአብሔር አባታችን ነው:: ድካማችንን፣ ጉድለታችንን፣ ፍቅራችንን፣ ነገራችንን ሁሉ በፍጹም ነጻነት በጸሎት መንገር አለብን እንጂ ቃላት አሳማሪዎች መሆን የለብንም:: ምክንያቱም ጸሎት የፍቅርና የልብ እንጂ የቃላት ቅንብር አይደለምና:: ማንም ልጅ ከአባቴ ጋር በደንብ ለመነጋገር ኮሌጅ መግባት አለብኝ ብሎ አያስብም:: ቢያስብም የልጁ ጤንነት አጠራጣሪ ነው:: እንዲሁም የተማረም ያልተማረም፣ ደካማውም ብርቱውም በአንድነት የሚጠቀምበት መንፈሳዊ ቋንቋ ቢኖር ጸሎት ነውና በቋንቋችን መጸለይ አለብን::

ከአዲስ አበባ ወጣ ብዬ በአንድ ከተማ ላይ ወዳጆቼ ዘንድ ዐርፌ ሳለሁ አንድ እናት መጡ:: እኚህ እናት ችግር ተናጋሪ አድርጓቸዋል:: ደህና ኑሮን ከዚህ በፊት ያዩ እንደ ነበሩ ወዳጆቼ ሲነግሩኝ ቀበል አደረጉና የጎንደር ገበሬ የሚገጥመውን ትልቅ ምሥጢር:-

*«በሳነው ጠግነው ለበስነው አለቀ!*
*ዕድሜ መች ይለቃል ካላጨማለቀ!»* በማለት አወረዱት::

እኔም እናቴ እንዴት ይኖራሉ? ብዬ ጠየቅኋቸው:: እርሳቸውም ደረታቸውን ሰፋ አድርገው የሚኖሩበትን ምሥጢር በኩራት መናገር ጀመሩ:- «ልጅ የለኝም፣ ልጁ መድኃኔዓለም ነው:: ጠዋት 11 ሰዓት



ሲሆን ግድግዳውን እያንኳኳሁ የምበላውን ስጠኝ እለዋለሁ:: ልክ 12 ሰዓት ሲሆን አንዱ በሬን ያንኳኳና የምበላውን ሰጥቶኝ ይሄዳል:: እኔ እንድበላ ስንቱን እንቅልፍ ይነሣዋል:: ከአዲስ አበባ ቀርቶ ከአውሮፓ አምጥቶ በሬ ላይ ያቆመዋል:: የምኖረው እንዲህ ነው» አሉኝ:: የምሰብከው እኔ የእርሳቸውን ያህል በመድኃኔዓለም ስላልኮራሁበት ራሴን ታዘብኩት:: የእኚህ እናት ጸሎት እንደ ሕጻን ልጅ በጠዋት ተነሥቶ ግድግዳ እየደበደቡ አብላኝ የሚል ነው:: ጸሎት ይህ ነው::

ብዙ ሰዎች «ጸሎት አንችልም እናንተ የምትጸልዩት ጸሎት ግን ያስቀናናል:: እባካችሁ ጽፋችሁ ስጡን» ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች:- «በጣም የምወደው የዘመኔ ወዳጅ አለኝ:: እናንተ ለወዳጃችሁ የጻፋችሁትን ደብዳቤ ኮፒውን ስጡኝና ገልብጬ ለወዳጄ ላንብብለት» እያሉ ነው ያሉት:: እነርሱ ገልብጠው ለማንበብ ባይሳቀቁም እንኳ የእነርሱ ያለ መሆኑን የሚያውቀው ያ ወዳጅ የእናንተ ኮልታፋ ቃላችሁ ይጥመኝ ነበር ማለቱ አይቀርም:: ወላጆች የልጆቻቸው ኮልታፋ ቃል እንደሚጣፍጣቸው እግዚአብሔርም ኮልታፋው ቃላችን ይጣፍጠዋል:: ስለዚህ ጸሎት የቃላት ቅንብር ጉዳይ አይደለም::

## 2. <u>ልጆች በወላጆቻቸው ይታመናሉ</u>

ልጆች አባታቸው ምንም እንደማይሳነው ያምናሉ:: ሞተር ሳይክል መግዛት የማይችለውን አባታቸውን አውሮፕላን ግዛልን ይሉታል:: አባታቸው ሁሉን ቻይ እንደሆነ ያምናሉ:: አንድ ሕጻን ልጅ ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት ልቅሶ ቤት ውስጥ አባቱ ሲመጣ ከሩቅ አይቶ «እናንተ አባዬ መጣ ተነሡለት» አለ:: እዚያ የነበሩትም ሰዎች «ደሞ ላንተ አባት ነው የምንነሣው?» ብለው የአገራችንን ክፉ ቃል ለዚያ ሕጻን አቀመሱት:: ለካ አባትዬው ምስኪንና ሁሉም ሰው የሚልከው ደሃ ነበር:: ለሕጻኑ ግን አባቱ የትልቆች ትልቅ ደግሞም ንጉሥ ነበረ:: የእርሱ አባት ከሁሉ በላይ (ራስ) ነው::

እንዲሁም በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኘው ምእመን እግዚአብሔር ሁሉን ለማድረግ ቻይ እንደሆነ፣ አቅቶት የሚተወው ምንም ነገር እንደሌለ ማመን ይገባዋል:: ኢዮብ:- *«ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ»* (42፥2) እንዳለ::

ልጆች በአባታቸው የሚታመኑት በሁሉም ነገር ነው:: ለትልቁም ሆነ ለትንሹም ነገር በእግዚአብሔር ይታመናሉ:: ለእርሳስ

ሳይቀር የሚታመኑት በአባታቸው ነው:: እኛም የልጅነት መንፈስ ሲያድርብን በሁሉም ነገር በእግዚአብሔር እንታመናለን:: ደሞዛችን የሚችለውን ጉዳይ ለራሳችን፣ የሚከብደንን ለእግዚአብሔር እናቀርብም:: ስለ ሁሉም ነገር በእርሱ እንታመናለን::

ልጆች ያለ አባታቸው ፈቃድ አይንቀሳቀሱም:: ክፉ ላልሆነው የኳስ ጨዋታ እንኳ ያስፈቅዳሉ:: በሁሉም ነገር ይሁንታ ካላገኙ ድፍረት አይለማቸውም:: እንዲሁም ምእመን ስለ በጎ ነገር ሳይቀር መጸለይ ያስፈልገዋል::

በመጀመሪያ:- ተጠሪ ያለው ሕይወት ስለሚኖር ስለ ሁሉም ነገር ለእግዚአብሔር ማሳወቅ አለበት::

ሁለተኛ:- መልካም ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለምና በጸሎት ዋስትና መጠየቅ ያስፈልገዋል::

ሦስተኛ:- ሰው የአሁኑን እንጂ ቀጣዩን አያውቅምና በእግዚአብሔር ዓይን ነገን በጸሎት ማየት አለበት::

## 3. ራቁትነታቸው አያሳፍራቸውም

ልጆች በአባታቸው ፊት መራቆታቸው አያሳፍራቸውም:: ከቆሸሹም አባታቸው እንዲያጥባቸው ሙሉ ፈቃድ አላቸው:: እንዲሁም ምእመናን ልጅነት ሲለማቸው ድካማቸውንና ኃጢአታቸውን ለእግዚአብሔር ይገልጡለታል:: እርሱም በምሕረቱና በልጁ ደም አጥቦ በጸጋውና በልጁ ጽድቅ ይሸፍናቸዋል::

አንድ ሰው ስለ ጸሎት እያስተማርኩት ሳለሁ እንዴት እንደሚጸልይ ጠየቅሁት:: እርሱም አስደናቂ ነገር ነገረኝ:- «ወደ መኝታ ክፍሌ ገብቼ ልብሴን ሙሉ በሙሉ አወልቅና ራቁቴን ቆሜ ጌታ ሆይ ሉፍና ከረባት ለሰው ነው፣ አንተ ግን የምታውቀኝ እንደዚህ ነው:: እባክህ ሰው አድርገኝ ብዬ ነው የምጸልየው» አለኝ:: አዎ ጸሎት ለእግዚአብሔር መታየት ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ወዳጅነት የሚጠነክረው ግልጽነታችን በጨመረ ቍጥር ነው::

በሕንድ አገር አንድ ሰባኪ ለባልንጀራው «እንተ ዛሬ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን እኮ አየሁት» ይለዋል:: ያም ሰው ተደንቆ «አየኸው?» ይለዋል:: አዎን «አየሁት» አለው:: ባልንጀራውም «ታዲያ ምን



አልከው?» አለው:: ሰባኪውም «ካየኝ ምን እለዋለሁ? ሁለመናዬን እይቶታል» አለው ይባላል:: እኛ ብንሆን በዚህች ሰዓት ክርስቶስ ቢታየን የምንጠይቀውን ዝርዝር እናስብ ነበር:: እርሱ ግን ሲያየን ሁለመናችንን ያየዋል:: እርሱ ሲያይ የቆሰለውን ጀርባ፣ የተሰበረውን አጥንት፣ የደከመውን ጉልበት፣ ጭል ጭል የሚለውን ሙጣጭ ትንፋሽ፣ በፍርሃት ልፍረስ ልፍረስ የሚለውን ሰውነት . . . ያየዋል:: መፍትሔውንም ይሰጠናል::

## 4. በማለዳ ይገናኛሉ

ልጆች ከእንቅልፋቸው ሲነሡ ቶሎ የሚታያቸው ነገር ከአባታቸው ጋር መገናኘት ነው:: አባታቸው በደጅ ሲያመሽም የአቅማቸውን ያህል ይጠብቁታል:: አቅማቸው ካልተረታ በቀር አይተኙም:: ማታም ተገናኝተው መተኛት ይፈልጋሉ:: እንዲሁም ምእመናን ከእግዚአብሔር ጋር በማለዳና በማታ በልዩ ሁኔታ መገናኘት ይጠበቅባቸዋል:: ሕጻናት አያገኙትም እንጂ አባታቸውን ቀኑን በሙሉ ቢያገኙት ይመኛሉ:: እግዚአብሔር ግን ለፈለጉት ሁሉ የሚገኝ፣ ደጆቹ የማይዘጉ፣ ቀጠሮ የማይፈልግ አባት ነውና በምቹ ጊዜ ሁሉ በጸሎት መገናኘት ይገባናል:: ነቢዩ ዳዊት:- *«ስለዚህ ቅዱስ ሁሉ በምቹ ጊዜ ወደ አንተ ይለምናል፤ ብዙ የጥፋት ውኃም ወደ እርሱ አይቀርብም»* (መዝ. 31፥6) ብሏል::

## 5. ምክንያቱ ፍቅር ነው

ልጆች ከአባታቸው ጋር የሚገናኙት ጉድለት ሲኖር ብቻ አይደለም:: የግንኙነታቸው መሠረቱ ፍቅር ነው:: ጉድለት ባይኖርም ይገናኛሉ:: ብዙ ሰዎች ችግር ከሌለ ጸሎት ያለ አይመስላቸውም:: ጸሎት ለእነርሱ የእሳት አደጋና የቀይ መስቀል ስልክ ቍጥር ነው:: የአደጋ ነፃ መስመሮች ከአደጋ ቀን ውጭ አይደወልባቸውም:: ትዝም አይሉንም:: ወዳጃችንን ግን በወትሮም እንደውልለታለን:: የሚያገናኘን ችግር ብቻ ሳይሆን ፍቅርም ነውና:: እግዚአብሔር አባታችን ነው:: ስለዚህ ዘወትር በፍቅር ልናወራው ይገባናል::

አዎ ሕፃን ልጅ በአባቱ ፊት ሁለመናው የተገለጠ ነው:: ዕድሜው፣ ታሪኩ፣ መልኩ፣ ቋንቋው፣ ጠባዩ፣ አልቃሻነቱ፣ ሳቁ፣ ጥያቄው፣ ... በአባቱ ፊት የተገለጠ ነው:: ፍጡር ለፍጡር እንዲህ ከሆነ እኛማ ለእግዚአብሔር እንዴት መራቆት ይገባናል? ጸሎት ለእግዚአብሔር መታየት ነው::

አንድ አገልጋይ ሲሰብክ ድምፁ በነፍሴ ውስጥ እስከ ዛሬ አለ:- *«ጸሎት ማለት መተያየት ነው:: ከፊታችን ካለው ሰው ጋር ስንተያይ*

*የእኛ መልክ በእርሱ ዓይን ውስጥ የእርሱም መልክ በእኛ ዓይን ውስጥ ይቀረጻል። እንዲሁም ስንጸልይ የእኛ መልክ በእግዚአብሔር ዓይን ውስጥ የእግዚአብሔርም መልክ በእኛ ዓይን ውስጥ ይሳላል። የእግዚአብሔር መልክ ተስሎብናልና ሰይጣን በፊታችን ለመቆም ጉልበት የለውም።»*



# ምዕራፍ ሦስት

## ጸሎት ንግግር ነው

*«ያገኙት ዘንድ አይሄዱም፤ በፈለጉትም ጊዜ አይታጣም፤ በያዙትም ጊዜ አይዳሰስም፤ ከሕሊና ልዩ ነው» (ሠለስቱ ምእት)።*

*«ጸሎት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለች ንግግር ናት።»* ጥንታውያን አባቶች ለጸሎት ከሰጡት አስደናቂ ትርጉም ሦስተኛው ይህ ነው። ህልውናው በዙሪያችን አስተማማኝ ከሆነውና ከሚናገር አምላክ ጋር መነጋገር ጸሎት ይባላል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ታላቅ ስም ትርጓሜ ሲናገር «ያለና የሚኖር» ይለዋል። ያለና የሚኖር ተብሎ የተተረጎመው ስም «ያህዌ» የሚለው ስመ አምላክ ነው (ዘፀ. 3፥14)። እግዚአብሔር ያለ ብቻ ሳይሆን የሚኖርም ነው። ብዙ ያሉ ነገሮች አሉ። ነገር ግን የሚኖሩ ላይሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፦ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያለ ቋጥኝ አለ። ነገር ግን የሚኖር አይደለም። እግዚአብሔር ግን ያለ ብቻ ሳይሆን በሕያውነትም የሚኖር ነው። ከዚህ አምላክ ጋር ማውጋት ጸሎት ይባላል።

ብዙ ሰዎች ጸሎትን የሚያስቡት ችግራቸውን የሚናገሩበት፣ ሁልጊዜ ጥቅም የሚፈልጉበት ነፃ መስመር አድርገው ነው። ስለዚህ የሚፈልጉትን ከተናገሩ በኋላ ፈጥነው ይሮጣሉ። ጸሎት ግን የአንድ ወገን ወሬ ወይም ሪፖርት አይደለም። በአባትና በልጅ መካከል የሚደረግ የፍቅር ውይይት ነው። ከምንወደው ወዳጃችን ጋር የምንወያየው በአጀንዳ አይደለም። የእኛ የሆነውን ጉዳይና ውሎ ሁሉ የመስማት መብት እንዳለው ስለሚሰማን ሁሉን እንወያያለን። ስለ ትንንሽ ነገሮች ስንነጋገር እንደ ትልቅ ስብሰባ በራችንን ዘግተን ነው። መንግሥታት ሲሰበሰቡ መንገድ ያዘጋሉ። ወዳጆችም ሲወያዩ ደጃቸውን ይዘጋሉ። ስዋራ ስፍራ ይፈልጋሉ። የማይነገር ነገር የለም። ሁሉም ይነገራል። ሁሉም የጋራ ጉዳይ ይሆናል። ትንሹ ጉዳይ እንደ ትልቅ ጉዳይ ይታያል። ጸሎትም ልክ እንደዚሁ ቋሚ ወዳጅ ታላቅ አባት ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የፍቅር ውይይት ነው። ስለዚህ ሙሉ ሕይወታችንን፣ የዛሬውን ውሎአችንን፣ ያደከሙንን

ጉዳዮች፣ ያዛሉንን ነገሮች፣ ያስቀየሙንን ሰዎች፣ መሸከም ያቃተንን ኮተቶች ሁሉ ከጌታ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ሲረዳኝ የኪሴን ሳንቲም አውጥቼ ይህን ያህል ተጠቅሜ ይህን ያህል ቀርቶኛል፤ ይህን ያህል እፈልጋለሁ እላለሁ። ግልጽነት ወደ ጸሎት ጥልቀትና በረከት ሲያደርሰኝ አይቻለሁ። ሳልጸልይ ስለ ገዛኋቸው ልብሶች ከልቤ አዝናለሁ። የምፈልገውን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ባገኘው እንኳ ደስታ እንደ ሌለው ተረድቻለሁ።

አንዳንድ ሰዎች እየደወሉ «ስለዚህ ነገር መጸለይ ተገቢ ነው ወይ?» ብለው ይጠይቁኛል። ይልቁንም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች ስለ ሥጋዊ ነገር በእግዚአብሔር ፊት መጸለይ ደረጃውን ያልጠበቀ አድርገው ያስባሉ። ሁሉን ነገር ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ይገባል። በጸሎት ሕይወት እያደግን ስንመጣም ፈቃዱን እየለየን መጠየቅ እንጀምራለን። ለምሳሌ:- በኪሳችን ገንዘብ ይዘን ወደ ገበያ ስንወጣ መልካም ዕቃን እንዲገዛልን እግዚአብሔርን መጠየቅ እንጀምራለን። ጸሎት የምናደርገው ስለማንችለው ነገር ብቻ ሳይሆን ልናደርገው ስለምንችለውም ነገር ለእግዚአብሔር እናሳውቃለን። አንድ ሰው ብዕር ለመግዛት ይጸልይ ነበር። ዕድሜው ከዐርባ በላይ ቢሆንም «ጌታ ሆይ ለእኔ ለልጅህ ብዕር እንድትገዛልኝ እለምንሃለሁ» ይል ነበር። ሕፃን ልጅ ሁሉንም እንደሚጠይቅ እኛም ስለ ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ይገባናል። ያለ ጸሎት የምንጨብጠው ነገር ቢጨበጥም አያረካም።

ጸሎት የእኛን ከፍተኛና ዝቅተኛ ጉዳዮች ለእግዚአብሔር የምናቀርብበት ሲሆን እግዚአብሔርም ሳይታዘበን ይሰማናል። የያዕቆብ መልእክት ስለ ጸሎት ከሚናገራቸው አስደናቂ ምንባቦች አንዱን በዚህ ክፍል ላይ ማንሣት ያስፈልገናል:- *«ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጐድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል»* (1፥5)።

የጥበብ ጉድለት ምንድነው? ከማለታችን በፊት ጥበብ ምንድነው? ስንል እውቀታችንን በቦታው በቦታው የምናውልበት ችሎታ ነው። የብዙ አዋቂዎች ችግር ጥበብ ነው። ስለዚህ እውቀታቸው የጋን ውስጥ መብራት ሆኖ ይቀራል ወይም ተሳዳቢ ያደርጋቸዋል። የብዙ ባለጠጎች ችግራቸው ጥበብ ነው። ገንዘባቸውን ለአዝማሪ ለአወዳሽ በትነው ያለ ውለታ ይጨርሱታል። የብዙ ኃያላን ችግር ጥበብ ነው ጉልበታቸውን የወደቀውን ለማንሣት



አይጠቀሙበትም። ስጥቶአቸው ሳያውቁበት ቀርተው የሚያለቅሱ ሰዎች ዓለምን ሞልተዋታል። «ገንዘብ የሚመጣው በሃያ ዓመት፣ ልብ የሚመጣው በዐርባ ዓመት» እንዲሉ።

በዐፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት መልከአ ክርስቶስ የተባለ ሽፍታ ተነሣ (መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ)። ግብረ አበሮቹን አስተባብሮ ዐፄ ፋሲልን ቢገጥማቸው የዐፄ ፋሲል ጦር ተፈታ። እርሳቸውም ዘውዳቸውን ይዘው ሸሹ። መልከአ ክርስቶስ የተባለውም ሽፍታ ከቤተ መንግሥት ገብቶ ቢመለከት ትልቅ መቅረዝ ዐይቶ ዘውድ ነው ብሎ በእናቱ ላይ ደፍቶ ወደ አደባባይ ወጣ። ያላወቀ አደነቀው ያወቀም «ንገሥ ያላለው ቢያነግሡትም አነጋገሡን አያውቅበትም» ብሎ ሳቀበት።

የመጽሐፉ ቃል ጥልቅ ነው:- *«ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጐድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል»* (ያዕ. 1፥5) ይላል። እውቀት፣ ገንዘብ፣ ሥልጣን፣ ወዳጅ፣ ... ስጦታን አጠቃቀሙን አላውቅበት ብለን እንዳናበላሽ ጥበብን ከጠቢባን ጠቢብ ከእግዚአብሔር መለመን አለብን። ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ደገኛ ባሕርይ ሲገልጽ *«ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን»* አለ። ባሕርዩ:-

1. አይነቀፍም፣
2. እኛን ያያል፣
3. ለሁሉም ቸር ነው፣
4. ተለማኝ ጌታ ነው።

## 1. <u>አይነቅፍም</u>

ሰዎች ቢሰጡም የሚሰጡት ነቅፈውን ነው። «የምትረባ ሰው አይደለህም፣ አጥፍው አሉ፣ ራስህን መቻል አለብህ፣ እኔ የሌለሁ ቀን እንዴት ልትሆን ነው? ...» እያሉ ይሰጣሉ። ለለማኝ ለመስጠት እንኳ ዘርና ሃይማኖት ይለያሉ። በዘር ይሳደባሉ። 0.5 ሣንቲም ለመስጠት የ5 ሺህ ብር ንግግር ይናገራሉ። ብዙ ደጎች የሚወቀሱትም:- «ደግ ነው፣ እጁን ቆርጦ ያበላል ግን ምን ዋጋ አለው በአፉ ያበላሸዋል» እየተባሉ ነው። የሰው ደግነት «ግን» የሚል አፍራሽ ቃል አያጣውም። ሰጠሁ ብሎ በመናገርም የሰጦታውን ክብር ዝቅ የሚያደርገው ብዙ ነው። ስጦታ ተቀባዩ ሲያወራው እንጂ ሰጪ ሲያወራው ዋጋው

ይቀንሳል:: እግዚአብሔር ግን *«ሳይነቅፍ»* የሚሰጥ ጌታ ነው:: «በዚህ ዕድሜህ እንዴት ጥበብ ጎደለህ? ይህ ሁሉ ትምህርትህ ይህን ካላሳወቀህ ምን ዓይነት ፍጡር ነህ?» በፍጹም አይለንም:: እንዲህ ያለውን ጥበብ ባለ መለመን ብዙ አዋቂዎች እብድ ሆኑ፣ ብዙ ሥልጣን መባለጊያ ሆነ፣ ብዙ ትዳር ተፈታ፣ ብዙ አገር ተላለቀ:: ይህን ጥበብ ለመቀበል ግን ያለው ቀላል መንገድ መጸለይ ነው::

## 2. እኛን ያያል

ስጦታ ስንሰጥ ወይ ሰውዬውን ወይ ስጦታውን እናያለን:: ሰውዬውን ስናይ ስጦታው ያንስብናል:: ስጦታውን ስናይ ደግሞ ሰውዬው ያንስብናል:: ስጦታው ሲያንስብን ገና ራሳችንን መስጠት እንደሚገባን እንረዳለን:: ሰውዬው ሲያንስብን ደግሞ በልባችን ንቀትና የባለውለታነት መንፈስ ይሰማናል:: ይህ ዓይነት ስጦታ እንደ መሥዋዕት የሆነ ፍጹም ስጦታ ሳይሆን የጫፉን ገመድ ይዘን የምንለቀው በመሆኑ ልግስና ይጎድለዋል:: የያዕቆብ መልእክት ግን ስለ እግዚአብሔር ስጦታ ሲናገር፦ *«...ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን »* (ያዕ. 1፥5) ይላል:: *«በልግስና»* የሚለው ቃል ትርጉሙ ጥልቅ ነው:: እግዚአብሔር ስጦታን ሲሰጠን የሚያየው እኛን እንጂ ስጦታውን አይደለም:: እርሱ ለጋስ ሰጪ ነው::

## 3. ለሁሉም ቸር ነው

ሰው እንዲሁ አይሰጥም:: ስጦታው ምን አገኛለሁ? ብሎ የሚያገናዝብ ነው:: የሰው ዓለም መርሁም «ሰጥቶ መቀበል ነው::» ስለዚህ ሰው «ለሁሉ» መስጠት አይሆንለትም:: እግዚአብሔር ግን «ለሁሉ» የሚሰጥ ነው:: ያዕቆብ *«...ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን»* (ያዕ. 1፥5) ይላል:: እግዚአብሔር በስጦታው አድልኦ የለበትም:: ለለመነው ሁሉ ቸር ነው:: ዘርን፣ ቀለምን፣ የትምህርትና የኑሮ ደረጃን አያይም:: እርሱ በብሩህ ፊት፣ በሰፊ እጅ ይሰጣል:: የእንስሳትን ጩኸት ሳይቀር ይሰማል:: የዱዳዎችንና የሕፃናትን ልመና ያደምጣል:: እግዚአብሔር የሕጻኑን የእስማኤልን ድምፅ እንደ ሰማ ተጽፎአል (ዘፍ. 21፥17)::

እግዚአብሔር ሁሉን ከሰማ እኛም ለሁሉም የመጸለይ ግዴታ አለብን:: አንድ ወዳጄ «በጸሎት አድልኦ የለም:: ለተጨነቀ ሁሉ ጸልዩ» በማለት ተናገረኝ:: ይህ ሰው ያለሁበት ድረስ የመጣው ስለ እንስሳት እንድጸልይ አደራ ሊለኝ ነው:: ሰዎች ለገዛ ጥቅማቸው ብለው



አስብተዋቸው መሄድ ባለመቻላቸው ስለሚገረፉ በሬዎች፣ ከነቁስላቸው ሸክም ስለሚጫንባቸው አህዮችና ፈረሶች እያለቀሰ ሲነግረኝ ደነገጥኩ:: ከአጠገቤ ሲለየኝ፦ «በጸሎት አድልኦ የለም ለተጨነቀ ሁሉ ጸልዩ:: እንስሳት በሰው ክፋት ተጨንቀዋል» አለኝ:: እኔም ስለ እንስሳት መጸለይ ጀመርኩ:: እግዚአብሔር የእነዚህም እንስሳት ታዳጊ ነው:: *«... በዚያ ላይ መርከቦች ይሄዳሉ፥ በዚያም ላይ የፈጠርኸው ዘንዶ ይጫወትበታል:: ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸው ዘንድ እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ»* (መዝ. 103፥10-28)::

## 4. ተለማኝ ጌታ ነው

በአገራችን ገበሬ ሳይቀር ሥነ መለኮት አዋቂ ነው:: በአጭር ቃል ብዙ ምስጋና ለእግዚአብሔር ማቅረብ ያውቅበታል:: «ሰማይን ከነግሡ ምድርን ከነልብሱ የፈጠረ ጌታ ያውቃል» ይላል:: ይህን ምስጋና መፍታት ብንጀምር ቀኑ ይመሻል:: ገበሬው ግን በአጭሩ ያመሰግናል:: ይህ ብቻ አይደለም «የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ ጌታ ይመስገን» ይላል:: ያዕቆብም *«...ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን»* (ያዕ. 1፥5) ይላል::

«ይለምን» የሚለው ቃል ድንቅ ነው:: በሰው ዓለም ላይ እንዳንዶች ሀብት አላቸው ግን ለመስጠት ፈቃዱ የላቸውም:: ሌሎች ደግሞ ደጎች ናቸው ግን የሚሰጡት የላቸውም:: እግዚአብሔር ግን ቻይም ለጋስም ነው:: ስለዚህ እርሱን መለመን ይገባናል:: ሰው በባሕርይው ልመናን ይሰለቻል:: ሁልጊዜ የሚለምነውን ሰው ማግኘት አይፈልግም:: በጣም የሚገርመው እግዚአብሔርን ለመለመን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድን ሊለምኑን የሚመጡትን ሰዎች ውስጣችን ይገፋቸዋል:: ለማኝ ሆነን ለማኝ መጥላታችን ትዝብት ነው::

ለምኑኝ ብሎ ያዘዘ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ሰው ቢለምኑት ይሰለቻል፣ ቢሰጥ ያልቅበታል:: ቢለምኑት የማይሰለች፣ ቢሰጥ የማያልቅበት እግዚአብሔር ብቻ ነው:: አንድ አባት ስለ ኢትዮጵያ ሲናገሩ፦ *«ብዙ አዋቂዎች የኢትዮጵያ ችግር አራርቆ አለመውለድ፣ የሕዝብ ቍጥር መጨመር ነው ይሉናል:: ችግራችን ግን ኃጢአታችን ነው የሚል አልሰማንም:: ኢትዮጵያ ገና ከሰው የምትከጅል አገር ናትና መከራዋ ያለቀ አይመስለኝም:: ከእግዚአብሔር ትቶ ከሰው የሚከጅል መከራው ብዙ ነው»* ብለዋል:: ያዕቆብም በሌላ ስፍራ፦ *‹‹አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም››* (ያዕ. 4፥2) እያለ ይወቅሰናል::

ጸሎት ከእንዲህ ያለው ለጋስና ሩኅሩኅ አምላክ ጋር መነጋገር ነው። የጥንት አባቶች ጸሎትን በንግግር የተጠቀሙበት እንዴት ነው? ብለን ስንመረምር የተወሰኑ ነገሮችን እናያለን፦

1. ጽሞና፣
2. ቃሉን ማንበብ፣
3. በመንፈስ መገናኘት።

## 1. ጽሞና

ጽሞና ቀጥተኛ ፍችው ጸጥታ ማለት ነው። ከጸጥታ ግን ልዩ የሚያደርገው አንደኛ፦ እግዚአብሔርን የመጠበቅ ቆይታ ሲሆን ሁለተኛ፦ አካባቢው ሲንጫጫ ቢችል እንኳ በውስጣችን የምናስከብረው ፀጥታ ነው። እግዚአብሔር ሲናገረን ከምንሰማበት መንገድ አንዱ ጽሞና ነው። የራሳችንን ጸሎት ከጨረስን በኋላ ለእግዚአብሔር ጊዜ በመስጠት በፀጥታ እንጠባበቃለን። ጽሞና ግን ቃሉን እንኳ ሲያነሡት ይናፍቃል። እኔም ጽሑፌን አቁሜ መጸለይንና በጸጥታ መሆንን ፈለግሁ። ሁከት በበዛበት፣ ሰው ከራሱ ጋር ላለመገናኘት ተጠንቅቆ በሚኳዝበት በዛሬው ዘመን ጽሞና እስፈላጊ ነው።

ብዙ ምእመናን በቤታቸውም ሆነ በቤተ ክርስቲያን፣ በማኅበርም ሆነ በግል ጸሎታቸውን ካቀረቡ በኋላ ፈጥነው ተነሥተው ወደ ተግባራቸው ይሄዳሉ። እግዚአብሔርን ለመስማት ጊዜ አይሰጡም። እግዚአብሔር በጽሞና ለማቸው በጽሞና ግን እርሱን ለመስማት ፈቃደኞች አይደሉም። በርግጥ ጠማማነት አይደለም። አብዛኛው አለማወቅ ነው። በእንዲህ ያለው የጽሞና ሰዓት ከጌታችን ጋር ስናሳልፍ አእምሮአችን በፀጥታ መባረክ ይጀምራል። ከዚህ ዓለምም ፍጹም ርቀን ከመለኮት ምንጭ አጠገብ መርካት እንችላለን። የቀደሙት አባቶች በጽሞና ለረጅም ሰዓት በጌታ ፊት ይሆናሉ። ጌታ ጽሞናን ይፈልጋል። በጽሞና ስንሆን ይገናኘናል። ያነጋግረናል። ጸሎታችንም ያልጠገበ ሕፃን ከጡት መለየት እንደማይፈልግ ከእግዚአብሔር መለየት እያቃተው ይረዝማል። በጸጥታ ውስጥ እግዚአብሔር ለልባችን ይናገራል። ምሥጢርን ይነግረናል። ዘመኑን ያሳየናል። ተጨማሪ የጸሎት ርእሶችን ይሰጠናል። ጸሎት መነጋገር እንዲሆን የጽሞና ጊዜ ወሳኝ ነው። በጸሎት የበረቱ አባቶች በጽሞና ውስጥ «አዎ ጌታዬ» «እሺ» «እንደ ፈቀድከው» እያሉ ሲያወሩ እንሰማለን። የእግዚአብሔር ድምፅ ለእኛ አይሰማንም። ለእነርሱ ግን



ይሰማቸዋል። ይህ የጽሞና በረከት ነው። ይህን የጌታ ድምፅ ስንለማ መኖራችን ምክንያታዊ ይሆንልናል። በእምነት ድፍረትም መሞላት እንጀምራለን። በጽሞና መነጋገር የተሰጠው ለጥቂት ሰዎች አይደለም። የአማንያን በረከት ነው። የአገራችን ሰዎች «ተወልዶ ብልጫ፣ እንክሶ ሩጫ የለም» እንዲሉ በልጅነት ሁላችንም እኩል ነን። የተጋድሎ ልዩነት ቢኖርም በእግዚአብሔር ፊት የምንሆንበት የልጅነት መብት ግን እኩል ነው። ለዚህም ቀጥሎ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ያረጋግጡልናል። *«ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን?»* (ሚል. 2፥10)። *«ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ፥ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች»* (ያዕ. 5፥17-18)።

## 2. ቃሉን ማንበብ

ጸሎትን ንግግር የሚያደርገው ሁለተኛው ቃሉን ማንበብ ነው። እኛ በጸሎት ለእግዚአብሔር ስንናገር እግዚአብሔር ደግሞ በተጻፈው ቃሉ በኩል ለእኛ ይናገራል። እግዚአብሔር በእርግጠኛ ከሚናገርበት መንገድ አንዱ ቃሉ ነው። *«ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን ለነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዘመናትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን»* (ዕብ. 1፥1-2)። እግዚአብሔር በነቢያት የተናገረው በብሉይ ኪዳን ሲሆን በአዲስ ኪዳን ደግሞ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ተናግሯል። እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና በሕልም፣ በራእይ፣ በምልክት፣ በነቢያት ተናግሯል። ዛሬ ደግሞ በእርግጠኝነት በተጻፈው ቃሉ በኩል ይናገራል። ስለዚህ ጸሎታችንን ካደረግን በኋላ ቃሉን በጽሞና ሆነን ማጥናትና ማሰላሰል ይገባናል። እግዚአብሔር በሕያውነት ይናገረናል። የሚያውል የቃሉን ኃይል እንሞላለን። ለዕለቱ የሚበቃንን መና እንለቅማለን።

## 3. በመንፈስ መገናኘት

የእስራኤል ልጆች ለዘመናት የዘለቀ ክርክር ነበራቸው። አንዱ ጽንፍ አምልኮን ብቁ የሚያደርገው በደብረ ገሪዛን ሲቀርብ ነው ሲል፣ ሌላኛው ጽንፍ ደግሞ አምልኮ በኢየሩሳሌም ካልሆነ አያርግም ብሎ ያምን ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እግዚአብሔር የሚፈልገው አምልኮ በመልክአ ምድር የተወሰነ ሳይሆን በመንፈስና በእውነት የሆነ

አምልኮ መሆኑን ገለጠ፡- *«እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል»* (ዮሐ. 4፥24)። እውነት ሲል የዮሐንስ ወንጌል እውነት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ. 14፥6)። በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምነን የምናቀርበውን አምልኮ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው የሚገልጥ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን አይጠሩም እንጂ እስላሞችም ሆኑ አይሁዶች አንዱን አምላክ እናመልካለን ይላሉ። እግዚአብሔር ግን የሚፈልገው አምልኮ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነቷ ላይ የተመሠረተ አምልኮን ነው (ዮሐ. 4፥22)። እውነት ሲል በሌላ መልኩ የሚገልጠው ከልብ የሆነ አምልኮን ነው።

በመንፈስ ሲልስ ምን ማለት ነው? መንፈስ ለሰው፣ ለመላእክትና ለእግዚአብሔር ይነገራል። ትርጉሙ ግን ይለያያል። ሰው በተፈጥሮ ሥጋ፣ ነፍስና መንፈስ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት ክፍል መንፈስ ይባላል። መላእክት መንፈስ ወይም መናፍስት ሲባሉ ረቂቃን ማለት ሲሆን ይህም ተፈጥሮአቸውንና አካላቸውን ይገልጻል። እግዚአብሔር መንፈስ ነው ሲባል ግን በተለየ ትርጉሙ በጊዜና በቦታ የማይወሰን ማለት ነው። እርሱ በጊዜ የማይገደብ አልፋ ኦሜጋ፣ በቦታ የማይወሰን ምሉዕ በኲለሄ የሆነ አምላክ ነው (መዝ. 89፥1-2፤ 139፥7-12)። እርሱን በመንፈስ ማምለክ ማለት በጊዜና በቦታ ሳንወሰን መጥራት ማለት ነው። በመንፈስ ማምለክ ትርጉሙ ከዚህም ይልቃል።

በጊዜና በቦታ የማይወሰን እግዚአብሔር አሁን በዚህች ሰዓትና በዚህች ቦታ እንዳለ በማሰብ ማምለክ ወይም ክብርን መስጠት፣ ህልውናው እያጠገበን፣ መገኘቱ እየተሰማን፣ በሕሊና ዓይነ-ርግብ እያየነው፣ በውበቱ ተመስጦ እየጠፋን፣ በሰማይ ደጃፍ በዘርፋፋው ቀሚሱ ላይ እየተንከባለልን መጮህ፣ መማለድ በመንፈስ ማምለክ ነው። ጸሎትን ንግግር ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ በመንፈስ መገናኘት ነው። ሠለስቱ ምእት በቅዳሴአቸው፡- *«ያገኙት ዘንድ አይሄዱም፤ በፈለጉትም ጊዜ አይታጣም፤ በያዙትም ጊዜ አይዳሰስም፤ ከሕሊና ልዩ ነው»* ብለዋል (ቅ.ሠለ. ምእት ቍ. 59)።

እውነተኛ አምልኮ በስፍራ ሳይሆን በልብ ዝንባሌ የሚወሰን ነው። በአንበሳ ጉድጓድም፣ በወኅኒም፣ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ እንደነ ኤርምያስ በሸንት ቤትም ሆነው የእግዚአብሔር ሰዎች ጸልየዋል። ከእግዚአብሔር ጋር ጥብቅ የሆነ ግንኙነት ያላቸውና በጸሎት ያደጉ ክርስቲያኖች እንደሚረዱት በመንፈስ ከእግዚአብሔር



ጋር እየተገናኙ ልዩ ምሥጢራትን ይቀበላሉ። ወደ ታላቅ የነፍስ ወደብም ይደርሳሉ። አዎ ጸሎት ንግግር እንዲሆን መንፈሳችን ከመንፈሱ ጋር መተባበር አለበት። ወደ ጣዕመ ጸሎት ለመግባት ጸሎታችን መናገር ብቻ ሳይሆን እኛም እግዚአብሔርን የምንሰማበት ሲሆን ይገባዋል።

# ምዕራፍ አራት

## የጸሎት ኃይል

፬

*«ጸሎት ኃይል አለው። የተቋረጠውን ግንኙነት ያድሳል። በበደለኝነት ስሜት ለሚሰቃየው ዕረፍትና እንቅልፍ ይሰጣል። ሽፍታው ጭምት፣ ሌባው መጸዋች፣ ዘማዊው የንጽሕና ወዳጅ የሚሆነው በጸሎት መንገድ ተጠቅሞ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመቀዳጀት ነው።»*

ዘመኑ የኃይል ዘመን እንደሆነ በተደጋጋሚ እንሰማለን። የሰው ልጅ በታሪክ ሂደቱ ከጉልበት ኃይል ወደ እንስሳት ኃይል፣ ከእንስሳት ኃይል ወደ አቶሚክ ኃይል ተሸጋግሯል። ሰው ግን ገና ያልተጠቀመበት ኃይል አለ። እርሱም ጸሎት ነው። ጣሊያን ሲገባ ወደ አድዋ የዘመቱ አባቶቻችን እንዲህ እያሉ ይጸልዩ ወይም ይናገሩ እንደ ነበር እንሰማለን፦

«ኀብረት ኃይል ውእቱ፣
አንድነት ኃይል ነው፣
አምላክነሰ አምላክ አድኅኖ፣
ሰልፍ የጀግና ነው ድል የጌታ ነው።»

በርግጥም አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው። ሰልፍም የጀግና ሲሆን ድሉ ግን የጌታ ነው። እንዲህ እያሉ በጸሎት የዘመቱት አባቶቻችን በወታደራዊ ሳይንስ፣ በጦር መሣሪያ፣ በዘመናዊ ትጥቅ የማይመጣጠኑ ቢሆኑም ጣሊያንን አሸንፈዋል። የተዋጋው ግን እግዚአብሔር ነበር። በርግጥም ጸሎት ኃይል ነው። ከክፉ ባልንጀሮቹ እንዲለይ ግድ የምንለው አንድ ጎልማሳ «ባልንጀሮቼ በኃይልም በገንዘብም ከእኔ ይበረታሉ እንዴት አትምጡብኝ እላለሁ?» አለን።



«ክርስትና የሥጋ ትግል አይደለም። ጌታዬ ሆይ ከመንገድህ ሊያወጡኝ ነፍሴን ሊያጎሳቍሏት ወደ እኔ የሚመጡትን እግሮች በቀራንዮ በፈሰሰው ደምህ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በተባለው ስምህ እሰርልኝ» ብለህ ጸልይ ተባባልን። በሌላ ጊዜ ይህን ጸሎት እንደ ጸለየ ስንጠይቀው «አዎ» አለንና ግን ጨምሬበታለሁ አለን። ምን ጨመርክበት? ብንለው «የእኔም እግሮች ቅልብልቦች ስለሆኑ ወደ እነርሱ ለመሄድ ሲያስቡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የታሠሩ ይሁኑ» ብዬ ጸልያለሁ አለ። እስከማውቀው ድረስ ከዚያ ቀን በኋላ ባልንጀሮቹ ወደ እርሱ አልመጡም፤ እርሱም አልሄደም። ጸሎት ኃይል ነው። ብዙ የሥጋ ትግሎችን የሚቀንስ፣ መቀያየምን የሚያስወግድ፣ ሳይታይ የሚታይ ሥራ የሚሠራ መሣሪያ ነው።

«የምወደው ወዳጄ ሩቅ አገር ነው፣ ውድ ቤተሰቤ እስር ቤት ነው። እንዴት ልረዳው እችላለሁ?» የምንለው የጸሎትን ኃይል ካልተለማመድን ብቻ ነው። ለእግዚአብሔር የሚርቅ የምድር ጥግ የለም። ዓይኖቹ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ያያሉ፣ እጆቹ ከአድማስ እስከ አድማስ ይዘረጋሉ። ሥልጣኑ ከጥልቅ እስከ አርያም የሰፈነ ነው። ለእግዚአብሔር ሩቅ ዳርቻ፣ ለሥልጣኑም የጊዜ ኀልፈት የለበትም። በገባዖን እንዳደረገው ካሻው ፀሐይን አቁሞ ይሠራል። በሰማርያ እንደሠራው በእፍኝ ደመና አገር ያረካል። ለእስራኤል እንደ ተዋጋው በበትር ባሕር ይከፍላል። ጸሎት ማለት ወዳጃችንን በእግዚአብሔር ሩኅሩኅ ዓይኖች ባለበት ስፍራና ሁኔታ እንዲታይ ማድረግ፣ ስለ ሰው ፍቅር በቀራንዮ በቆሰሉ የኢየሱስ ክርስቶስ እጆች እንዲዳሰስ ማድረግ ነው። በአካል አብሮን የሌለውን ሰው በአካል ከመገኘት በላይ በጸሎት መርዳት ይቻለናል። በወኅኒ ለሚማቅቁ፣ በሩቅ አገር ሆነው በብዙ ችግር ለተጨነቁ ወገኖች የጸለይነው ጸሎት ሲሰምር ቋሚ ምስክሮች ነን። የእግዚአብሔርን መኖር በደንብ ከሚገልጡ ነገሮች አንዱ በምእመናን ጸሎት የሚደረገው ተአምር አንዱ ተጠቃሽ ነው። እግዚአብሔር በቃሉ በየዕለቱ ይናገረናል። በየዕለቱ በጸሎት አማካይነት ይሰማናል። እርሱ ልመናችንን የሚመልሰው የእኛን ጥሩነት ውለታ አድርጎ ሳይሆን *«ለምኑኝ እሰማችኋለሁ»* (ኤር. 29፥12-13) ስላለው ቃሉ ነው።

ከብዙ ሰባኪያን ከብዙ የሃይማኖት አባቶች ይልቅ እናቶቻችን የጸሎትን ኃይል ይጠቀማሉ። እነርሱ ራሳቸው እንደሚናገሩት እግዚአብሔርን በመሀይም ቃላቸው ያዋዩታል። እርሱም ደስ ይለዋል። አንዳንድ ጊዜ ያኮርፉታል። እንደ እኛ ግን አኵርፈው አይቀሩም። እንዳኮረፉትም ሊነግሩት ይሄዳሉ። የሚጸልዩት በምልልስ መልክ ነው። ሲያዋሩትም ይሰሙታል። ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጸልያሉ።

ቤተ ክርስቲያኑን እየዞሩ ያወራሉ። ውዳሴ ከንቱ ፈልገው ነው እንዳንል እንዲህ የሚባል ነገር መኖሩንም አያውቁም። «ዶልዷሌው አምላክ፣ ጥሎ አይጥሌው፣ በየትኛው ጆሮህ ልመናዬን ታፈሰዋለህ» ይሉታል። ድንቅ የሆነ ቃል ነው። አንዳንድ ጊዜ ዝናብ ሲዘንብ ዶል ዶል የሚል ወፍራም ነጠብጣብ አለው። በዚያ ምሳሌ ዶልዷሌው ይሉታል። በረከተ ብዙ ነህ ማለታቸው ነው። ፈጥሮ የማይጥል፣ አስቀምጦ የማይረሳ፣ ለጊዜው የተወ ቢመስልም አለሁ የሚል ጌታ መሆኑን እያስታወሱ «ጥሎ አይጥሌው» ይሉታል። ያንተ ጆሮዎች ጸሎትን አፍስሰው አያውቁም። ሾለዚህ ልመናዬን አትረሳብኝም እያሉ ያሞጋግሱታል። አንዳንዶቹም «እንደምን አደርክ ጌታዬ?» ይሉታል። ሲጨርሱም «በል ደህና ዋል። ይሆን እግሬን ብርድ እየሸመቀቀኝ ነው። ደህና ከሆንኩ ነገ እመጣለሁ። እንዳትቀየመኝ አቅም እያነሰኝ ነው ማታ የማልመጣው። ዓይኔም እምቢ እያለኝ ነው። እስቲ አንተ ታውቃለህ። ሰው ቢሆን ይህን ጊዜ እንዴት በታዘበኝ ነበር። በል ደህና ዋል። ነገ እመጣለሁ» ይሉታል። እግዚአብሔር እንዴት ያዝንላቸው እንዴት ይደሰትባቸው ይሆን? እግዚአብሔር በምሁራን ሲመረር እነዚህ እያየ ደስ ይለዋል። የእኔ አንጀት እንኳ ስጽፈው ተላወሰ። የጌታዬማ እንዴት ይሆን? እነዚህ እናቶች ለምነው አይቀሩም። ሲደረግላቸው ደግሞ ለምስጋና ይመለሳሉ። በዘመናቸው ሁሉ «እርሱ ያደረገልኝ» እያሉ ይተርካሉ። የጸሎትን ኃይል ያልተማሩ የሚመስሉ ሰዎች ሲጠቀሙበት እናያለን።

ከእናቶች ሌላ የጸሎትን ኃይል የሚጠቀሙ ሕፃናት ናቸው። ሕፃናት በባሕርያቸው የእምነት ሰዎች ናቸው። የተነገራቸውን ያምናሉ። ወላጆቻቸው አውሮፕላን እገዛልሃለሁ ቢሏቸው እንኳ ከየት ታመጣለህ? ሳይሉ ያምናሉ። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አለ ሲሏቸው በትክክል ሲያገኙት ነው የሚሄዱት። «ጌታ ሆይ የተገዛልኝን ጫማ እሑድ ቤተ ክርስቲያን ስመጣ አሳይሃለሁ» ይላሉ። እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ምሁራዊ ሁኔታችን ሳይሆን እንደ ሕፃናት የሆነው እምነታችን ነው።

አንድ ወዳጄ ስለ አንድ ሕፃን ልጅ የነገረኝን ታሪክ ዘወትር አስታውሰዋለሁ። ልጁ የጎረቤቱ ልጅ የሚጫወትበትን መኪና አይቶ አባቱን ካልገዛህልኝ ብሎ ያለቅሳል። አባቱም አባብሎ «እኛ ደሃ ነን ሀብታም ስንሆን እገዛልሃለሁ» ይለዋል። ልጁም እሺ ብሎ ዕንባውን ጠረገ። አባትዬውም ወደ ከተማ ሲወጣ ልጁ ያለቀሰበትን መጫወቻ በርካሽ ዋጋ ቻይና ሠርቶ ጎዳናው ላይ አፍስሶት ያገኘዋል። «ወይ ጉድ ልጄን አሳቀቅሁት፣ ለካ እንዲህ ርካሽ ነበር?» ብሎ ገዝቶ ሲገባ ልጁ



በደስታ ዘለለ። በደስታ የዘለለው በመጫወቻው አይደለም። «አባዬ ሀብታም ሆንን አይደለ?» እያለ ነው። አባቱም በልጁ እምነት ተደንቆ ተመሰጠ። ልጁ የተነገረውን አምኗልና ጠዋት ለከሰዓት ሀብታም መሆኑን አመነ። ሕፃናት የእምነት ማንነት አላቸው። እነዚህ ሕፃናት በፍጹም ግልጽነት ስለሚጸልዩ ከፕሮቶኮል ሰዎች ይልቅ የጸሎትን ኃይል ይለማመዳሉ።

አንድ ወዳጄ ሦስት ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች አስቀምጦ በፍርሃት ይናጥ የነበረበትን ዘመን አስታውሶ ዛሬ ያገኘውን ዕረፍት አጫወተኝ። በብዙ የጦር ሜዳዎች የተዋጋ ሰው ቢሆንም ባማረ ቤት ፍርሃት አውሬ ሆኖ ይታየው ነበር። ምን እንደሚያስፈራው አያውቅም። ራሱ ፍርሃት ግን ፍርሃት ሆኖበታል። ብዙ የጦር መሣሪያ ቢኖረውም ፍርሃቱ ሊወገድለት ስላልቻለ ከጎረቤቱ ያሉ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የጦር ሳይንስ ከተማሩ ሰዎች አንዱ የሆኑትን ኮሎኔል ሊያማክራቸው ሄደ። እርሳቸውም በእርጅና ሚስታቸው ከድታቸው ከአንድ ዘበኛ ጋር መኖር፣ በገና እየደረደሩ ስብሐተ እግዚአብሔር ማድረስ ሥራቸው ሆኗል። እግዚአብሔር ትዳርም መሆኑ ተገልጦላቸው ዓለምን ንቀዋል። ይህም ሰው የፍርሃቱ ምሥጢር ሌላ መሣሪያ አለመጨመሩ መስሎት ሲያማክራቸው ሄደ። እርሳቸውም በገና እየደረደሩ በግቢያቸው ተቀምጠዋል። በአባታዊ ሰላምታ ከተቀበሉት በኋላ ጥያቄውን አቀረበላቸው፡- «ኮሎኔል እርስዎ መቼም መሣሪያ የሚያውቁ በብዙ ዐውደ ውጊያ ዝና ያተረፉ ሰው ነዎት። ዛሬ የመጣኹት ደህና መሣሪያ እንዲጠቁሙኝ ነው። ለዋጋው አይጨነቁ፣ እገዛለሁ» አላቸው። እርሳቸውም በገናቸውን ቆም አደረጉና «ልጄ እኔ ከንጉሡ ጊዜ ጀምሮ ብዙ የጦር ትምህርትና የውጊያ ክብር አግኝቻለሁ። ስለዚህ የምጠቁምህ መሣሪያ ልዩ ነው» ሲሉት ዝቅ ብሎ እጅ ነሣ። እርሳቸውም «አየር መቃወሚያን የሚያስንቅ፣ ወፍ የሚያወርድ ድንቅ መሣሪያ እነግርሃለሁ» አሉት። እርሱም እባክዎ ይጠቁሙኝ ብሎ ቆመ። እርሳቸውም «ይህ ድንቅ መሣሪያ ሲጥል እንጂ ሲወረወር የማይታይ ጸሎት ነው» አሉት። ያ ሰው እንደ ነገረኝ ራሴ አነሰብኝ፣ ሕጻን ልጅም የሆንኩ መሰለኝ። እቤቴ ያለውን መሣሪያ ሁሉ ከቤቴ አወጣሁ። አሁን በእግዚአብሔር ደፈርኩ። የጦር መሣሪያዬ ጸሎት ነው አለኝ። ይህ ሰው ከዚያን ጊዜ በኋላ የጸሎትን ጋሻ አነሣ፤ ፍርሃቱም ተወገደለት።

በዓለም ላይ ትልቁ መሣሪያ ጸሎት ነው። ጸሎት ትልቅ መሣሪያ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ገና ያልተጠቀምንበት መሣሪያ ቢኖር ጸሎት ነው። ምእመናንም ሆኑ ቤተ ክርስቲያን ገና በጸሎት ኃይል እንደሚገባ አልተጠቀሙም። በዓለም ላይ የምናየው የሰው ልጅ ሰቆቃ

የክርስቲያኖች ያለ መጸለይ በደል መሆኑን ስንቶቻችን እንደምናስተውል አላውቅም።

የጸሎት ኃይል፡-

- የሚያድን ኃይል ነው።
- ከወዳጃችን ጋር የምንሰለፍበት ነው።
- ለጠላታችን ይቅርታን የምንለምንበት ነው።
- ድካሞችንን የምንጥልበት ነው።
- ኃጢአታችንን የምንደመስስበት ነው።
- ሸክማችንን የምናራግፍበት ነው።

ለዚህች ዓለም የሚያስፈልጋት የኒውክለር ኃይል ሳይሆን የጸሎት ኃይል ነው።

እግዚአብሔር ሕያው ነው። ህልውናውም በአስተማማኝ መልኩ በዙሪያችን ሰፍኗል። ከእስትንፋሳችንም ይልቅ ቅርብ ነው። ሕይወት ያለው ነገር ደግሞ ኅብረት ያደርጋል። እግዚአብሔርም ሕያው ነውና ከእኛ ጋር ኅብረት ማድረግ ይፈልጋል። ጽድቁንና ቅድስናውን ከመካፈል ቀጥሎ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የምናደርገው በጸሎት ነው። ጸሎት በዙሪያችን የሰፈነው የእግዚአብሔር ህልውና ይበልጥ እንዲሰማን ያደርጋል። የእግዚአብሔር ህልውና ሲሰማን፡-

- ተስፋችን ይለመልማል፣
- ሸክማችን ቀሎ ይታየናል፣
- ኃጢአታችን ይፈወሳል፣
- ጠላቶቻችንን እናያቸዋለን፣
- ፍርሃታችን ይወገዳል፣
- ማውራት /መተንፈስ/ እንጀምራለን።

ጸሎት የእግዚአብሔር እጆች እንዲዘረጉልን የምንወተውትበት፣ የእኛ የውዳቂዎቹ ኃይል ነው። ብዙ ሰዎች «እንግዲህ ከመጸለይ ውጭ ምንም አማራጭ የለኝም» ይላሉ። የጸሎትን ኃይል እንደ ቀላል ቆጥረውት ነው። ነገር ግን ከመጸለይ የበለጠ ምን ዓይነት አማራጭና መፍትሔ አለ? በጸሎት የማይቻሉ ነገሮች ሲቻሉ አይተናል። ጦርነት ሲበርድ፣ ጠላቶች ሲታረቁ፣ የማይድኑ በሽታዎች ሲድኑ፣ ድሆች ሲጠግቡ ሕያው ምስክሮች ነን። ሰይጣን የሚፈራው የጦር መሣሪያን የያዘ ሰው አይደለም። እንደውም የጦር መሣሪያ እንዲኖረን



ይመክረናል። ሰይጣን የሚፈራው ጸሎትን ነው። ለዚህ ነው እንዳንጸልይ በብርቱ የሚዋጋን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው የእግዚአብሔር ሰዎች በጸሎት ኃይል ሲጠቀሙና ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ተአምራት ሲፈጸምላቸው እናነባለን።

- ኤልያስ በጸሎት 3 ዓመት ከመንፈቅ ሰማይን ለጉሟል። በጸሎት እንደ ገና ዝናብን አዝንቧል።
- ዳንኤል በጸሎት የአንበሳ አፍ ተዘግቶለታል።
- ጴጥሮስ በጸሎት ከሞት ፍርድና ከወኅኒ አምልጧል።

የሚበዛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ ጸሎትና ምላሾቹ የሚናገር ነው። መዝሙረ ዳዊትን ስንመለከት በተለያየ የሕይወት ገጽታ ውስጥ አማንያን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የአምልኮ ግንኙነት በደንብ ያሳያል። ለእግዚአብሔር የማይነገር ደስታ፣ የማይገለጥ ሐፍረት እንደ ሌለ መዝሙራቱ ያሳዩናል። ደግሞም በድካም ጊዜ ለመበርታት፤ በሀዘን ጊዜ ለመጽናናት፤ በችግር ጊዜ እርዳታ ለማግኘት፤ በበደለኝነት ስሜት ጊዜ ይቅርታ ለመቀበል፤ በብቸኝነት ዘመን መንፈሳዊ ሙቀትን ለማግኘት፤ በስደት ጊዜ መጠጊያ ለመፈለግ፤ በጦርነት ዘመን ድል ለመቀበል፤ በጭንቀት ወቅት ሰፋትን ለማግኘት ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ጸሎትን እንደ ተጠቀሙ እናያለን።

በ1ነገ. 17፥1 ላይ ያለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተቀመጡት አስደናቂ የእውነት ፈርጦች አንዱ ነው። ቃሉ እንዲህ ይላል፡- *«በፊቱ የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም።»* ነቢዩ ኤልያስ በእስራኤል ንጉሥ በአክአብ ፊት ቆሞ የሚሰማው ገና በእግዚአብሔር ፊት እንደ ቆመ ነው። የድፍረቱ ምሥጢር ይህ ነው። በእግዚአብሔር ፊት መቆምን የተለማመደ በሰው ፊት መቆም አያሳፍረውም። እውነትን የምንናገረውም በእግዚአብሔር ፊት እንደ ቆምን ሲሰማን ብቻ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ስንቆም ኃይል እንሞላለን። ጨረቃ በፀሐይ ፊት ስላለች የፀሐይ ብርሃን ተስሎባት ለጨለማው ዓለም እንደምታበራ ክርስቲያንም በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ሲሆን የእግዚአብሔር ኃይልና ብርሃን ይሳልበታል። በጭንቀት ለሚኖሩም መጽናናትን ይዞ ይወጣል።

እንደ ኤልያስ ያለ መንፈሳዊ ልምምድ የምናገኘው በነቢዩ ኢሳይያስ ሕይወት ነው:: ቃሉ እንዲህ ይላል:- *«ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር:: ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር»* (ኢሳ. 6፥1-3)::

ዖዝያን ኢሳይያስን ያስፈራው ንጉሥ ነበር:: ኢሳይያስ የፈራው ዖዝያን ግን ሞተ:: እግዚአብሔርም ለኢሳይያስ ተገለጠለት:: ዖዝያን በሞተበት ዓመት በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ሆኖ መገለጡ:- «ዖዝያን ሞተ እኔ ግን አለሁ» ማለቱ ነው:: የልብሱ ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር:: ሱራፌል ደግሞ በልብሱ ዘርፍ ላይ ቆመው ነበር:: በአባታቸው ልብስ ላይ ቆመው የሚናገሩ ሕፃናት ብቻ ናቸው:: ሱራፌልም በልብሱ ዘርፍ ላይ ቆመው ያመለኩት ነበር:: እኛም ስንጸልይ በልብሱ ዘርፍ ላይ ሆነን ነው:: ታዲያ እግዚአብሔር በልብሱ ዘርፍ ላይ ሆነን የነገርነውን ልመና እንዴት ይረሳል? ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ሲያይ ኃጢአተኝነቱ ታየው:: ቆሻሻን የሚያሳይ ንጹሕ መስታወት ነውና በእግዚአብሔር የቅድስና ብርሃን ፊት ማንነቱን ካየ በኋላ ንስሐ ገባ:: ጸሎት ኃይል አለው:: የተቋረጠውን ግንኙነት ያድሳል:: በበደለኝነት ስሜት ለሚሰቃየው ዕረፍትና እንቅልፍ ይሰጣል:: ሽፍታው ጭምት፣ ሌባው መጽዋች፣ ዘማዊው የንጽሕና ወዳጅ የሚሆነው በጸሎት መንገድ ተጠቅሞ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመቀዳጀት ነው::

ባለንበት ዘመን መረጃ ኃይል እንደሆነ ይነገራል:: ስለዚህ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት መረጃ የሚሰጡ መንገዶችን በመፈላለግና ያገኙትንም መረጃ በማስተላለፍ ነው:: ትልቁ የመረጃ መስመር ግን ጸሎት ነው:: እግዚአብሔር የዘመኑን ሁኔታ፣ ሊያደርግ ያለውን እቅድ፣ ለመጨረሻው ቀጠሮ የቀረውን ጊዜ የሚገልጠው በጽሞናና በጸሎት ለሚጠባበቁት ልጆቹ ነው:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች በጸሎት ምሥጢርን ስለሚያውቁ ሕይወትን ሲሆን ብቻ ሳይሆን ከመሆኗ በፊት ያውቋቷል:: *«በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም»* (አሞ. 3፥7)::



# <u>ምዕራፍ አምስት</u>

## <u>የጸሎት ምክንያታችን</u>

*«ጸሎትንም ሆነ ማንኛውንም በጎ ምግባር የምናከናውነው ለራሳችን ብለን እንደ ምግብና መጠጥ ስለሚያስፈልገን ነው::»*

ሁሉም ነገር የራሱ ምክንያት አለው:: ላለመጸለያችን ምክንያት ማቅረብ ብንወድም መጸለይ እንዳለብን ደግሞ ብዙ ምክንያቶች መኖራቸውን እንረሳለን:: አንዳንዶች መጸለይ እንዳለባቸው ስንነግራቸው ችግር አለባችሁ የተባሉ ይመስላቸውና «የሚያጸልየኝ ምንም ምክንያት የለም» ብለው ያስባሉ:: ሌሎችም ጸልዩ ስንላቸው «ያለነው በጸሎታችን ነው» ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች ሲጀመር አይጸልዩም:: ሌላው ደግሞ የሚኖሩት በቸርነቱ መሆኑን ዘንግተዋል:: የተቀሩትም ጸልዩ ስንላቸው የማይፈጽሙትን «እሺ» ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች ለመንፈሳዊ ነገር የሚታዘዙት ለመንፈሳውያን አገልጋዮች ጥቅም ብለው እንጂ ለራሳቸው አይመስላቸውም:: ጥቂቶችም ጸልዩ ስንላቸው «ሁለት ሥራ ነው የምሠራው፣ ካልሠራው እንዴት ቤተሰቤን አስተዳድራለሁ? ሁለት ትምህርት ነው የምማረው ባይሆን ትምህርቴን ስጨርስ እንጂ እያወቃችሁ እንዴት ጊዜዬን የሚሻማ ነገር ታዙልኛላችሁ?» በማለት ይቆጡናል:: እግዚአብሔር ካልሮጠበት የሰው ሩጫ ትርፉ ድካም ብቻ መሆኑ አልገባቸውም:: *«እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፥ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፥ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል:: በማለዳ መገስገሳችሁም ከንቱ ነው:: ለወዳጆቹ እንቅልፍን በሰጠ ጊዜ፥ እናንተ የመከራን እንጀራ የምትበሉ፥ ከተቀመጣችሁበት ተነሡ»* (መዝ. 126(127)፥1-2) የሚለውን ቃል አላስተዋሉም:: ሌሎችም ጸልዩ ስንላቸው «እኔ በጉልበቴ፣ ሚስቴ በጸሎት እየተጋገዝን ነው የምንኖረው» ያላሉ:: እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር መንግሥት በውክልና ይመስላቸዋል:: መንግሥቱ ከእስትንፋሳችን ይልቅ ስለቀረበችን ውክልና የለባትም:: ተራኞችም «ባለጠጋ በምጽዋቱ፣ ደሃ በጸሎቱ» ይላሉ:: አዎ ላለመጸለይ ከምናቀርበው ምክንያት ይልቅ ለመጸለይ ያለን ምክንያት ብዙ ነው::

ለመጸለይ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩንም በዚህ ክፍል ሦስቱን ለማየት መርጠናል:: እነርሱም:-

1. ጸሎት የማያቋርጥ አገልግሎት በመሆኑ፣
2. ማንኛውም በጎ ነገር ያለ ጸሎት ኃይል ስለ ሌለው፤
3. በክፉ ዘመን የማምለጫው መርከብ ጸሎት በመሆኑ ነው።

## 1. <u>ጸሎት የማያቋርጥ አገልግሎት በመሆኑ</u>

ጸሎት ጠዋት ከእንቅልፋችን ስንነሣ «በሰላም ያሳደርከኝ አምላክ በሰላም አውለኝ» ወይም ማታ መቀነታችንን ስንፈታ «በሰላም ያዋልከኝ አምላክ በሰላም አሳድረኝ» ብለን ብቻ የምናከናውነው፣ አልፎ አልፎ ወይም የሰንበት ቀን አሊያም በወር መባቻ ቀን ደግሞም ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ብቻ የምናደርገው ሳይሆን ጸሎት የማያቋርጥ አገልግሎት ነው። እስትንፋስ የማያቋርጥ የሕይወት ሂደት እንደሆነ ሁሉ ጸሎትም የክርስትናው እስትንፋስ ነው። ዓሣ ከውኃ ለብዙ ሰዓት ተለይቶ በሕይወት መኖር እንደማይችል ክርስቲያንም ያለ ጸሎት መንፈሳዊ ህልውናውን ጠብቆ መቆየት አይችልም። ልጆች በማለዳ ከአባታቸው ጋር መገናኘት ደስ ይላቸዋል። ግድ ሆኖባቸው እንጂ ቀኑን በሙሉ አብረው ቢውሉ፣ አብረው ቢሄዱም ይመኛሉ። ማታም ከእንቅልፋቸው ጋር እየታገሉ አባታቸውን ይጠብቃሉ። እንዲሁም ማንኛውም ክርስቲያን በማለዳ ከሰማያዊው አባት ጋር በጸሎት በመገናኘት አብሮ መዋል አብሮ ማደር ይገባዋል።

ክርስቲያን እንደ ነቢዩ ዳንኤል በመጸለዩ መከሰስ አለበት እንጂ ባለመጸለዩ ከተወቀሰ ያለው አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነው። የማያምነው ንጉሥ እንኳ ዳንኤልን፦ *‹‹የሕያው አምላክ ባሪያ ዳንኤል ሆይ፥ ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ ከአንበሶች ያድንህ ዘንድ ችሎአልን?››* (ዳን. 6፥20) ብሎታል። እግዚአብሔር የሁልጊዜ አምላክ ነው። ጸሎት ሁልጊዜ የምናከናውነው ተግባር እንጂ አጋጣሚ ወይም እግረ መንገድ ጎራ የምንልበት መበዘኛ አይደለም። ለሰው ከነፍስ የሚበልጥ ጉዳይ፣ ከጸሎት የሚበልጥ ሥራ የለበትምና የሰው ልጅ «ጉዳይ አለኝ፣ ሥራ ነኝ» እያለ ጸሎትን ቢተው ይጎዳል። የምንጸልየው ለእግዚአብሔር ብለን ሳይሆን ለራሳችን ብለን ነውና። ነቢዩ ዮናስ ሥራህ ምንድነው? ቢሉት፦ *«ባሕሩንና የብሱን የፈጠረውን እግዚአብሔርን አመልካለሁ»* (ዮና. 1፥9) ያለው ቃል ለክርስቲያኖች ያኮራል። አምልኮ ሥራ ነው። አንድ አባት «የምንበላው የምንጠጣው እግዚአብሔር እንዳይቀየመን ብለን ነውን?» ብለው ከጠየቁ በኋላ «አይደለም ለመኖር ብለን ነው። ጸሎትንም ሆነ ማንኛውንም በጎ



ምግባር የምናከናውነው ለራሳችን ብለን እንደ ምግብና መጠጥ ስለሚያስፈልገን ነው» ብለዋል።

*ቃሉም «ሳታቋርጡ ጸልዩ»* (1ተሰ. 5፥17) ይላል። አልፎ አልፎ ወይም ጠዋትና ማታ፣ በቀን ሰባት ጊዜ ሳይሆን ሳናቋርጥ እንድንጸልይ ታዘናል። ስንተኛ፣ ስንነሣ፣ ስንቀመጥ፣ ስንጓዝ፣ ስንበላ፣ ስንጠጣ፣ ከሰዎች ጋር ስንገናኝ፣ ሥራችንን ስንጀምር ... መጸለይ ይገባናል። ሰዎች እንዲያዩን ለታይታ ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲያየንና እንዲሰማን በመንገድም ስንጓዝ፣ ሰዎች ቀጥረውን ሲዘገዩ፣ የምክር አገልግሎት ስንሰጥ በልባችን ካመቸንም በለሆሳስ መጸለይ ይገባናል። በገበያ ስፍራ ውስጥ ሆነንም ልንጸልይ እንችላለን። እኛ ለመጸለይ ካልቸገረን እግዚአብሔር ለመስማት ጫጫታው አይረብሸውም። እናት በብዙ ጫጫታ ውስጥ የልጇን ድምፅ እንደምትለይ እግዚአብሔርም የእኛን ጩኸት ለመስማት ይተጋል።

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ፦ *«ስለዚህ ቅዱስ ሁሉ በምቹ ጊዜ ወደ አንተ ይለምናል፤ ብዙ የጥፋት ውኃም ወደ እርሱ አይቀርብም»* (31÷6) ብሏል። ስብሰባችንን ልክ ስንጨርስ፣ ከአንዱ ቢሮ ልክ ስንወጣ፣ ከአውሮፕላን ልክ ስንወርድ፣ ፋታን ባገኘን ጊዜ ሁሉ የምንደውልላቸው የእኛ ሰዎች አሉ። ከእነርሱ ይልቅ በምቹ ጊዜ ልናገኘው የሚገባን እግዚአብሔርን ነው። በምቹ ጊዜ ሁሉ ስንጸልይ የጥፋት ውኃም ወደ እኛ አይቀርብም።

*ዳግመኛም «በሁሉ አመስግኑ»* የሚለውን ቃል ስናስታውስ ጸሎት የማያቋርጥ አገልግሎት እንደሆነ እንረዳለን።

## 2. <u>ማንኛውም በጎ ነገር ያለ ጸሎት ኃይል ስለ ሌለው</u>

በጎ ነገር እግዚአብሔርና በጎ ሰዎችን ደስ የሚያሰኝ እንጂ በራሱ ኃይል አይደለም። የበጎ ነገር ኃይል ጸሎት ነው። ስለዚህ ለሠርጋችን፣ ለትዳራችን፣ ለልጆቻችን፣ ለምናደርገው እርዳታ፣ ላሰብነው አዲስ ዕቅድ፣ ለምናገለግለው መንፈሳዊ አገልግሎት ጸሎት ያስፈልገናል። የተሳኩ አገልግሎቶች ከጀርባቸው ያለው ምሥጢር ምንድነው? ብንል ጸሎት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ክርስቲያን አይሁዶች ከአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት እርዳታ ከሰበሰበ በኋላ በልቡ ተጨነቀ። ይኸውም በቅን ልብ የሆነውን እርዳታ የአይሁድ ክርስቲያኖች በቅን ልብ ባይቀበሉትስ ብሎ ነው? ይህን ጭንቀቱንና

የጸሎት እርዳታ መፈለጉን ለሮሜ ክርስቲያኖች ገለጠ (ሮሜ. 15÷32)። የኢየሩሳሌም ድሆች ተቸግረዋል። ለተቸገረ ደግሞ እርዳታ አስደሳች ነው፤ ጸሎት ምን ያደርጋል? ብንል እርዳታ ብዙ ጊዜ ቅን ተቀባይ አያገኝም። ጸሎት ግን ሰጪውንም ተቀባዩንም የማስደሰት አቅም አለው። በጎ ነገር ከያዝን ጸሎት የሚያስፈልገው አይመስለንም። የጳውሎስ ልምምድ ግን ለእኛ ትልቅ ትምህርት ነው።

በበጎ የተጀመረ በበጎ እንዲያልቅ፣ በመንፈስ የተጀመረ በመንፈስ እንዲደመደም፣ እርዳታችን ሁሉ የፍቅር ትርጉም እንዲያገኝ ጸሎት ያስፈልጋል። መልካም ትዳር፣ የተባረኩ ልጆች፣ እግዚአብሔርን ብቻ የሚያስከብር አገልግሎት እንዲኖረን ጸሎት ያስፈልጋል። በርግጥ ጸሎት ተግባርን አይተካም፣ ጸሎት ግን ተግባርን ያጠነክራል።

ይልቁንም መንፈሳዊ አገልግሎት እንደ ሥጋ ተግባር ጉልበትን ብቻ የሚጠይቅ አይደለም። ሰይጣናዊ ውጊያ ስላለው መጸለይ ወሳኝ ነው። ውጊያው ያለው በአደባባይ ቆሞ በመስበክ ወይም በመዘመር ላይ አይደለም። ውጊያው ያለው ጸሎት ላይ ነው። የአደባባይ ስብከትም ሆነ ዝማሬ ምርኮ መሰብሰብ ነው። ታዲያ ያልተዋጋነውን መማረክ፣ ያላሰርነውን መበዝበዝ እንዴት ይቻለናል? (ማቴ. 12÷29)።

## 3. <u>በክፉ ዘመን የማምለጫው መርከብ ጸሎት በመሆኑ</u>

ክፉ ዘመን ጥንትም ነበር። የኖኅ ዘመን የጥፋት ውኃ፣ የሰዶምና የገሞራ እልቂት ይህን ያሳየናል። በአባቶቻችንም ዘመን ክፉ ነገር ነበር። ለምሳሌ:- የአንደኛና ሁለተኛው ዓለም ጦርነት ሊጠቀስ ይችላል። ባለንበትም ዘመን ክፉ ነገር አለ። ሰው እስካልተመሰለ ድረስ ክፋት በቅቶኛል ብሎ በራሱ አይቆምም። ሥራ እስካለ ደሞዝ ክፋይ እንዳለ ሁሉ ክፉ ነገርም የሥራችን ደሞዝ ሆኖ ይኖራል። ካለፉት ዘመናት ይልቅ ክፉ ነገር የበዛበት ዘመን የእኛ ዘመን ነው። ክፉ ነገርን ከመልመዳችን የተነሣ አሁን ያለው ክፉ ነገር ሳይሆን የሚመጣው ነው የሚያስፈራን። በዜና ማሰራጫዎች ዕለት ዕለት የምንሰማው ነገሥታትና ሕዝቦች ምጥ ላይ መሆናቸውን ነው። የእግዚአብሔር ቃል ትንቢቶችን ስናጠና ክፋት እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይመጣም።

ታዲያ በክፉ ዘመን የማምለጫው መርከብ ምንድነው? ስንል በተሰበረ ልብ የሚቀርብ ጸሎት ነው። እነ ኖኅ፣ እነ ሎጥ እንደ ዳኑ፣ በክፉ ቀን ውስጥ እንዳለፉ እናነባለን። «አድነኝ» ብለን የምንጸልየው



የሚያድነውን አምላክ ነው። ደርግ ሲወድቅ አቅራቢያ በአዲስ አበባና በአካባቢዋ የነበረው ጸሎትና ዕንባ ምን እንደ ሠራ እናውቃለን። እግዚአብሔር ይሰማል፣ ያድናል። በአገራችን ክብትና አዝመራ የሚያጠፋ መቅሰፍት ሲመጣ «እግዚኦ» ይባል ነበር። መቅሰፍቱም ሲመለስ ድርቁም ሲርቅ እናውቃለን። ዛሬ ግን ይህ ሁሉ ወጣት በቅጠል ሲቀር «እግዚኦ» የሚል መጥፋቱ ምን ያህል እምነት እንደ ራቀን ያሳያል። አዎ የእግዚአብሔር እጅ የምናውቀው ነው።

ሞት ሰይፍ ይዞ በጎዳና በወጣበት፣ ሰው ለሰው አውሬው በሆነበት፣ ከምንም በላይ ራሳችን ለራሳችን ጠላት በሆንበት ዘመን በንጹሕ ልብ የምትቀርብ ጸሎት ይህን ክፉ ነፋስ ትለውጣለች። ጸሎት ክፉ ቀን ሳይመጣ ነው። ክፉ ቀን ከመጣ በኋላ ግን እየተገረፉ እንደ መጮህ ነው። አዎ በደግ ቀን ያልጸለዩት ጸሎት በክፉ ቀን አይረዳም። በጦርነት፣ በረሀብ፣ በእርስ በርስ እልቂት ዘመን ሕዝቦችን ያዳኑ ታሪካዊ መርከቦች አሉ። ከዚያ ይልቅ በጸሎት መርከብ ባሕሩን የተሻገሩ፣ ማዕበሉን ያለፉ ብዙ ምስክሮችን ምድር ተሸክማለች። እግዚአብሔር በክፉ ቀን መንገድ ይሰጣል። ነገሥታት በጦርነት ቀጠና ውስጥ ለቱሪስቶች የደኅንነት ዋስትና ለመስጠት አይደፍሩም። እግዚአብሔር ግን በዐውሎና በወጀብ ውስጥ መንገድ አለው (ኢሳ. 43፥2፤ ናሆም 1፥3)።

በአንድ ኵሬ ውስጥ የሚኖሩ እንቍራሪቶች ይዘላሉ ይጨፍራሉ። ከመካከላቸው ግን አንዷ ጥግ ይዛ «አውጣኝ አውጣኝ» እያለች ትጸልያለች። ባልንጀሮቿም ወደ እርሷ መጥተው:- «ከእኛ ጋር የማትደሰችው ጥግ ይዘሽ የምትጮኺው ለምንድነው?» አሏት። እርሷም:- «እዚያ ማዶ ቤት ሲቃጠል አያለሁ፣ ስለዚህ አውጣኝ እላለሁ» አለች። እነርሱም:- «ቤት የሚቃጠለው እዚያ ማዶ ነው፣ እኛ ያለነው ውኃ ውስጥ ነው ምን አስጨንቆሽ ነው?» አሏት። እርሷም:- «እሳቱን ለማጥፋት በአቅራቢያቸው ያለውን ውኃ ተጠቅመው አልጠፋ ካላቸው ውኃ ለመቅዳት የሚመጡት ከዚህ ነውና አውጣኝ እላለሁ» አለቻቸው። እነርሱ ግን ዘብተውባት ዝላያቸውን ቀጠሉ። እሳቱም እየፀና መጣ። አቅራቢያው ባለው ውኃ፣ ቅጠልና አፈር ቢሞክር አልጠፋ ሳላለ የአካባቢው ሰው ባልዲውን እየያዘ ወደ ኵሬው መጒረፍ ጀመረ። እነዚያ ይዘሉ የነበሩት እንቍራሪቶችን ዝቀው እሳት ውስጥ ሲጨምሯቸው ያች አውጣኝ የምትለው እንቍራሪት ግን ዳነች። «አውጣኝ ያለም ወጣ፣ ያላለም ተቀጣ።»

«ዳር ሲነካ መሐል ይሆናል» እንደሚባለው ሩቅ የሚመስለው የሰዎች ጥፋት ካልተጠነቀቅነውና ካልጸለይን ወደ እኛም ይመጣል። የጎረቤታችን ውድቀትና ሞት ለእኛ ማስጠንቀቂያ እንጂ የጨዋታ ርእሳችን አይደለም። በባላገር ዳስ ጥለው ይዘፍናሉ። ዳሱም ቶሎ ይፈርሳል። በዚህ ምክንያት «የዘፈን ቤት ሳይፈርስ አይቀርም» ይባላል። እንዲሁም ጭፈራና ብዙ ደስታ ልቅሶና ዋይታ ሳያመጣ በፍጹም አይቀርም። ለሰዎች ማዘን ሲያለቅሱ ሳይሆን ዘፈን ዘፈን ሲላቸው ነው። የሚቀጥለው ልቅሶ ነውና። በእውነት በክፉ ዘመን የማምለጫው መርከብ መረጃ ሳይሆን ጸሎት ነው። አዎ ለመጸለይ ያለን ምክንያት ከምክንያት የሚልቅ ነው፡-

1. ጸሎት የማያቋርጥ አገልግሎት በመሆኑ፣
2. ማንኛውም በጎ ነገር ያለ ጸሎት ኃይል ስለሌለው፤
3. በክፉ ዘመን የማምለጫው መርከብ ጸሎት በመሆኑ ነው።



# ምዕራፍ ስድስት

# ጸሎትና አገልግሎት

*«የተከበረ አገልግሎት ለሰዎች ስለ እግዚአብሔር በመንገር ሳይሆን ለእግዚአብሔር ስለ ሰዎች በመንገር የሚጀመር ነው።»*

አገልግሎት ጦርነት ነው። ሰይጣን በኃጢአት ያሰራቸውን፣ በድንቁርና የጋረዳቸውን፣ በደዌና በጭንቀት ያጋዛቸውን ሰዎች ነጻ ለማውጣት የሚደረግ መንፈሳዊ ትግል ነው። ሰዎችን ወደ ወንጌል እውነት ለመመለስ ከእቅዶቻችንና ከበጀታችን በላይ የሚያስፈልገን መንፈሳዊ ኃይል ነው። ያለ እቅድ ያለ በጀት ማገልገል ይቻላል። ያለ ራእይና ያለ ጸሎት ግን ማገልገል አይቻልም። ያለ ጸሎት የሚያገለግል አገልጋይ በተፋፋመ ጦርነት ውስጥ መሣሪያውን ጥሎ እንደሚንጎማለል ወታደር ነው። የሚጠብቀው ነገር ቢኖር ቀጥሎ መውደቅ ብቻ ነው።

እንደ ዓላማና እቅድ ያለው ጦርነት ሦስት ነገሮች ሊኖሩት ግድ ነው። ደጀን፣ የጦር ሰፈርና ምቹ የሆነ የውጊያ ስፍራ። ደጀኑ ስንቅና ትጥቁ እንዳይጓደል ከኋላ ሆኖ የሚገፋ ኃይል ነው። ደጀኑ በጦርነቱ ላይ አይታይም፣ በድሉ ላይ ግን ይታያል። የጦር ሰፈሩ ደግሞ ውጊያ በወረቀትና በሜዳ ላይ የሚሠራበት፣ የመመካከሪያ ቦታ ነው። ጦርነቱ የሞት ሽረት ትግል የሚካሄድበት ደጀኑ የሚኮራበት፣ በጦር ሰፈር የተሠራው የውጊያ ሥዕል በተግባር የሚተረጎምበት፣ ግዛት ማስለቀቅና ግዛት መያዝ የሚከናወንበት ነው።

በመንፈሳዊ አገልግሎትም የሚታየው ነገር በማይታይ ሁኔታ ይፈጸማል። አገልግሎትም ደጀን፣ የጦር ሰፈርና የውጊያ ዐውድ በትክክል አለው። ገንዘባቸውን የሚሰጡ፣ አገልጋዮችን የሚያስተናግዱ፣ በቤተ ክርስቲያን ጀርባ ሆነው የሚጸልዩ ምእመናን ደጀን ናቸው። የሰባኪው ድል ያለው እዚህ ነው። ዳዊት ለእስራኤል የዘመናት ሥርዓት የሚሆን የምርኮ ሕግ አውጥቶ ነበር። ይህ ሕግ

በጦር ሜዳ የተዋጋውና የጦሩን ስንቅና ልብስ የጠበቀው ወገን ምርኮን እኩል እንዲካፈል የሚል ነው (1ሳሙ. 30፥24-25)። የወታደር ድል ያለው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ራሱ ጋ አይደለም። ከኋላ ደጀን ሆኖ የሚያበረታው፣ ስንቅና ትጥቅ የሚያቀርብለት ሕዝብ አለ። የድሉ ክብር ደጀን ለሆነውም ሕዝብ ጭምር ነው። ስለዚህ የውጊያውን ድምዳሜ የሚያበስረውን ምርኮ ደጀኑም እኩል መካፈል አለበት ብሎ ዳዊት በዘመኑ ደነገገ። የአደባባይ ዝማሬዎች፣ የአደባባይ ስብከቶች ድል የሚኖራቸው ከጀርባ የጸሎት ደጀን ካላቸው ብቻ ነው። ምሽግ ሳይቆፍር የሚዋጋ ወታደር ለጠላቱ ዒላማ የተመቻቸ ሲሆን ብዙም ሳይቆይ በጠላቱ ቀስት ይወድቃል። የጸሎት ምሽግ ያልቆፈረ አገልጋይም የሚንጎማለለው ለጊዜው ነው። በጠላቱ ቀስት ተመትቶ ይወድቃል።

ለዘመናት እሳታቸው ያልጠፋ አገልግሎቶች፣ ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ የመለሱ ራእዮች፣ ቦግ ብለው ያልጨለሙ መነቃቃቶች ከጀርባቸው ያለው ምሥጢር ጸሎት ነው። በእውነት ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ አባቶችን፣ ምእመናንን የሚያጸኑ አገልጋዮችን፣ ሕዝብን ለአምልኮ የሚቀሰቅሱ ዘማርያንን ያህል በድብቅ የሚጸልዩ ምእመናን ዋጋቸው እኩል ነው። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያለው ውጊያ ከግልጹ በሸሸግ ጸሎት የሚያልቅ ነው። አስተዋይ የሆነ አገልጋይ በጸሎት ይተጋል፣ የጸሎት ሠራዊት ይመለምላል፣ የምእመናንን የጸሎት እርዳታ ይጠይቃል።

የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት የዘመን ርቀት፣ የመከራ ወላፈን፣ የተግዳሮት ብዛት ሊያጠፋው ያልቻለው ለምንድን ነው? ስንል በጸሎት ላይ የተመሠረተ አገልግሎት ስለ ነበር ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአገልግሎቱ መልስ፣ ከአደባባይ ገለል ሲል ከሰማያዊ አባቱ ጋር በጸሎት ይገናኝ ነበር። ብዙ ሌሊቶችን በደብረ ዘይት ጫካ ውስጥ በመጸለይ አሳልፏል። መለኮታዊ ምሪት ያለው አገልግሎትም የምሪት መቀበያው መንገድ ጸሎት መሆኑን በተግባር አሳይቷል። በአገልግሎቱ በዋናነት ጸሎትን እንዴት እንደ ተጠቀመ አራት ሁኔታዎችን እናያለን።

1. ገዳመ ቆሮንቶስ
2. የጸሎት ሌሊት
3. ጌቴሴማኒ
4. ቀራንዮ



# 1. <u>ገዳመ ቆሮንቶስ</u>

በማቴ. 4፥1-11 ላይ ስናነብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አገልግሎት ከመግባቱ በፊት ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት በጾም በጸሎት እንደ ቆየ ይነግረናል። የተከበረ አገልግሎት ለሰዎች ስለ እግዚአብሔር በመንገር ሳይሆን ለእግዚአብሔር ስለ ሰዎች በመንገር የሚጀመር ነው። ከዘር በፊት መሬት መቆፈርና መለስለስ አለበት። የሰውን ልብ ለወንጌል የምናለሰልሰው በጸሎት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት በጾም በጸሎት የሆነው አገልግሎቱን ለአባቱ ለማስረከብ በተጨማሪም የሚገጥመውን የወንጌል ተግዳሮት ቁጭ ብሎ ለማጤን ነው።

ሰይጣን እንደ ፈተነው ተጽፎአል። ትልቁ ውጊያ ያለው ቆሞ በመስበክ፣ ቆሞ በመዘመር ላይ አይደለም። ውጊያው ያለው ጸሎት ላይ ነው። ስብከትና ዝማሬም ምርኮ መሰብሰቢያ ነው። ግን ያልመቱትን ወይም ያልገደሉትን መማረክ እንዴት ይቻላል? ያለ ጸሎት የሚሰብኩ፣ የሚዘምሩ አሉ። አገልግሎታቸው ግን ጭርታን ለማጥፋት ካልሆነ በቀር ውስጥን የመግዛትና ለምእመናን የሕይወትን ኮምፓስ ማስጨበጥ የቻለ አይደለም። የስብከት ዘዴን ስናስተምር ለ10 ደቂቃ ስብከት አንድ ሰዓት መጸለይ ተገቢ መሆኑን እናስተምራለን። ዛሬ በመንፈሳዊ ኮሌጆችና ተቋማት የሚሰጡት የስብከት ዘዴዎች የጸሎትን ኃይል የጣሉ የኑሮ ዘዴዎች መሆናቸው ያሳዝናል። ከዚያ ቦታ የሚወጡ የእምነት ሰዎች ጥቂቶች መሆናቸውን ስናስብ ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን በጀት ክህደቱን እንዴት እያስፋፋ መሆኑን እንገነዘባለን።

# 2. <u>የጸሎት ሌሊት</u>

ለመጸለይ ማታ ላይ እንቅልፍ የሚጥላቸው ወገኖች ብዙ ናቸው። ፊልምና ኳስ ለማየት ግን አይጥላቸውም። ሌሊት ነቅተው ሲያዳንቁ ጎበዝ ናቸው። የሚመለከታቸውን ጸሎት ትተው የማይመለከታቸውን ፈረንጅ ሲያመልኩ ያድራሉ። እነዚህ ሰዎች ጸሎት እንዲሁ የሚከናወን እንጂ ውጊያ ያለበት አይመስላቸውም። ሰይጣን እንዳንጸልይ በብርቱ ይዋጋናል። በአዚም በድንዛዜ፣ በስልቹነት፣ በስንፍና፣ ቢዚ በማድረግ፣ ግርግር በማብዛት፣ ስልኮቻችንን ፋታ በማሳጣት ይዋጋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሌሊቱን በሙሉ ሲጸልይ እንዳደረ የተጻፈው ደቀ መዛሙርቱን ለመምረጥ ነው:: ዓለምን የሚለውጠውን አገልግሎት በዕቅድ ሳይሆን በጸሎት አደረገው:: ሉቃስ 6፥12-16 ይህን በደንብ ይነግረናል:: ተተኪ አገልጋዮችን ቅልጥፍናን በማየት እኛ የምንመርጠው ሳይሆን በጸሎት አሳልፈን በመስጠት እግዚአብሔር የሚመርጠው ነው:: እኛ እንኳን ለእግዚአብሔር ለራሳችንም መምረጥ አንችልም:: ይልቁንም ጌታችን በሌላ ስፍራ:- *«መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት»* (ሉቃ. 10፥2) ብሏል:: አጽናኙን ሰብስቡን የሚል የደረሰ ራሱ የመጣ መከር (ትውልድ) ዛሬ እያየን ነው:: አገልጋዮቹ ደግሞ መከሩን ትተው የሚሰክሩና የሚዘፍኑ ሆነዋል:: ታዲያ ይህ ጸሎት የዘመናችን ጸሎት አይደለምን? «ሕዝብህ ሰብሳቢ አጥቶ ይባዝናል:: የሰው ምግብ ቢያጣ ከዕሪያ አሠር ከተረትና ከዘፈን በልቶ ለመጥገብ ጠጥቶ ለመርካት ይመኛል:: እባክህ ጌታ ሆይ ለመንጋው የምታዝን አንተ ነህና በግ ነጋዴዎችን የበግ ሌቦችን አስወግደህ የበግ ጠባቂዎችን አስነሣልን» እያልን በብርቱ መማለድ ይገባናል::

## 3. ጌቴሴማኒ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተልዕኮውን ሲፈጽም ጥቂት ጊዜ ቀርቶታል:: እንደ ነገ በቀራንዮ ተሰቅሎ የሰውን ሞት ሰራሉ፣ የእርሱን ሕይወት ለሰው ሊሰጥ ተቃርቧል:: በጌቴሴማኒ ግን ብርቱ ጸሎት ከዕንባና ከጣር ድምፅ ጋር አቀረበ:: በጸሎቱ ላይ ደጋግሞ የተናገረው:- *«አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ! ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን»* (ማቴ. 26፥39) በማለት ነው:: ከጣር ጭንቀቱ በላይ የከበደው የአባቱ ፈቃድ ነው:: ፈቃድህ ከሆነ ልሙት አለ:: «እግዚአብሔር ሆይ፥ አንተ የምትከብርበት ከሆነ ብቻ ልኖር፥ በእኔ የምትሠራውን ሥራ ከፈጸምክ ግን ውሰደኝ:: ሌላ የምኖርበት ምክንያት የለኝም» እያሉ የሚጸልዩ የእግዚአብሔር ሰዎችን አውቃለሁ::

ጌታችን ሕይወቱ በጸሎት የተቃኘ፣ ሞቱ እንኳ ለአባቱ ፈቃድ የተተወ ነበር:: ለእግዚአብሔር ኖሮ ለእግዚአብሔር ማለፍ እንዴት ደስ ያሰኛል? የመረጥነው ያቆሰለን ሰዎች ዛሬም እኔ ልምረጥ አንልም:: «ፈቃድህ ይሁን» እንላለን:: ለዓለም መሥዋዕት የሚሆንበት ቀን ከትልቅ መንፈሳዊ ጉባዔ በላይ ነው:: ጌታ ግን ጸለየ:: መንፈሳዊና መልካም የሚመስሉ ነገሮች ሲመጡ ፈቃድህ ነው ወይ? ብለን



ለመጸለይ ጊዜ የለንም:: እንደውም እግዚአብሔር ሳይሰማ ቶሎ ቶሎ ጨርሰን ኋላ ለመንገር እናስባለን:: «መልካም ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም!» ስለዚህ ስለ ሁሉም መጸለይ ይገባናል:: አምስት ደቂቃ ተንበርክከን ለመጸለይ ጊዜ ያጣንበትን ጉዳይ መንፈሳዊ አገልግሎት ቢሆን እንኳ ቆም እናድርገው:: ምክንያቱም ለእኛ የሚሆኑ ነገሮች ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጁ ስለሆኑ እስክንጸልይ አያልፉም::

## 4. ቀራንዮ

ቀራንዮ የመጨረሻው የዓለም ንጹሕ የተቀጣበት፣ ፍቅር በብዕር ሳይሆን በደም ነጠብጣብ የተጻፈበት፣ ወዳጅ ለጠላቶቹ የሞተበት፣ ባለቀ ሰዓትና አቅም ለባላጋሮች ክርስቶስ ይቅርታ የለመነበት ስፍራ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በጸሎት ያገለግል ነበር:- *«አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው»* (ሉቃ. 23፥34) በማለት::

ጸሎት ልባችን በቂም በበቀል ስሜት እንዳይሻክር የማለስለሻው ዘይት ነው:: ስንጸልይ በእኛና በጉዳታችን መካከል የእግዚአብሔር ጸጋ ጋሻ ይሆናል:: ጸሎት ሊያዩን የማይሹትን ሰዎች በእግዚአብሔር ዓይን የምናይበት፣ ለሰቀሉን ሰዎች የማስተዋልን ብርሃን የምንለምንበት፣ እንደ ገና በጸሎት ዋጋ ገዝተን ገንዘባችን የምናደርግበት፣ በሸለቆዎች መካከል የምንዘረጋው መንፈሳዊ ድልድይ ነው::

በሰዎች በተጐዳንበት ቅጽበት የጸሎትን ኃይል ስንጠቀም የእግዚአብሔር ጸጋ ጉዳታችንን ይካፈልልናል:: ለሰዎቹም የሚያስተውሉበት ብርሃን ይመጣል:: በአንድ ጊዜ ተጎጂውንም ጎጂውንም የሚረዳ ጸጋ ጸሎት ነው:: ከዓመታት በፊት አንድ መንፈሳዊ አባትን ለመጎብኘት እቤታቸው ድረስ ሄድኩ:: ሰላምታ ሰጥተውኝ እንደ ተቀመጥኩ የብዙ ሰዎች ስም ዝርዝር የተጻፈበት አንድ ትልቅ ወረቀት ከፊት ለፊቴ ተለጥፎ አየሁ:: ከስም ዝርዝሩ ባሻገር የገረመኝ አንዳንዱ ላይ ጭረት ተደርጓል:: ስም ዝርዝሩንና የራይት ምልክቱን ምንድነው? ብዬ ጠየቅኋቸው:: እርሳቸውም «እነዚህ ሰዎች የሰደቡኝ፣ የዛቱብኝ፣ ክፉ ያደረጉብኝ ናቸው:: ሲሰድቡኝና ክፉ ሲያደርጉብኝ የምረዳው ነገር ደክሞናል ጸልይልን ማለታቸው እንደሆነ ነው:: እነጋገሩን ስላላወቁበት እንጂ ጸልይልኝ ማለታቸው ነው:: ስለዚህ ሰው ሲሰድበኝ ስሙን እጽፋለሁ:: ንስሐ ሲገባ ራይት አደርጋለሁ» አሉኝ:: እኚህ አባት እንደ ቃሉ የሚኖሩ

እንደሆነ አውቃለሁ:: እኔስ? ብዬ ራሴን ታዘብኩኝ:: አዎ ቀራንዮ የጠፋ ወዳጅ በጸሎት ዋጋ የሚገዛበት ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱ በጸሎት እንጂ በባለጠጎች የታጀበ አልነበረም:: ስለዚህ ዛሬም ድረስ ይሠራል፣ ይማርካል:: ዘመን የሚዘልቅ አገልግሎት የጸሎት ፍሬ ነው:: አባቶች እንዳስተማሩት ጸሎት ዘር ነው:: ጸሎተኛ ደግሞ ገበሬ ነው:: ገበሬ ዘሩ እቤት ውስጥ ሳለ ጭንቀትና አሳብ የለበትም:: ጭንቀትና አሳብ ያለበት ዘሩን አውጥቶ በደጅ ከዘራ በኋላ ነው:: ዘሩ ከተዘራ በኋላ አረሙ፣ እሾኹ፣ በረዶ፣ አንበጣ፣ ኩብኩባ፣ ተምች፣ ዋግ፣ ውርጭ፣ ነቀዝ፣ ... ያሳስባሉ:: እንዲሁም ጉዳያችንን ለእግዚአብሔር በጸሎት ካቀረብን በኋላ ብዙ ፈተናና ውስብስብ ነገሮች ይከሰታሉ:: መጸለያችን እንዳባባሰው እስክናስብ ግራ እንጋባለን:: እግዚአብሔር የልመናችንን መልስ ሊሰጠን ሲመጣ ከጸሎት ስፍራችን ላይ እንድንታጣ ሰይጣን በብዙ ይታገለናል:: እግዚአብሔር ትቶአችኋል፣ እስከ መቼ የተረሳችሁ ሰዎች ትሆናላችሁ? በሚሉ አሳቦች ይፈትነናል::

ዕለቱን ዘርቶ ዕለቱን የሚያጭድ ገበሬ የለም:: ገበሬ በአንድ ዘመን ይዘራል፣ በሌላ ዘመን ያጭዳል:: ጸሎትም ዘር ነውና ዛሬ የጸለይነውን በሌላ ዘመን እናጭደዋለን:: ይልቁንም ስለ አገልግሎት የምናቀርበው ጸሎት በሌላ ትውልድ መከሩ ሊደርስ ይችላል:: እኛ የሌሎች ልመና ውጤት ነን:: የእኛም የጸሎት ልጆች ወደ ፊት አሉ:: ደግሞም ገበሬ ብዙ ከዘራ በረዶና አንበጣ ቢመጣ እንኳ ያተርፋል:: እኛም በጸሎት ብዙ ዘር መዝራት ይገባናል:: የትኛው እንደሚድን አናውቅምና:: ለማናውቃቸው አገሮችና ሰዎች በርእስ መጸለይ ይገባናል:: የትኛው እንደሚድን አናውቅምና:: ባሪያ ፈንጋይ የነበረ አንድ ሰው በወንጌል አምኖ ዳነ:: ሰዎችም «መንግሥተ ሰማያት ብትሄድ የሚደንቅህ ምንድነው?» ቢሉት «እዚያ አገኛቸዋለሁ የምላቸውን ሰዎች አለማግኘቴና እዚያ አላገኛቸውም የምላቸውን ሌባና ወንበዴዎች ማግኘቴ ነው:: ከሁሉ በላይ እኔ ራሴን እዚያ ስለማገኘው ይደንቀኛል» ብሏል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአገልግሎት ጸሎት ወሳኝ መሆኑን ከተናገረበት ክፍል ዋነኛው በማቴ. 12፥29 ላይ ያለው ነው:- *«ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል::»*



ኃይለኛ የተባለው ሰይጣን ነው:: ሰይጣን የሰውን ነጻ ፈቃድ እታሎ እስኪጥለው በሰው ላይ ኃይል የለውም:: ሰው ነጻ ፈቃዱን ለሰይጣን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ግን ሰይጣን በኃይል ይገዛዋል:: ሰዎችንም እውነትን እንዳያውቁና እንዳይረዱ አእምሮአቸውን በመጋረድ ይዋጋቸዋል:: አንዳንዶችን በደዌ በጭንቀት ያስራቸዋል:: ወንጌል የምንሰብክበት አንዱ ዓላማ በሰይጣን የድንቁርና ግዛት የሚኖሩትን ነጻ ለማውጣት ነው::

ሰይጣን የሚገዛቸውን ሰዎች በወኅኒ አጥሮ ይገዛቸዋል:: ስለዚህ እነዚህን ነፍሳት ነጻ ለማውጣት ወኅኒውን መስበር ያስፈልጋል:: ዓይኑ እያየ ወኅኒውን የሚያሰብር ጠባቂ በፍጹም የለም:: የአንድ ኃይለኛ ሰውን ቤት ለመዝረፍ አስቀድሞ ኃይለኛውን ማሠር ይገባል:: አሊያ ኃይለኛ ሰው ቤቱ ሲዘረፍ ዝም ብሎ አይመለከትም፣ ይጋደላል:: ሰውዬውን ካሠሩ ግን መበዝበዙ ቀላል ይሆናል:: እንዲሁም ሰይጣን ያሠራቸውን ሰዎች ለመፍታት አስቀድሞ ሰይጣንን ማሠር ይገባል:: ያን ጊዜ ቀጣዩ አገልግሎት ቀላል ይሆናል:: ሰይጣንን የምናስረው በጸሎት ነው::

ስለዚህ አገልጋዩ ከማገልገሉ በፊት በጸሎት ሰይጣንን ማሠር ይገባዋል:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአገልግሎት ወሳኝ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ጸሎት መሆኑን ተናግሯል:: የምድር አገልግሎቱን ፈጽሞ ሊያርግ ሲልም:- *«እነሆም፥ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ»* (ሉቃ. 24፥49) ብሏቸዋል:: የሚቆዩት ግን በጸሎት ነው:: ወታደር ከልምምድ በኋላ ይልቁንም ወደ ጦርነት ሲገባ ኃይል ይለብሳል:: በትከሻው በወገቡ መሣሪያውን ይታጠቃል:: ክርስቲያንም በጸሎት ኃይልን ለብሶ ሲወጣ ድልን ይጎናጸፋል:: የአገልጋይ ኃይል «ከላይ» ነው:: በምድራዊ ጥበብና ብልሃት ቢጠቀም እግዚአብሔርን ሊያስከብር አይችልም:: ደቀ መዛሙርቱም መንፈስ ቅዱስ እስኪወርድ በጸሎት ቆዩ (የሐዋ.ሥራ 1፥14):: መንፈስ ቅዱስም ወረደ:: የወረደውም መንፈስ የግላቸውን ድካም ወደ ብርታት ለወጠላቸው፣ ከሰዎች ጋር የሚገናኙበትን የቋንቋ ሀብት ሰጣቸው:: ደቀ መዛሙርቱም ዘወትር በጸሎት እየተጉ ይፈጥኑ ነበር::

አዎ አገልግሎታችን የጸሎት እስትንፋስ ያለው ሊሆን ይገባዋል:: ጸሎት የሌለበት ጉባዔ የሞት መንፈስ የተጫነው ነው:: ጸሎት የሌለበት አገልግሎት በድን ነው:: አገልጋዩ እንደ ሻማ እያለቀ ማገልገል የለበትም:: እየኖረ ማኖር አለበት:: የተጣለ እንዳይሆን በግሉ

ራሱን በጸሎትና በቃሉ ማበርታት ይገባዋል (1ቆሮ. 9፥27)፡፡ ይልቁንም በማማከር የሚያገለግል አገልጋይ በማያቋርጥ ጸሎት ውስጥ ሆኖ ማማከር ይገባዋል፡፡ አሊያ የሰዎች ፈተና ፈተና ሆኖ ይዋጋዋል፡፡ በርኅራኄም ውስጡ እየተጎዳ ይመጣል፡፡ ጭንቀታችንን አይደለም ኃጢአታችንንም በመስቀል ላይ ለተሸከመው ጌታ የሰማውን በጸሎት ካላሰማ ሸክሙ እርሱ ላይ ይወድቃል፡፡ የሚያማክረውንም ሰው ያለ ጸሎት ሊረዳው በፍጹም አይችልም፡፡ እያማከረ እያለም በማያቋርጥ ጸሎት ውስጥ ሆኖ «ጌታ ሆይ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ የምሰማውን ስማ» ብሎ ማስተላለፍ ይገባዋል፡፡ በጸሎቱ ጋሻ ካልተከላከልነው የምንሰማው ፈተና ፈተናችን ሆኖ ይዋጋናል፡፡



# ምዕራፍ ሰባት

# እምነት

*«ብዙ ሰዎች ብዙ ፈተና እንደ ደረሰባቸው ይናገራሉ፡፡ መጸለይ እንዳለመቻል ያለ ፈተና ግን የለም፡፡ ምክንያቱም ሌላ ፈተና ሁሉ ድል የሚነሣው በጸሎት መንገድ ነውና፡፡»*

ለመጸለይም መጸለይ ያስፈልጋል፡፡ መጸለይ የምንችለው እግዚአብሔር የጸሎትን መንፈስ ሲያፈስስልን ብቻ ነው፡፡ ጸሎት በሥጋ ኃይል የምናደርገው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት የምናከናውነው ነው፡፡ ለእስራኤል ልጆች ከቀረላቸው ተስፋ አንዱ በነቢዩ በዘካርያስ የተነገረው ነው፡፡ ተስፋው እንዲህ ይላል፡- *«በዳዊትም ቤት ላይ፥ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ፤ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ፤ ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፥ ሰውም ለበኵር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኀዘን ያዝኑለታል»* (ዘካ. 12፥10)፡፡

ብዙ ሰዎች ብዙ ፈተና እንደ ደረሰባቸው ይናገራሉ፡፡ መጸለይ እንዳለመቻል ያለ ፈተና ግን የለም፡፡ ምክንያቱም ሌላ ፈተና ሁሉ ድል የሚነሣው በጸሎት መንገድ ነውና፡፡ የእስራኤል ልጆች የቀረላቸው ተስፋ የልመና (የጸሎት) መንፈስ ነው፡፡ ትልቅ ተስፋ ነው፡፡ ከጸለዩ ምን ይቀርባቸዋል? የጎጃሙ ገዥ የነበሩት ራስ ኃይሉ ለማዕከላዊ መንግሥት የሚከፈል በጎጃም ሕዝብ ላይ አንድ አንድ ብር ግብር ጣሉ፡፡ አንዲት ደሃ ሴትም መጥታ እንዲያዝኑላት ብላ «ጌታዬ ይህችን አንድ ብር ያመጣሁት ውኃ ሸጬ ነው» ብትላቸው ራስ ኃይሉም «ተቀበላት ተቀበላት አንቺማ የያዝሽው የማያልቀውን ነው» አሉ ይባላል፡፡ የጸሎት ሰውም የያዘው የማያከስረውን ገበያ፣ የማይነጥፈውን በረከት ነው፡፡ በእውነት ለእስራኤል ቤት የቀረላቸው ተስፋ ትልቅ ተስፋ ነው፡፡

*«ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ፤»* ይላል፡፡ ጸሎት እግዚአብሔርን መመልከት ነው፡፡ ችግራችንን ሳይሆን እርሱን

መመልከት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ስንመለከት ተራራው ትንሽ ሆኖ ይታየናል፡፡ ይልቁንም ስለ ሰው ፍቅር በጦር የተወጋውን ጌታ ማየት የጸሎት ሕይወት ነው፡፡ አባቶቻችን በቅዳሴያቸው፡-

> *«ስለ እኔ በቀራንዮ የፈሰሰ ንጹሕ የሚሆን የመሢህም ደም እነሆ ስለ እኔ ይጮኻል፡፡ ይህ የሚናገር ደም የኔን የባርያህን ኃጢአት የሚያስተሰርይ ይሁን፡፡ ስለ እርሱም ልመናዬን ተቀበል፡፡ ወዳጅህ ስለ እኔ ጦርንና ቅንዋትን ተቀብሏልና ደስ ያሰኘህም ዘንድ ታመመ፡፡ ከዳንሁም በኋላ ሰይጣን ወደ ልቡናዬ ተመልሶ በፍላፆቹ ወጋኝ አቤቱ ምሕረትህን ስጠኝ ጽኑ ከሳሽ ነውና»*

በማለት የክርስቶስ ሕማምና ሞት የተዘጋው የጸሎት ደጅ የተከፈተበት መሆኑን ሲገልጡ ሞቱንም መማፀኛቸው አድርገዋል፡፡ እግዚአብሔር አብ በልጁ ሲያየን ተወዳጅ ልጆች ነን፡፡ እኛም በክርስቶስ እግዚአብሔር አብን ስናየው አፍቃሪ አባት ነው፡፡ ለእስራኤል ልጆች የተገባላቸው ተስፋ ታዲያ የሰቀሉትን ጌታ ማየትና የልመና መንፈስ ነው፡፡ ትልቅ ተስፋ ትልቅ በረከት ነው፡፡ የጸሎትን መቅጃ የያዙ ከማያልቅ ምንጭ የተጎራበቱ ናቸው፡፡

ጸሎት ከጅምር እስከ ፍጻሜው እግዚአብሔር እኛን በጸጋ የሚባርክበት መሆኑን ሳንጠቅስ አናልፍም፡፡ ስለዚህ፡-

- ስለ ታማኝነታችን ሳይሆን ስለ ተስፋ ቃሉ፣
- ስለ ፈቃዳችን ሳይሆን ስለ ፈቃዱ፣
- ስለ ልመና እውቀታችን ሳይሆን ስለ አባትነቱ፣
- ስለ ማንነታችን ሳይሆን ስለ ይቅርታው፣
- ስለ ትልቅነታችን ሳይሆን ስለ ስሙ መልካምን የሚያደርግልን እግዚአብሔር ነው፡፡

ጸሎት ከጸጋ መንገዶች አንዱ ነው፡፡ የጸጋ መንገድ ደካማውም ሲፈጽመው የሚችል ዓይንን ብቻ ገልጦ ማየት የሚጠይቅ ነው፡፡ በረሀብ የደከሙ ሰዎች ይለምናሉ፡፡ የልመና እቅም አላቸው ነገር ግን የመታገል አቅም የላቸውም፡፡ ክፈሉኝ ሳይሆን በነጻ ስጉኝ ይላሉ፡፡ «ከእኔም ይከፍላል ብላችሁ አትጠብቁ፡፡ ብድር ለመመለስ አቅምም አሳብም የለኝም ግን ራበኝ» የሚሉ ይመስላሉ፡፡ አቅም ያጡ ሰዎች የመለመን አቅማቸው ሳያልቅ ይለምናሉ፡፡ ምላሻቸውም ምስጋና ብቻ ነው፡፡ ጸሎትም እንዲሁ ቀላልና የጸጋ መንገድ ነው፡፡



ጸሎታችን ተወዳጅ፣ ልመናችን ግዳጅ ፈጻሚ፣ መሥዋዕታችንም የሠመረ እንዲሆን ልንፈጽማቸው የሚገቡ የጸጋ መንገዶች አሉ፡፡ ምነው ጸሎት የስጦታው መንገድ ነው ብለን የለም ወይ? ቢባል አዎ ጸሎት የስጦታው መንገድ ነው፡፡ ስጦታን ግን ለመቀበል ፈቃደኝነት፣ የተዘረጋ እጅ፣ ባዶ ማድጋ፣ ንጹሕ ማሰሮ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ የፈቃደኝነታችንና የዝግጅት መንገዶቻችን፡-

1. እምነት፤
2. እንደ ፈቃዱ መጸለይ፤
3. በስሙ መጸለይ፤
4. ኃጢአታችንን መናዘዝ፤
5. የምንለምነውን ማወቅ፤
6. ትዕግሥት ናቸው፡፡

## እምነት

ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የምናደርገው በእምነት መስመር ነው፡፡ የለመነውን እንደማይነሳን የነገርነውን እንደማይረሳብን በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም እምነት ሲኖረን በጸሎት ኃይል መጠቀም እንችላለን፡፡ የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት፣ ከደዌ ለመፈወስ፣ በቅድስና ለመኖር፣ በመከራ ለመጽናት፣ ዓለምን ለማሸነፍ፣ ተራራን ለመደልደል፣ ... እምነት ያስፈልጋል፡፡ ያለ እምነት ብዙ ነገሮችን ብናከናውን እንኳ እግዚአብሔር ደስ አይሰውም፡፡ *«ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ይገባዋልና»* (ዕብ. 11፥6)፡፡

ከአንድ ሰው ጋር ለመነጋገርና ለመግባባት መጀመሪያ በሰውዬው ላይ እምነት ያስፈልገናል፡፡ ያለ እምነት የምንነጋገር ከሆነ እንኳን ልንግባባ ልንደማመጥ አንችልም፡፡ እንዲሁም ከሰማያዊ አባት ጋር በጸሎት የሚነጋገረው ሰው ጸሎቱ ተሰሚ፣ መሥዋዕቱ ግዳጅ ፈጻሚ እንዲሆን እምነት ያስፈልገዋል፡፡ *«ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና፡፡ ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው»* (ያዕ. 1፥6-8)፡፡

እንድንለምን ያዘዘን እግዚአብሔር ነው፡፡ *«ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያ አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል»* (ማቴ.

7፥7) ያሰን ራሱ ጌታችን ነው። ለምኑ ያለ አምላክ ላይሰጥ አያለፋም፣ እሹ ያለ አምላክ በምኞት ሲያቃጥለን አይደለም። አንኳኩ ያለን እጃችንን ለመላጥ አይደለም። ሊሰጠን ነው። ስለዚህ በእምነት መጸለይ ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር ባያደርግልን እንኳ እኛን በጽሞና ማዳመጡ ያስደስታል። የሰማይ የምድር ንጉሥ የሚሰማን ከሆነ እንዴት የታደልን ነን? በዓለም ላይ የተበደለ ሰው ቢኖር በጸሎት ከጌታው ጋር ማውራትን ያልተለማመደ ሰው ነው። እግዚአብሔር ማድመጥ ብቻ አይደለም። የለመነውን ይሰጣል። ስለዚህ በእምነት መጸለይ ያስፈልገናል። ስጦታውን የምንቀበለው በእምነት እጅ ነው። ያለ እምነት መቀበል አንችልም።

በአንድ አገር ላይ ዝናብ ጠፍቶ ጽኑ ድርቅ ሆነ። የአገሩም ሰዎች የዝናቡን ጌታ ለመለመን የጸሎትና የእግዚኦታ መርሐ ግብር አወጡ። አንዲት ሴትም ወደ ምህላው ስፍራ ለመሄድ ስትሰናዳ ልጅዋ ወዴት ነው የምንሄደው? አለቻት። እግዚአብሔር ዝናብ እንዲሰጠን ለመጸለይ ነው አለቻት። ልጂቱም ታዲያ ጥላ እንያዝ አለቻት። እናትም ጥላ ምን ያደርጋል? ብትላት እግዚአብሔርን ለምነን ዝናብ ስለሚሰጠን ዝናቡ እንዳይመታን ነው አለች። እናቲቱ ግን የልጅዋን እምነት ማስተዋል አልቻለችም። ጸልየው ሲፈጽሙ ድንገተኛ ደመና መጣ። በዝናብ እየራሱም ወደ ቤታቸው ገቡ። እግዚአብሔር ዝናብን የሰጠው እንደምትቀበል አምና የወጣችውን የዚያችን ልጅ እምነት አይቶ ነው።

እግዚአብሔር እንደ ሕፃናት ያለ እምነት እንዲኖረን ይፈልጋል። ፍጹም እንድናምነው እንድንደገፈው ይፈልጋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነት ወደ እርሱ የመጡትን ሲፈውስ፣ ባለማመናቸው ምክንያት ደግሞ ተአምራት ለማድረግ ሲቸገር በወንጌል እናነባለን። ስለ እምነትም የተናገረባቸውን ክፍሎች ብንመለከት አስደናቂ መልእክቶችን እናገኛለን።

ደቀ መዛሙርቱ ሊፈውሱት ስላቃታቸው በሽተኛ ምክንያቱ ምን እንደ ሆነ ሊጠይቁት *«ኢየሱስም፡- ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ፡- ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም»* (ማቴ. 17፥23) ብሏቸዋል። ሰናፍጭ ሙሉ አካሏ እንኳ ደቃቃ ነው። የሰናፍጭ ቅንጣት ደግሞ ለዓይን የማይታይ ረቂቅ ነው። እጅግም ትንሽ ነው። የተወዳደረው ግን የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል



እምነት ከትልቅ ተራራ ጋር ነው። ይህ ምን ማለት ነው? ትልቅ ችግር በትንሽ እምነት ይሸነፋል ማለት ነው።

ወደ ጦር ሜዳ የሚዘምት ወታደር «እናሸንፋለን» እያለ ነው የሚዘምተው። የሚዘምተው ድልን ይዞ ነው። ገና ድል ለማድረግ ቢሆን የሚዘምተው በጥርጣሬ ፍርሃትን፣ በፍርሃት ሽንፈትን ያስተናግዳል። የሚጸልይ ምእመንም በእምነት «ይህን ሲያደርግ እግዚአብሔር ይችላል፣ በቃሉም ታማኝ ነው» ብሎ መለመን ይገባዋል። ከፊት ለፊታችን እንደ ተራራ የሚጋረጡትን ነገሮች የምናሸንፈው በእምነት ነው። በነቢዩ በዘካርያስ፡- *«ታላቅ ተራራ ሆይ፥ አንተ ምንድርነህ? በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ፤»* (ዘካ. 4፥7) በማለት የእምነት ሰው ስለ ነበረው ስለ ዘሩባቤል ተነግሯል። በእምነት ሰው ፊት ከባዱ ይቀልላል። አስቸጋሪው ነገር መንገድ ይሆናል። ዓይናችን የሚታየውን ያያል፣ እምነት ግን የማይታየውን ያያል። ዓይናችን ተራራውን ሲያይ እምነት ግን ከተራራው በስተጀርባ ያለውን ያያል።

*ዳግመኛም* ጌታችን ስለ እምነት ጸሎት የተናገረው በማቴ. 21፥22 ላይ ነው፡- *«አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ»* ብሏል። የምንለምነውን የምንቀበለው በእምነት እጅ ነው። ልብ ልንል የሚገባው ሌላው ነገር ግን አምነን መጸለይ ይገባናል እንጂ በጸሎታችን ማመን የለብንም። *«አምናችሁም በጸሎት ...።»* ብዙ ሰዎች የእኔ ጸሎት ጠብ አትልም ይላሉ። የእግዚአብሔርን ቸርነት አስበው ከሆነ መልካም ነው። በግል ጸሎታቸው ተመክተው ከሆነ ግን ስህተት ነው። በሚሰጥ እግዚአብሔር አምነን እንድንጸልይ እንጂ በጸሎታችን እንድናምን አልተፈቀደም። በጸሎታቸው የሚያምኑ ሰዎች እነርሱ በሰላም የሚኖሩት በጸሎታቸው፣ ሌሎች የሚታወኩት ባለ መጸለያቸው እንደሆነ ያስባሉ። ሁሉን የሚያኖረውን ቸርነቱን ይረሳሉ። ጸሎታቸውንም የተጋድሎ የግብ ግብ ጉዳይ ያደርጉታል። ስለዚህ ጸሎታቸው የመጣውን ፈተና ከመመለስ አዲስ መከራ የሚጎትት ይሆናል። ሱባዔ መልካም ቢሆንም ለብዙ ክርስቲያኖች ግን ከሰይጣን ጋር ለመጋደል ቀጠሮ የሚይዙበት እንጂ የእግዚአብሔርን የፍቅር ፀሐይ የሚሞቁበት አለመሆኑ ያሳዝናል። ቃሉን አስተውሉ፡- *«አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ»* (ማቴ. 21፥22)።

ልጁ የታመመበት አንድ ሰው ወደ ጌታችን መጥቶ እንዲያድንለት ሲለምነው *«ቢቻልህ ግን እዘንልን እርዳንም»* አለው። ጌታችን *«ቢቻልህ ትላለህ፤ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል»* አለው።

ወዲያውም የብላቴናው አባት ጮኸ:- *«አምናለሁ፤ አለማመኔን እርዳው»* አለ (ማር. 9፥24):: ጌታም ልጁን አዳነለት::

ይህ ሰው ወደ ጌታ የመጣው ለሙከራ ነው:: ልጄ ከዳነልኝ ጥሩ ነው ካልሆነም ፈተናዬ ነው ብዬ ተሸክሜ እኖራለሁ በሚል ስሜት ነው የመጣው:: ጌታን ቢቻልህ ሲለው የሰጠው ምላሽ እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚችል ነገር ግን አለማመናችን እንዳይሠራ እንደሚገድበው ነገረው:: የብላቴናው አባትም በሐቀኝነት ልቡን ሲያዳምጥ የተከፈለ እምነት አገኘ፣ በራሱ ሊገጥመውና ሊያቀመው አልቻለም:: አምኖ ግን የእምነትን በረከት ይዞ ለመግባት ወስኗል:: የእርሱ እምነት በልጁ ዕጣ ላይ ‚ወሳኝ ነበር:: በዚያን ጊዜ *«አምናለሁ አለማመኔን እርዳው»* አለ:: ይህ ሰው የተናገረው ንግግር አስደናቂ ነው:- «አምናለሁ ደግሞም አላምንም አንተ የእምነት አቅሜን እርዳው» የሚል ምላሽ ነው:: ንግግሩን በአድማጭ ቃል ብንለውጠው:- «ጌታ ሆይ እንደምትችል አምናለሁ ግን ልቤን ሳዳምጠው እንደ አፌ አይደለም:: እንዳምንህ እርዳኝና እባክህ ልመንህ» የሚል ሆኖ እናገኘዋለን:: ጌታ ከዚህ ሰው ጋር ምንም ዓይነት ክርክር አላደረገም፣ ወዲያው ልጁን ፈወሰለት:: ሰውዬው በትክክል አምኗል:: እምነት የእግዚአብሔርን መቻል ብቻ ሳይሆን የራስንም ድካም ማመን ነውና:: ዛሬም የእምነት አቅም ሲያንሰን «የእምነት ሰው አድርገኝ» ብለን መጸለይ ይገባናል:: እግዚአብሔር እምነትን ይሰጠናል::

እምነት ተስፋ አይደለም:: ብዙ ሰዎች በተስፋ ይጸልያሉ:: ተስፋ ይሆናል ይፈጸማል የሚል አስተሳሰብ ነው:: እምነት ግን ሆኗል ተፈጽሟል ብሎ ማረፍ ነው:: ተስፋ ነገ ከነገ ወዲያ ነው፣ እምነት ግን አሁን ነው:: ስለዚህ የታዘዝነው በእምነት እንድንጸልይ እንጂ በተስፋ እንድንጸልይ አይደለም::

ሐና መጠቃቷን፣ መዋረዷን፣ ብሶቷን ለእግዚአብሔር እስክትነግር መጽናናትን ጠላች:: በእግዚአብሔር ፊት ዕንባዋን ካፈሰሰች በኋላ ግን *«ፊትዋም ከእንግዲህ ወዲያ አዘንተኛ መስሎ አልታየም»* (1ሳሙ. 1፥18) ይላል:: እግዚአብሔር የጣለችበትን ጉዳይ ሠራውና ሳሙኤልን ልጅ አድርጎ ሰጣት:: ማዘን ማልቀስ ለእግዚአብሔር እስክንነግር ነው:: ለእርሱ ከነገርን በኋላ ግን ፋይል የተከፈተለት ጉዳይ ነውና በቀኑ ይፈርድበታል:: በምንም መንገድ ጉዳያችን ከመጸለያችን በፊት እንደ ነበረው አይሆንም:: እግዚአብሔር የሰማው ጉዳይ በቁጥጥር ሥር የዋለ ጉዳይ ነው:: የባሰ እየተበላሸ ቢመጣ እንኳ ዋስትና ስላለን መፍራት አይገባንም:: እርሱ የሥጋና የነፍስ ፈጣሪ በመሆኑ ለሥጋና ለነፍስ ጉዳያችን መልስ አለው:: የሥጋው ለእኛ የተተወ አድርገን መመልከት አይገባንም::



# <u>ምዕራፍ ስምንት</u>

## <u>እንደ ፈቃዱ መጸለይ</u>

*«ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊሰጠንም ሆነ ሊወስድብን የሚችል ምንም ነገር የለምና ፈቃድህ ይሁን ብለን ለመጸለይ መፍራት የለብንም::»*

አንድ የመንዝ ገበሬ የሚስቱን ዘመዶች ለመጠየቅ ከሚስቱ ጋር ወደ ቆላ ወረደ:: በዚያም አማቾቹን ጠይቆ እንደ ነገ ሊመለስ አሰበ:: ባለቤቱንም:- «የቆላው መንገድ በማለዳ ካልሆነ አይገፋምና ልክ ዶሮ እንደ ጮኸ ተነሥተን ጉዞ እንጀምራለን» ብሏት ይተኛል:: ዶሮ በመጀመሪያ እንደ ጮኸ ባለቤቱን:- «በይ ደጅ ወጥቼ እስክመጣ ተነሥተሽ ቆይኝ» ይልና ይነሣል:: ደጅ ደርሶ ሲመጣ «አልተነሣሽም ወይ? በይ አህያውን እስክጭን ተነሺ» ይላትና ይወጣል:: አህያውን ጭኖ ሲመለስ አሁንም አልነቃችም:: «ምን ሆነሽ ነው ፀሐይ ሊወጣ ነው ተነሺ እንጂ» ቢላት ዝም አለችው:: ቢቀሰቅሳት አልሰማ አለችው:: ገልጦ ቢያያት ቀዝቅዛለች:: መሞቷን አውቆ ኡኡ ቢል ዙሪያው ዘመዶቿ ናቸውና ሁሉም እየጮሁ ተሰባሰቡ:: ሁሉም መሰባሰባቸውን ሲያይ አህያው በተጠንቀቅ ለጉዞ ተዘጋጅታ ነበርና:-

*«ባሰበችው ቀርቶ ባሰበው ካዋላት፣*
*እኔ መሄዴ ነው እናንተ ቅበሯት!»*

ብሎ አህያውን እየነዳ ወደ አገሩ ገባ ይባላል:: የእርሷ አሳብ እቤቴ ገብቼ በረቴን አጽድቼ፣ የእገሌን እዝን ወስጄ . . . የሚል ነበር:: የእግዚአብሔር አሳብ ግን የምድር ሩጫዋን እንድትፈጽምና ዛሬ በደጋ ሳይሆን በሰማይ እንድትውል ሆነ:: የሰው ውሎውም ሆነ ኑሮው እንዳሰበው ሳይሆን እንደ ታሰበለት ነው:: ይህ እውነት የገባው አዋቂው ገበሬ ሞትም አልደነቀውም:: ፈቃዱ ሲገባን ደስታችንን የሚቀማን ኃይል አይኖርም::

በጎንደር ዘመነ መንግሥት የተፈፀመ አንድ ታሪክ አለ:: በነጋሢያን ታሪክ ውስጥ እንደ ተለመደው አልጋ ወራሹ ዙፋኑን ሲይዝ ወንድሞቹ እንዳይቀናቀኑት ስለሚፈራ ማሰር የተለመደ ነበር::

ለምን? ቢሉ ሕዝቡ ከንጉሡ ልጆች አንዱን ይዞ ማንገሥ ስለሚችል ነው:: በአምባ ማርያም ከታሰሩት የንጉሥ ልጆች የመጨረሻው ልጅ በቅጽል ስሙ «ዘዋህድ እዴሁ» ወይም አንድ እጁ ዮሐንስ የሚባለው ነበር:: ዮሐንስ ትንሽ ቢሆንም እእምሮው ግን ከነገሠው ወንድሙ ይልቅ ብሩህ ነበርና ሕዝቡ ታላቁን ትቶ ታናሹን ነበር ማንገሥ እያለ ሲያጉረመርም ንጉሡ ዮሐንስን በቅንአት ጠላው:: የሕዝቡም ማጉረምረም እየበዛ ሲሄድ በሌሊት አምባ ድረስ ሄዶ ዮሐንስን አስጠርቶ ቀኝ እጁን ቆረጠው:: አሳቡ ንጉሣዊውን ዘንግ (ሀለተ ወርቁን) የማይዝ አካለ ጐዶሎ አይነግሥም ብሎ ነው:: እንደ ባሕሉ ትክክል ነው:: ዮሐንስም በዚህ ምክንያት ዘዋህድ እዴሁ (አንድ እጁ) ተባለ:: ሕዝቡም በዮሐንስ ላይ የተሠራውን ክፋት ሲሰማ «በእእምሮው እንጂ በእጁ አይገዛን» ብሎ ያለ ጊዜው ቁጣው ተቀሰቀሰ:: ወንድሙንም አውርዶ ዮሐንስ ዘዋህድ እዴሁን አነገሠው:: ዮሐንስም የተቀባው በአእላፋት መላእክት በዓል ዕለት በህዳር 13 ቀን ነው:: ዮሐንስም በንግሥናው ቀን እንዲህ የሚል ቅኔ አቀረበ:-

*«ሕእላፈ ሕመመከሩ ለእላፍ፣*
*አንተ ዘሀለይከ ወዘወሰንከ ኢይተርፍ!»*

ትርጓሜው:-

*«ዐሥር ሺህ ሰው ተሰብስቦ፣*
*ዐሥር ሺህ ምክር ቢመክር!*
*አንተ ያሰብከውና የወሰንከው አይቀርም»*

ማለት ነው:: ዘዋህድ እዴሁ ዮሐንስ:- «ወንድሜ እንደ ባሕሉ ትክክል ነበር:: ጌታዬ ግን ከባሕሉም ከሕጉም በላይ ነው:: የሰው ብዙ ምክር አይጸናም:: የእግዚአብሔር አሳብ ግን ይሆናል» ብሎ ማመስገኑ ነው:: የእጅ መቆረጥ የእግዚአብሔርን አሳብ አያግደውም:: ባሕልና ሕግም እግዚአብሔርን አይዘውም:: በገባያን ፀሐይን ለአንድ ቀን ያዘገየ ጌታ ከተፈጥሮ ሕግም በላይ ነው:: የዐፄ ዮሐንስ ዘዋህድ እዴሁን ታሪክ ሳስብ ልቤ ይነካል:: ሰው የሚያዳምጠው ሁልጊዜ የራሱን ምኞት ነው:: የእግዚአብሔርን አሳብ አያውቅም:: ከላይ የጠቀስናቸው ሁለት ታሪኮች የሰው አሳብና የእግዚአብሔር አሳብ እንደሚለያይ ሲገልጡ የእግዚአብሔር አሳብም በመጨረሻ እንደሚያሸንፍ ያሳያሉ:: እዎ ለጸሎታችንም ፈቃዱን ማወቅ አስፈላጊ ነው::

ታላላቅ ውሳኔዎች በእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈጽመዋል:: የሰማይና የምድር መፈጠር፣ ሰውን ለማዳን የተደረገው አምላካዊ ጉዞ፣ የፍጥረትና የታሪክ ምዕራፍ የሚያበቃበት የዓለም ፍጻሜ ፈቃዱ የእግዚአብሔር ነው:: ሰው ሆነን መፈጠራችን፣ ራሳችንን በተፈጥሮ



ያገኘንበት አገርና ቤተሰብ፣ የቆዳችን ቀለምና የፊታችን አቀማመጥ፣ የዕድሜያችን ስፍርና ገደብ ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ተጠቅልለዋል:: እነዚህን ታላላቅ ውሳኔዎች ስንመለከት በራሳችን ላይ ካለን ሥልጣን እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያደረገውና የሚያደርገው ሥልጣንና ፈቃድ እንደሚበልጥ እንረዳለን::

ታላላቅ ውሳኔዎች በእግዚአብሔር ተወስነው ፈቃዱ ተስማምቶን ከተቀመጥን ለዕለታዊ ፍላጎታችንና መጥቶም ለማይሞላው ጉዳያችን፣ ሆኖም ለማያረካው ጭንቃችን «ፈቃድህ ይሁን» ማለት በእውነት ተገቢ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረው የአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት ላይ *«ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን»* (ማቴ. 6፥10) ብለን እንድንጸልይ አስተምሮናል:: ጸሎታችን የእኛ ፈቃድ በሰማይ እንዲሆን የምንጥርበት ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር ላይ እንዲሆን ስፍራ የምንለቅበት ነው:: ሰማይ የእግዚአብሔር ፈቃድ የጸናባት መንፈሳዊት አገር ናት:: ስለዚህ ብርሃኗ አይጨልምም፤ ዘመኗ አይፈጸምም:: እንዲሁም የሰማይ ደስታ ወደ ምድር እንዲመጣ የምንፈልግ ከሆነ ፈቃዱን መጠየቅና መቀበል አለብን:: ጥያቄ የሌለበት ኑሮ መኖር የምንችለው እንደ ፈቃዱ ስንኖር ነው:: «ፈቃድህ ይሁን» ብለን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለምን እንጠይቃለን? ስንል የሚከተሉትን ነጥቦች እናገኛለን::

## 1. <u>እግዚአብሔር የራሱ ፈቃድ ያለው አምላክ ስለሆነ</u>

የምናመልከው የፈጠርነውን ጣኦት ሳይሆን የፈጠረንን እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ፈቃድ ያለው እኔ ባይ አምላክ ነው:: ጸሎታችን የመልካምነታችን ደሞዝ ሳይሆን እግዚአብሔር በጸጋውና በፈቃዱ ለእኛ ሊያደርግልን ያሰበውን እንዲያደርግልን መጠየቂያ ነው:: ባለቤቱን ሳያስፈቅድ የሚወስድ ሌባ ብቻ ነው:: ማንኛውም ልክኛ ሰው ባለቤቱን ያስፈቅዳል:: ፈቃድ ሲጠየቅ ባለቤቱ በደስታ ይሰጣል:: ተቀባዩም እርግጠኝነት ይሰማዋል:: እንዲሁም እግዚአብሔርን ስንለምን ፈቃዱን መጠየቅ ይገባናል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ፈቃድ ያለው አምላክ ነውና:: የእርሱ ፈቃድ ያለበት ነገር ሁሉ ደስታና ዋስትና አለው:: እኛ ግን ብዙ ጊዜ ጸሎታችንን የምንጠቀምበት የምንፈልገውን በዝርዝር ከመዘገብን በኋላ ጌታ ሆይ መጨረሻዋ ላይ ሳታነብ ፈርም የምንልበት ይመስላል:: የምናስበው እኛ የመጻሰይ ድርሻችንን ከተወጣን እግዚአብሔር የመፈጸም ግዴታ አለበት ብለን ነው:: እግዚአብሔር ፈቃድ ያለው

አምላክ ነው። ራሳችን ለራሳችን ለማድረግ እንኳ ራሳችንን እናስፈቅዳለን። ታዲያ ፈቅዶ የፈጠረንን አምላክና ፈቅዶ ያኖረንን ጌታ ፈቃድህ ይሁን ማለት በጣም ተገቢ አይደለምን? በሕጻንነት እእምሮዬና ዕድሜዬ ከሰዎች ጋር ስንቀጣጠር «እግዚአብሔር ከፈቀደ» ካሉኝ የተጠራጠሩና ለመቅረት ያሰቡ ይመስለኝ ነበር። ለካ እንደ እኛ እናስባለን እንደ እርሱ ፈቃድ ይፈጸማል! ተቀጣጥረን አለመገናኘት ተገናኝተን መጣላት እንዳለ ስረዳ እነዚያ ሰዎች በመኖር እንደ ቀደሙኝ ተረድቻለሁ። የያዕቆብ መልእክት እንዲህ ይላል፡- *«አሁንም፡- ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ፥ ተመልከቱ፥ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና። ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁና። በዚህ ፈንታ፡- ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል»* (ያዕ. 4፥13-15)።

በእውነት መስጠትና መንሣት የእግዚአብሔር የመንግሥቱ ብቸኛ ሥልጣን በመሆኑ ፈቃድህ ይሁን ብለን መጸለይ ይገባናል። ጸሎታችን እግዚአብሔርን ከእኛ ፈቃድ ጋር የምናስማማበት አይደለም። ጸሎታችን ለእግዚአብሔር ፍርድ አስተማሪ፣ ቅጣት ለንዛሪ አይደለም። ጸሎት የእግዚአብሔር የፈቃዱ አገልጋይ ወይም ታዛዥ ነው።

## 2. ለእኛ መልካም አባት ስለሆነ

እግዚአብሔር ለእኛ የሚያስብ ቸር አባት ነው። በነቢዩ በኤርምያስ፡- *«ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም»* (ኤር. 29፥11) ይላል። ወዳጆች በጊዜያዊ ፍቅር ስክረው ለእኛ መልካም ነገር ያስባሉ። ይህ ጊዜያዊ ስሜታቸው ነው። አባት ግን ዕዳው የእኔ ነው ደግሞም የምለፋው ስልጄ ነው በማለት ፍጻሜ ያለው አሳብ ያስባል። እግዚአብሔርም እንደ አባት ያስብልናል። ስለዚህ ለእኛ ለመስጠት ፈቃድም ኃይልም ያለውን አባት ፈቃድህ ይሁን ማለት ተገቢ ነው።

ጸሎታችን ጥያቄአችን እንጂ የእኛ የመጨረሻው ውሳኔያችን ሊሆን አይገባውም። ለእኛ የመጨረሻ መልካም የመሰለን ሁሉን በሚያውቅ በእግዚአብሔር ዘንድ የመጨረሻው ስህተት ሊሆን ይችላል። ጸሎታችን ከጠቢባን ጠቢብ ጋር የምንመካከርበት እንጂ



እግዚአብሔርን አስጨንቀን የምንነጥቅበት አይደለም። የምክር አገልግሎት በምንሰጥበት ጊዜ የምናማክረው የራሱን ውሳኔ ይዞ ያልመጣን ሰው ነው። ብዙ ሰዎች በነገሩ ላይ ወስነው አማክሩን ይላሉ። ሰዎቹ ግን የፈለጉት ምክር ሳይሆን ውሳኔያቸውን የሚያጸድቅላቸው ወይም የድጋፍ ድምፅ ነው። ስለዚህ እነዚህን ሰዎች ማማከር ከባድ ይሆንብናል። መጽሐፍ፡- *«በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ»* (ምሳ. 3፥5) ይላል። ስለዚህ ጸሎተኛው ፈቃድህ ይሁን ማለት አለበት እንጂ ለእኔ የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ፣ የእግዚአብሔር ድርሻ የጠየቅሁትን መስጠት ነው ብሎ ማሰብ የለበትም። ለራሳችን ያወቅን መስሎን ካልሆነልኝ ከምንለው፣ ሰዎችም አውቀውልን እንዲህ በሆነላችሁ ከሚሉን ሁሉ እግዚአብሔር ያወቀልን እርሱ ይሻለናል። ወላጆች ልጆች የጠየቁቸውን ሁሉ አይሰጡም። የወላጅነታቸውን ፈቃድ ያዳምጣሉ። የልጆች ጥያቄ፡-

- አንዳንዱ ፍጹም ምላሽ የማይሰጠው ነው።
- አንዳንዱ የጊዜ ቆይታ የሚፈልግ ነው።
- አንዳንዱ አሁን የሚመለስ ነው።

እግዚአብሔርም የልጆቹን ልመና፡-

- አይሆንም፣
- ታገሥ፣
- ይሰጥሃል በሚሉ ሦስት ውሳኔዎች ይመል ሳል።

## 3. በእግዚአብሔር ዓይን ጉዳያችንን ለማየት

እኛ ስላለፈው እንጂ ስለሚመጣው አናውቅም። እግዚአብሔር ግን ኃላፊያትን ብቻ ሳይሆን መጻያትንም ያውቃል። «እንደ ፈቃድህ» ስንል «ጌታ ሆይ እኔ አይታየኝም እዚያ ማዶ የማየው እውነተኛው ሙዝ ነው ወይስ የፕላስቲክ ሙዝ ነው? እባክህ እይልኝ» ማለት ነው። በአንድ ምሽት አንድ ዓይነ- ሥውር መኪና በበዛበት መሻገሪያ ላይ ቆሞ «ወገኖቼ እባካችሁ ዓይን አውሱኝ» እያለ የሚያሻግረው ሰው ለመነ። በዚህ ምሳሌ «ፈቃድህ ይሁን» ማለት ይልቁንም ዛሬ «ዘመኑ ጨለማ ነው አይታየኝም፤ የእውነት መመዘኛ ጠፍቷል። ጨለማው ብርሃን፣ ብርሃኑ ጨለማ ሆኗል፤ ነውሩ ክብር፣

ክብሩ ነውር ሆኗል። እባክህ ጌታዬ እንድሻገረው ዓይን አውሰኝ» ማለት ነው።

ዛሬ ላይ ቆሜ ሳስበው እግዚአብሔር የለመንኩትን ሁሉ ቢሰጠኝ ኖሮ ይህን ጊዜ በሕይወት እንደማልቆይ ተረድቻለሁ። በጊዜው ግን ስላላገኘሁ አዝኛለሁ። ልጆች ያደጉ መስሏቸው ወላጆቻቸውን ድርሻዬን ስጡኝ ይላሉ። ወላጆች ግን ለንብረቱ ሳይሆን ለልጆቻቸው አዝነው እምቢ ይላሉ። እምቢ መልስ፣ እምቢ ርኅራኄም ነው። ይህ የሚገባን ግን በአእምሮ ስንጎለምስ ነው።

## 4. *ለእኛ የሚሆነውን እርሱ ስለሚያውቅ*

ሰው ለሰው መምረጥ ቢችልም ሰው ግን ለራሱ መምረጥ ፍጹም አይችልም። እግዚአብሔርን ገሸሽ ብለን የመረጥነው ትዳር በአጭር ርቀት የዋሻ ጉዞ ሆኖ ረዝሞብናል። ቁመናቸውን እያየን የመረጥናቸው፣ በአለባበሳቸውና በቋንጣቸው ተማርከን ያሳደድናቸው ሳማ ሆነውብን እየለበለቡን ነው። ዋናው ዘመኑን መምሰል ነው ብለን የገባንበት ሰፊው የፖለቲካ በር መውጫው ጠባብ ሆኖብን ከአሳብ ጋር እንደሚበሉት ምግብ ትንታ የበዛበት ሆኗል። ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም ብለን ደፍረን የሠራነው ኃጢአት በአደባባይ አስፈርዶብን ወኅኒ ጥሎናል። ከአገሬ ያውጣኝ እንጂ ኢትዮጵያ ከምጸድቅ አሜሪካ ብኮነን ይሻለኛል ብለን ወጥተን የባዕድ አገር አንገሽግሾናል። እንደ ብረት ምድጃ የሚያቃጥሉን ነገሮች በአብዛኛው የምርጫችን ብልሽቶች ናቸው። «ፈቃድህ ይሁን» ብለን ስንጸልይ፦

> *«ጌታ ሆይ ዓሣ ያዝኩ ብዬ እባብ ጨብጫለሁ፣ ዳቦ አነሣሁ ብዬ ድንጋይ አንስቻለሁ። ለራሴ መምረጥ አላውቅም። የነገሮች ዳሩ እንጂ ፍጻሜው አይታየኝም። ድንበሩ እንጂ ግዛቱ ለእኔ ስውር ነው። ሁሉን የምታይ ሁሉን የምታውቅ አምላኬ ፈቃድህ ከሆነ ስጠኝ። ካልሆነ ከልክለኝ። እምቢ ብዬ ባስቸግርህ እንኳ በፍቅር ቅጣኝ እንጂ ለፈቃዴ አሳልፈህ አትስጠኝ»* ማለታችን ነው።

ወላጆች ልጆቻቸው በፈንጂ ኳስ ሲጫወቱ ቢያዩ ፈጥነው ይቀሟቸዋል። ልጆቹ ቢያለቅሱ ወላጆች ለማባበል እንኳ ጊዜ የላቸውም። እኛም በሞት የምንጫወት ልጆች ነንና ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በመከልከል የሰጠንንም በመንሣት ዕድሜያችንን ያስረዝመዋል።



የእግዚአብሔር ፈቃድ የፍላጎታችን ተቃራኒና ተቀናቃኝ የሚመስለን ጊዜ ብዙ ነው። ፈቃድህ ይሁን ማለት አሁን የምጠይቅህን አትስጠኝ ማለት ይመስለናል። ነገር ግን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚሰጠንም ሆነ የሚወስድብን ምንም ነገር የለም። ስለዚህ «ፈቃድህ ይሁን» ብለን መጽናናትና መጽናት ይገባናል። የራሴን የሕይወት ልምዶች ሳገላብጥ አሁን አሁን ፈቃዱ ያልሆነ ነገርን እንዳልለምን መፍራት ጀምሬአለሁ። የእስራኤል ልጆች ከእግዚአብሔር በላይ የመሰላቸውን ሥጋ አገኙ። በአፋቸው ውስጥ ሲገባ ግን ሞቱ። የሻቱት ተገኘ ግን ገዳይ ነበረ (መዝ. 77፥29-31)። ሌሎችም በአቋራጭ እግዚአብሔርን ለመቅደም ይሞክራሉ።

እግዚአብሔር ለአብርሃም በ85 ዓመቱ የልጅ ተስፋን ሰጠው። አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነና ተስፋውን መጠበቅ ጀመረ። 85 ዓመት የጠበቀ ሰው ተስፋው ከተሰጠ ዓመት ሳይሞላው ልቡ ደከመ። ሣራም ብልሃቷን አቀረበችለት። ገረዶን ልስጥህና ከእርሷ ውለድ አለችው። አጋርን ያስማመናቸውና የጭካኔያቸው መሣሪያ አደረጓት። አጋርም ከአብርሃም እስማኤልን ወለደች (ዘፍ. 16.)። በዚህ ጊዜ ከሣራ ጋር ሰላም ጠፋ። አብርሃምም የፈለገው ልጅ ነበር። ልጅም ተገኘ ነገር ግን አልረካም። የሚፈልገውን ቢያገኝም ውስጡ ግን አልሞላም ነበር። ለምን? ስንል ያ ልጅ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል አልነበረም። ተስፋውን የሚቀድም የሰው ብልሃት ነበር። ስለዚህ ሰላም ጠፋ፣ እርካታም ራቀ። ዛሬ ድረስ የዘለቀው የፍልስጤምና የእስራኤል ጦርነት የእስማኤልና የይስሐቅ ዘሮች ጦርነት ነው። አቋራጭ መንገድ የ3 ሺህ ዓመት ጦርነትን ወለደ። በእኛ መንገድ ሀብትም፣ ትዳርም፣ ልጅም ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ሰላም የለውም። የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን እንኳን በረከቱ መከራው የልብ ሰላም አለው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረን ጸሎት *«ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን»* (ማቴ. 6፥10) እንድንል አዝዞናል። ሰማይ የደስታና የዕረፍት ቦታ ናት። የሰማይ ደስታና ዕረፍት ምሥጢሩ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ የፀናባት መሆኗ ነው። በሕይወታችን የሰማይን ደስታና ዕረፍት የምንለማመደው ፈቃዱ በእኛ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ስፍራ ሲያገኝ ነው። ጸሎት የእኛ ፈቃድ በሰማይ የሚሆንበት ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር የሚሆንበት ነው። ቃሉ *«እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል»* ይላል (1ዮሐ. 5፥14)።

ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ስናነሣ በፈቃዱ ዙሪያ ሦስት ዐቢይ ነጥቦች አሉ፦

1. የተገለጠ ፈቃዱ - የምንፈጽመው፤
2. የምንጠይቀው ፈቃዱ - የምንጸልይበት፤
3. የታወቀ ፈቃዱ - የማንደራደርበት፤

ፍቅር፣ ርኅራኄ፣ በጎነት፣ እምነት፣ ቸርነት፣ ይቅርታ፣ ለሌሎች ማካፈል፣ ... የተገለጠ ፈቃዱ በመሆኑ ለመፈጸም መትጋት አለብን፡፡ ለሕይወታችንና ለኑሮአችን ያስፈልጉናል የምንላቸውን በጸሎት የምንጠይቅበት ፈቃዱ ደግሞ ሁለተኛው ነው፡፡ ኃጢአትንና በደልን በተመለከተ ደግሞ የታወቀ ፈቃዱ በመሆኑ የማንጸልይበት፣ እግዚአብሔር ለዘብተኛ እንዲሆን አሳብ የማናቀርብበት የማንደራደርበት ፈቃዱ ነው፡፡ ኃጢአትንና ጽድቅን በተመለከተ ግራ የማንጋባበት ግልጽ ፈቃዱ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ጽድቁን ለማድረግ ኃጢአትን ለመተው ኃይል እንዲሰጠን በቊርጥ ልብ እንለምናለን፡፡ ለኑሮአችን የሚያስፈልገንን ነገር ደግሞ ፈቃዱን በመጠየቅ እንጸልያለን፡፡ ለምሳሌ፡- ሥራችንን፣ የትዳር ዓላማችንን፣. . . በተመለከተ ጌታ ፈቃዱን እንዲያሳውቀን በትሕትና እንጸልያለን፡፡



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## በስሙ መጸለይ

*«አንድ ደብዳቤ የሚደርሰው በጥሩ አጅ ጽሕፈቱ፣ በቃላት አጠቃቀሙ፣ በታሪክ ፍሰቱ ሳይሆን በአድራሻው ነው፡፡ አድራሻ የሌለው ደብዳቤ አይደርስም፡፡ እንዲሁም የጸሎታችን አድራሻ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፡፡»*

ወደ ህላዌ የመጣ ነገር ሁሉ ስም አለው፡፡ የህላዌ (የመኖር) መሠረት የሆነው እግዚአብሔርም ባሕርዩን የሚገልጡ የተለያዩ ስሞች አሉት፡፡ ስም የማንነት ወይም የምንነት መለያ ሲሆን አንዳንዴም መግለጫ ይሆናል፡፡ በግዙፉ ዓለም ስም የማንነት መለያ ሲሆን መግለጫ ግን ላይሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- ብዙ ሰዎች ከስማቸው ተቃራኒ በሆነ ኑሮ ይገኛሉ፡፡ የእግዚአብሔር ስሞች ግን እንደ ስሙ የሚሠራ አምላክ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ የእግዚአብሔር ስሞች የተገለጡባቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ስናጠና ሰዎቹ ላሉበት ሁኔታ መልስ በሚሰጥ ስሙ እንደ ተገለጠ እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ፡- አብርሃም ስለ ልጅ ተስፋ በቆረጠበት በ99 ዓመቱ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነቱን በሚገልጠው በ «ኤልሻዳይ» ስሙ ነው የተገለጠው (ዘፍ. 17÷1)፡፡

የእግዚአብሔር ስም የእግዚአብሔር ክብር ነውና ይህ ስሙ ለፍጡር አይቀፀልም (አይሰጥም) (ኢሳ. 42÷8)፡፡ ስሙንም ለአምልኮና ለምስክርነት ካልሆነ በከንቱ መጥራት የተከለከለ ነው (ዘፀ. 20÷7)፡፡ የእግዚአብሔርን ስም ማወቅ ያስፈልገናል፡፡ ስሙ ለፈውስ፣ ለድል፣ ለመጽናናት፣ ለምስክርነት፣ ለአምልኮ ይረዳናል፡፡ የእግዚአብሔርን ስሞች ስናውቅ ስለ እግዚአብሔር ያለን ዕይታም ይጨምራል፡፡ መጽሐፍ *«ስሙ ማን የልጁስ ስም ማን ነው?»* ይላል (ምሳ. 30÷4) ፡፡ ሙሴም *«ስሙስ ማን ነው? ባሉኝ ጊዜ÷ ምን እላቸዋለሁ?»* በማለት እግዚአብሔርን ጠይቋል (ዘፀ. 3÷13)፡፡

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በዕብራይስጥ ቋንቋ የታወቁት ስሞች እነዚህ ናቸው::

ኤል:- ኤል የሚለው ስም ኃያል (አምላክ) ማለት ነው:: በብዙ ሲጠራ ኤሊም ወይም ኤሎሂም ይባላል:: በዘፍጥረት መጽሐፍ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች «ኤል - ኤሎሂም» የሚለውን በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር አምላክ» በማለት ተተርጉሟል:: «ኤል ኤሎሂም» አምላክ - አማልክት የሚል ትርጉምም ይሰጣል:: ኤል ከብዙ ሁኔታዎችና ስሞች ጋር ተዛምዶ አገልግሎት ላይ ውሏል:: ለምሳሌ:- «ኤልሮኢ» «የሚያየኝን አምላክ አየሁት» (ዘፍ. 16÷13)፣ «ኤልሻዳይ» «ሁሉን ቻይ አምላክ» (ዘፍ. 17÷1፤ ዘፀ. 6÷3) ኤል ከሚለው ስም ጋር በመጣመር አገልግሰዋል::

ያህዌ:- ያህዌ ማለት «ያለና የሚኖር» ማለት ነው (ዘፀ. 3÷14):: በዕብራይስጥ ቋንቋ የታወቀው የእግዚአብሔር መጠሪያ ስም «ያህዌ» ነው:: እግዚአብሔር ያለ ብቻ አምላክ አይደለም የሚኖርም ነው:: ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ያሉ ነገሮች አሉ:: የሚኖሩ ግን አይደሉም:: ለምሳሌ:- ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያለ ድንጋይ አለ:: ግን የሚኖር አይደለም:: እግዚአብሔር ግን ያለና የሚኖር እንደ ስሙም የሚሠራ ነው::

ያህዌ የሚለው ስም ከሌሎች ምስጋናዎች ጋር ተጠቅሷል:: ለምሳሌ:- «ያህዌ ይርኤ» (እግዚአብሔር ያያል) (ዘፍ. 22÷14)፣ «ያህዌ ንሲ» (እግዚአብሔር ዓላማዬ) (ዘፀ. 17÷15)፣ «ሃሌ ሉያ» (እግዚአብሔርን አመስግኑ) የሚሉት በተዛማጅነት አገልግለዋል::

አዶናይ:- አዶናይ ማለት ጌታ ማለት ነው:: ይህ ስም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ «ጌታ» «አቤቱ» የሚሉትን ስፍራዎች ተክቷል:: በግእዙ የሕዝቅኤል መጽሐፍ ግን እግዚአብሔር የሚለው «አዶናይ» በመባል ተጠቅሷል:: አዲስ ኪዳን በተጻፈበት በግሪክ ቋንቋ ግን እግዚአብሔር ወይም አምላክ የሚለውን «ቴዎስ» ሲለው «ጌታ» የሚለውንም «ኪርዮስ» በማለት ተተርጉሟል::

በዕብራይስጡ ያህዌ ወይም ኤል ኤሎሂም የሚለውን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ብሎ ተርጉሞታል:: ይኸውም እግዚእ ማለት በግእዝ ቋንቋ ጌታ (ገዥ) ማለት ሲሆን ብሔር ማለት ዓለም ማለት ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔር ማለት «የዓለም ጌታ» (ገዥ) ማለት ነው::



ከተጸውኦ /ከመጠሪያ/ ስም በተጨማሪ እግዚአብሐር የሚጠራባቸው ስሞች አሉት:: እነዚህም የቅጽል ስሞች፣ የግነት ስሞች፣ የምስጋና ስሞች ይባላሉ::

## የቅጽል ስሞች:-

- አባት:- ለሁሉ የሚያስብ
- ልዑል:- ከፍ ያለ
- ቅዱስ:- የተለየ
- የሠራዊት ጌታ:- የፍጥረት ባለቤት
- የእስራኤል ቅዱስ:- ተወዳጅ
- ወሃቤ ጸጋ:- ጸጋን የሚሰጥ (አደላዳይ)
- አምላከ ብርሃናት:- የብርሃናት ገዥ

## የገናናነቱ ስሞች:-

- ግሩም:- ተፈሪ
- ድንቅ:- የሚያስገርም
- የኃያላን ኃያል:- የማይሸነፍ
- የአማልክት አምላክ:- የበላይ
- የነገሥታት ንጉሥ:- የሚገበርለት
- የጌቶች ጌታ:- ሀብቱ የማይጨረስ

## የምስጋና ስሞች:-

- ፈታሒ በጽድቅ፣ ኰናኒ በርትዕ:- እውነተኛ ፈራጅ
- ስቡሕ:- ምስጉን
- ውዱስ:- የተመሰገነ
- ቡሩክ:- የተባረከ
- ፊተኛውና ኋለኛው /አልፋ ያሜጋ/:- ዘላለማዊ ዘመን የማይመሽበት
- መዓቱ የራቀ ምሕረቱ የበዛ:- የኃጢአተኞች ተስፋ

በአዲስ ኪዳንም ጎልቶ የታወቀው የጌታችን ስም ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:-

- አማኑኤል

- ኢየሱስ
- ክርስቶስ
- የእግዚአብሔር ልጅ
- የሰው ልጅ
- ጌታ በሚሉ መጠሪያዎች ተጠርቷል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው። ስሞቹም ፍጹም ሰውነቱንና ፍጹም አምላክነቱን ይገልጣሉ። አማኑኤል፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ጌታ የሚሉት ስሞች አምላክነቱን ሲገልጡ ክርስቶስ፣ የሰው ልጅ የሚሉት ስሞች ደግሞ ፍጹም ሰውነቱን ይገልጣሉ። ኢየሱስ የሚለው ስም ደግሞ መለኮትና ሰውነት የተዋሃዱበት የተዋህዶ ስም ነው። የተዋህዶ ስም ብቻ ሳይሆን የተጸውኦ ስምም ነው። ኢየሱስ ማለት በግሪክ ቋንቋ አዳኝ- መድኃኒት ማለት ነው። ከምን የሚያድን? ስንል ከኃጢአት የሚያድን ማለት ነው (ማቴ. 1፥21)። ይህ ስም ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ሞገሳችን ነውና በዚህ ስም እንድንጸልይ ታዟናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምልኮአችን የሚያርገው በእርሱ ስም ስንጸልይ መሆኑን ገልጾልናል። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ ጥልቅ ምሥጢርና ፍቅር አለው።

የተከበረ ባለሥልጣን ዘንድ ሄደን «እገሌ ልኮኝ ነው» እንላለን። የእኛ ስምና ማንነት ሚዛን የሚደፋ ስላልሆነ የእገሌን ስም አስቀድመን ጉዳያችንን እናቀርባለን። ባለሥልጣኑም የወዳጁ ስም ሲጠራበት የወዳጁን ስሙን ብቻ ሳይሆን ውለታውን፣ ፍቅሩን፣ ታማኝነቱን አስታውሶ ወዳጁ ልክ ቢመጣ ለእርሱ የሚያደርግለትን አቀባበል ለእኛም ያደርግልናል። በታላቁ የእግዚአብሔር ዙፋን ፊትም ስንቀርብ የእኛን ማንነት ንቀነው በአንድ ታላቅ ስም እንቀርባለን። ይህ ትልቅ ትሕትና ሲሆን የሁላታችን ወዳጅ የሆነው ያ ስም ለማኙም የማያፍርበት ተለማኙም ፊቱን የማይመልስበት ስም ነው። እርሱም «ኢየሱስ ክርስቶስ» የተባለው ስም ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአምልኮ መስፈርቶች ሰጥቷል። እግዚአብሔርን ለማምለክ ስንነሣ እንደ ፈለግነው ሳይሆን እንደ ሚፈልገው ማምለክ አለብን። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ዋና ዋና የአምልኮ መስፈርቶች በመንፈስ ማምለክና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ ናቸው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ ስለ መጸለይ፡- *«እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ*



*አደርገዋለሁ»* (ዮሐ. 14፥13-14) በማለት ተናግሯል። በአገራችን ባሕል «አባ እገሌ» የእገሌ አባት ብሎ በበኵር ልጅ ስም መጥራት ፍቅርም ክብርም ነው። እግዚአብሔር አብም በልጁ ስም መሰመኑ ትልቅ ክብርና ፍቅር ነው። ለዚህ ነው አባቶቻችን በልመና፣ በምልጃቸው እንዲህ የሚሉት፡-

*«ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ»* ትርጓሜው፡- *«ሁሉን የፈጠረ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ዳግመኛ እንማልዳለን»* (መስተብቍዕ ተመልከት)።

በስሙ መሰመን በልመናችን መጨረሻ ላይ «በኢየሱስ ክርስቶስ ስም» ማለት ብቻ አይደለም። ጥልቅ ምሥጢሩ በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን አባት ብለን ለመጥራት ያገኘነውን የልጅነት መብት፣ በደሙ ፈሳሽነት ያገኘነውን ሕይወትና መንፈሳዊ ርስት እያሰብን በሊቀ ካህንነቱ ሥልጣን መጸለይ ነው። በስሙ የምንጸልየው ጸሎት ግዳጅ የሚፈጽም፣ ምስጋናችንንና መሥዋዕታችንን የሚያከብር ነው። ራሱ ጌታችን *«በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል። እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ»* ብሎናል (ዮሐ. 16፥23-24)። ፍጹም ደስታ በሕይወት ውስጥ ብዙ ጊዜ የለም። ማሩ ከእሬት ጋር የተለወሰ ነው። ጅምሩ ከፍጻሜው ጋር የማይጋጠም ነው። ከሙሉ ሀዘን በላይ ከፊል ደስታ ይጎዳል። ስለዚህ ደስታችሁ ፍጹም (ሙሉ) እንዲሆን በስሜ ጸልዩ አለ።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ መጸለይን በይበልጥ ግልጥ የሚያደርግልን የፊልጵስዩስ መልእክት ነው፡- *«በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው»* (ፊልጵ. 2፥9-11) ይላል።

በዓለም ላይ የማንም ስም ከማንም አይበልጥም። መዓረጉ ሊለያይ ቢችልም ስም ግን እኩል ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ግን ከስም ሁሉ በላይ የሆነ ስም ነው። የስም ሁሉ ጉልላት ነው። *«በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ»* የምትለውን ቃል ብዙ ጊዜ በልምድ የምናነባት «ለኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ» ብለን ነው። ሁለቱ ግን

ልዩነት አላቸው። በርግጥ ኢየሱስ ስግደት የሚገባው አምላክ ወልደ አምላክ ነው። መልእክቱ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ማምለክ የሚናገር ነው። *«በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ»* ዘንድ ማለት «በኢየሱስ ስም ያመልኩ ዘንድ» ማለት ነው።

እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ በማስተዳደር ትልቅ *ሥራ* ሠርቷል። በ*ታሪክ* ውስጥ ትውልድን በመተካት፣ *ነገሥታትን* በማፈራረቅ፣ በረከትን በማደል፣ ጦርነትን በማስቆም፣ ዳኝነትን በመስጠት ብዙ *ሥራዎችን* ሠርቷል። ለዚህም ምስጋና ይገባዋል። እግዚአብሔር ግን ከሠራው *ሥራ* ሁሉ አልቆ የሚመሰከተው በኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ያዳነበት ተግባሩን ነው። አባቶቻችን «እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል» የሚሉት ከዚህ ተነሥተው ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ሊመሰገንና ሊመለክ የወደደው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወይም በአዳኝነቱ ፍቅር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከዋለ ጊዜ አንሥቶ በሰማይም በምድርም ከምድርም በታች ያለ ምስጋና ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚቀርብ ሆኗል። ዮሐንስ በራእዩ እንዳየው፡- *«በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ሁሉ በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉ ይሁን ሲሉ ሰማሁ»* (ራእይ 5፥13) ብሏል።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጸሎታችን ብቻ ሳይሆን ተግባራችንም ይከብራል፡- *«እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት»* (ቆላ. 3፥17) ተብሏልና። ዳግመኛም (ሮሜ. 1፥8፣ ኤፌ. 5፥20)ን አንብቡ።

አንድ ደብዳቤ የሚደርሰው በጥሩ እጅ ጽሕፈቱ፣ በቃላት አጠቃቀሙ፣ በታሪክ ፍሰቱ ሳይሆን በአድራሻው ነው። አድራሻ የሌለው ደብዳቤ አይደርስም። እንዲሁም የጸሎታችን አድራሻ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። ስለዚህ በስሙ መጸለይ ይገባናል። የቤተ ክርስቲያን አባቶች በስሙ እንደሚጸልዩ ብዙ እናነባለን። አጠራራቸውም፡-

| | | |
|---|---|---|
| በአሐዱ ወልድከ | - | በአንድ ልጅህ |
| በፍቁር ወልድከ | - | በምትወደው ልጅህ |
| በቅንዉ ወልድከ | - | በተቸነከረው ልጅህ |
| በስቁል ወልድከ | - | በተሰቀለው ልጅህ |



እያሉ ይጸልያሉ። ለምሳሌ፡- በቅዳሴ ሐዋርያት መጀመሪያ ላይ፡- *«ነአኵተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ ዘበደኃሪ መዋዕል ፈኖከ ለነ ወልድከ መድኅነ ወመቤዝወ መልአከ ምክርከ»* ትርጓሜው፡- *«አቤቱ በተወደደ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ እናመሰግንሃለን። በኋለኛው ዘመን የምክርህን አበጋዝ መድኃኒትና ቤዛ የሚሆን ልጅህን የሰደድህልን»* በማለት በስሙ ያመሰግናሉ። በሰዓታቱ ላይም፡- *«ኦ አብ በእንተ ኢየሱስ ርድአነ- አብ ሆይ ስለ ኢየሱስ እርዳን»* እያሉ ይጸልያሉ። ሲያሳርጉም «በአማኑኤል ስሙ በፈሰሰ ደሙ ምሬአችኋለሁ ይቅር ብያችኋለሁ ይበለን» ይላሉ። ይህ በስሙ መጸለይ ነው።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ ለእግዚአብሔር አብ ክብርን መስጠት፣ ትሕትናችንን መግለጥ፣ ጸሎታችንን መቀደስ፣ ፍጹም ደስታን መቀበል፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን *ሥራ* አባ አባት ብለን ለመጸለይ ያገኘነውን ነፃነትና ክብር ማሰብ ነው (ሮሜ. 8፥15)።